ጅማ ዩኒቨርሲቲ

የሶሻል ሳይንስና ሂውማኒቲስ ኮሌጅ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ- ጽሁፍ (አማርኛ) ትምህርት ክፍል

ድህረ ምረቃ መርሃ ግብር


# ሚታዊ ሁነቶች ለታሪክ ማስኬጃነት ያላቸው አበርክቶ

# በዝጎራ መርበብት ልቦለዶች ማሳያነት


በ

ውብነሽ ወንድሙ



መስከረም 2012 ዓ.ም

ጅማ

# ሚታዊ ሁነቶች ለታሪክ ማስኬጃነት ያላቸው አበርክቶ

# በዝጎራና መርበብት ልቦለዶች ማሳያነት

ጅማ ዩኒቨርሲቲ

የሶሻል ሳይንስና ሂውማኒቲስ ኮሌጅ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ- ጽሁፍ (አማርኛ) ትምህርት ክፍል

ድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

በኢትዮጵያ ስነ-ጽሁፍና ፎክሎር ድህረ ምረቃ መረሀ ግብር ከፊሉን ማሟያ የቀረበ ጥናት

በ

ውብነሽ ወንድሙ

አማካሪ

ጌታቸው አንተነህ (PhD)

ሀብታሙ እንግዳው (MA)

መስከረም 2012 ዓ.ም

የሶሻል ሳይንስና ሂውማኒቲስ ኮሌጅ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ- ጽሁፍ (አማርኛ) ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

# ሚታዊ ሁነቶች ለታሪክ ማስኬጃነት ያላቸው አበርክቶ በዝጎራና መርበብት ልቦለዶች ማሳያነት

በ

ውብነሽ ወንድሙ

የፈተና ቦርድ አባላት

የአማካሪ ስም ፊርማ

_______________________________ _______________

የፈታኝ ስም ፊርማ

_______________________________ _____________

_______________________________ ______________

# ምስጋና

በመጀመሪያ ስለ ሁሉም ነገር ቅዱስና ኃያል የሆነው አምላክ እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ፡፡ በማስከተል ከዚህ በታች የዘረዘርኳቸው ሰዎችና ተቋማት በተለያየ መንገድ ለዚህ ጥናት መሳካት የየራሳቸውን ድርሻ ያበረከቱ ናቸውና ምስጋና ይገባቸዋል፡፡ ለአማካሪዬ ዶ/ር ጌታቸው አንተነህ ከመጀመሪያው የትልመ ጥናት ንድፍ ጀምሮ ሲያደርጉልኝ ለነበረው ቅንነትና የተገባ አስተያየት መስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡ ሃሳቤን በማንኛውም ሰዓት በፍፁም ቅንነት እና ዕውቀት በመስማት ለማንበብ ፍፁም ፈታኝ የነበሩትን በተለያዩ ጊዜያት ያቀረብኳቸውን ንድፎች ያለመሰልቸት በማንበብ እና እርማት በመስጠት ከመስመር እንዳልወጣ በእጅጉ ላገዙኝ የእውቀት ብቻ ሳይሆን የህይወት  መምህሬ ለሆኑት ለዶ/ር ለማ ንጋቱ ልባዊ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡ እንዲሁም ፈር አልባ  የነበረውን የመጀመሪያ ንድፍ ፈር በማስያዝ ገንቢ አስተያየታቸውን ለሰጡኝ ረዳት አማካሪዬ ሀብታሙ እንግዳው ምስጋናዬ ላቅ ያለ ነው፡፡  እንዲሁም የትምህርት እድሉን ለሰጠኝ ለጅማ ዩኒቨርሲቲ ኮሚውኒቲ ትምህርት ቤት ከፍ ያለ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

ይህንን ጥናት በማካሄድበት ጊዜ ሁሉ ከጎኔ በመሆን ብዙ ውለታዎችን ለዋላችሁልኝ ቤተሰቦቼ ከፍ ያለ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡ ጓደኞቼም በዚህ ጥናት ላይ ድርሻ አላችሁና ምስጋናዬ ይድረሳችሁ፡፡

# አጠቃሎ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ *በዝጎራና መርበበብት* ልቦለዶች ሚታዊ ሁነቶች ለልቦለዶቹ ታሪክ ማስኬጃነት ያበረከቱትን  አስተዋጽኦ መተንተን ነው፡፡  የጥናቱ ዘዴ አይነታዊ ሲሆን የመተንተኛ ስልቱ ደግሞ ብዝሀ ግብር (multifunctionalism) ዘዴን መሰረት  ያደረገ ፍካሬ ነው፡፡ በመረጃ አሰባሰብ ሂደትም ለጥናት በተመረጡት የአማርኛ ረጅም ልቦለዶች(ዝጎራና መርበብት) መፃህፍት ውስጥ ሚታዊ ባህርያት ያሏቸውን ሁነቶች ከልቦለዶቹ ታሪክ ለይቶ በማውጣት ለትንተና በሚያመች መልኩ በመመደብ  ሚታዊ ባህሪ ያላቸው ሁነቶች ከልቦለዶቹ ታሪክ ጋር እንዴት ውህደት እንደ ፈጠሩና ሚታዊ ባህርያት ያሏቸው ሁነቶች በልቦለዶቹ ታሪኮች ቀጣይነት ላይ ስላበረከቱት አስተዋጽኦ ለመርመር የሞከረ ነው፡፡ ለዚህም የሚቶሎጂና ስነፅሁፍን ድንበር መሰረት ያደረጉ ንድፈሃሳቦችን ለጥናቱ በሚያመች መልኩ በማሰናዳት ለትንተናው ማስኬጃነት አውሏል፡፡ ልቦለዶቹ ውስጥ ያሉትን ሚታዊ ሁነቶች ከአላማው አንፃር ለመመርመር ያመቹ ዘንድ የሁነቶችን ተለጣጣቂነት በመፍጠተር እና ጉዞ ትልም (ምንን እና ለምንን) በማሳየት  በሚሉ ሁለት ክፍሎች ተከፍለዋል፡፡ በምርምሩ ለማረጋገጥ እንደተሞከረው በልቦለዶቹ ውስጥ ሚታዊ ባህሪያት ያሏቸው ሁነቶች በታሪኮቹ ውስጥ በመግባታቸው በልቦለዶቹ ታሪክ ውስጥ ያሉ ሁነቶች ጥምረት የሰመረ እንዲሆን፣ ትልማቸውን ለመገንባትና ጥብቅ እንዲሆን ለማድረግ፣ ታሪኮቹ ተአማኒነትን እንዲላበሱ፣  አግባባዊ በሆነ መንገድ ታሪኮቹ አቅጣጫቸውን እየቀየሩ የልቦለዱ ይዘት እንዲያሰፋና ታሪኩ ወደፊት እንዲቀጥል ጉልህ ሚና እንደተጫወቱ ታይቷል፡፡

# ማውጫ

ይዘት ገጽ


ምስጋና........................................................................................I

አጠቃሎ.......................................................................................II

ማውጫ........................................................................................III

ምዕራፍ አንድ ........................................................................................ 10

መግቢያ........................................................................................ 10

1.1 የጥናቱ ዳራ........................................................................................ 10

1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ........................................................................................ 14

1.3 የጥናቱ ዓላማ ........................................................................................ 14

1.4 የምርምር ጥያቄዎች........................................................................................ 15

1.4.1 ዓብይ የምርምር ጥያቄ........................................................................................ 15

1.4.2 ንዑሳን የምርምር ጥያቄዎች........................................................................................ 15

1.5 የጥናቱ ጠቀሜታ........................................................................................ 15

1.6 የጥናቱ ወሰን........................................................................................ 16

1.7 የምዕራፍ አደረጃጀት ........................................................................................ 16

ምዕራፍ ሁለት........................................................................................ 17

ክለሳ ድርሳናት ........................................................................................ 17

2.1 ንድፈ ሃሳባዊ ዳራ........................................................................................ 17

2.1.1 የሚት ምንነት........................................................................................ 17

2.1.2 የሚት አፈጣጠር ........................................................................................ 22

2.1.3 ሚትን የድሮ ነገር ብቻ አድርጎ መደምደም የማይቻል ስለመሆኑ.................... 23

2.1.4 የሚት ምደባ ........ 24
2.1.5 የሚት አይነተኛ ጠባያት ........ 25
2.1.6 የሚት ተግባራት ........ 28
2.1.7 የሚት ተረክ አላባውያን ........ 29
2.1.8 ሚትና ስነ ፅሑፍ ........ 33
2.1.9 ሚቶ ኪን (mythopoesis) ........ 38
2.2 የተዛማጅ ጽሁፎች ቅኝት ........ 40
ምዕራፍ ሦስት ........ 47
የጥናቱ ሥነ-ዘዴና ዘዴዎች ........ 47
3.1. የጥናቱ ሥነ-ዘዴ ........ 47
3.2 የጥናቱ ዘዴ ........ 48
3.2.1 የመረጃ ምንጭ ........ 48
3.2.2 የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ........ 49
3.2.3 የናሙና አመራረጥ ........ 49
3.2.4 የመተንተኛ ስልት ........ 49
ምዕራፍ አራት ........ 52
የመረጃ ትንተና ........ 52
4.1 የልቦለዶቹ አፅሙ-ታሪክ ........ 52
4.1.1 የዝጎራ ረጅም ልቦለድ ጭምቀ ታሪክ ........ 53
4.1.2 የመርበብት ረጅም ልቦለድ ጭምቀ ታሪክ ........ 56
4.2 ለልቦለዶቹ ታሪክ ማስኬጃነት የሚታዊ ሁነቶች ፋይዳ ትንተና ........ 62
4.2.1 የሁነቶችን ተለጣጣቂነት በመፍጠር ........ 63
4.2.2 ጉዞ ትልም (ምንን እና ለምንን) በማሳየት ........ 76
ምዕራፍ አምስት ........ 87
ማጠቃለያ እና አስተያየት ........ 87
5.1 ማጠቃለያ ........ 87

5. 2 አስተያየት ........................................................................................................ 90

ዋቢዎች ...................................................................................................................... 92

# ምዕራፍ አንድ

# መግቢያ

## 1.1 የጥናቱ ዳራ

የሰዉ ልጅ ማንነቱን በሚሰራበት የማሰብና ያንን እሳቤ በኑሮ ዉስጥ የመተግበር ሂደት ላይ ብዙ ጥያቄዎች ተነስተዉበታል፡፡ አንደንዶቹን በጊዜ ሂደት የፈታቸዉና በተግባር ሊያረጋግጣቸዉ የቻላቸዉ ጉዳዮች ነበሩ፡፡ ቀሪዎቹ ጥያቄዎች ደግሞ ከአዕምሮ በላይ የሆኑ እና በደመነፍሱ ጉትጎታ መልስ ሊያገኝላቸዉ የሞከራቸዉ የመነሻዉና የመድረሻዉ ምንነት ጉዳዮች ነበሩ ለነዚህ ክፍተቶቹ መሙያ የሆኑት ደግሞ እራሱ የሰራቸው ሚቶች ናቸው፡፡ በዚህ ሂደት ውስጥም ሚቶችን መፍጠር ችሏል፡፡ለማ ንጋቱ(2002) ኦክፔውን በመጥቀስ ሚት ከአፈ ታሪክ ተመዞ እንደሚወጣ የገለፁ ሲሆን አፈታሪክ ከሚነገርበት ጊዜና ከተራኪው ነፃነት አኳያ ሚታዊ አፈ ታሪክና ታሪካዊ አፈታሪክ ተብሎ በሁለት የሚከፈል ሲሆን፣ታሪካዊ አፈታሪክ ተራኪውና ታዳሚዎቹ የሚኖሩበት ወይም በቅርብ የሚያውቁት የቅርብ ጊዜ ክስተት ትረካ ሲሆን እውነታዊነትን የተላበሰ ትረካ መሆኑንና የተዛባ ትረካ ቢቀርብ ሀይ ባይ ያለው መሆኑን ሲገልጹ ባንፃሩ ሚታዊ አፈ ታሪክ ደግሞ የጥንት የሚባሉ ታሪኮች ትረካ እንደሆነና በጥንታዊነታቸው ሳቢያ ታሪኩን በቅርበት የሚያውቁ አድማጮች ላይኖሩ ስለሚችሉ የተዛባ መረጃ እየቀረበ እንኳ ቢሆን ልክ አይደለም የሚል አድማጭ ስለማይኖር ተራኪው እዚህ ላይ የምናብ ነፃነት ያገኛል፡፡ (2002፣112-114) ነገር ግን በዚህ ጥናት ሚት የጥንት የሚባሉ ታሪኮች ትረካ ብቻሳይሆን የሰው ልጅ በየትኛውም ዘመን በሚያደርጋቸው መንፈሳዊም ሆነ ዓለማዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ የሚያጋጥሙትን የህይወት ዝብርቅርቆች ለመረዳትና መልክ ለማስያዝ ለዘመኑ በሚሆኑ መልኩ በማበጀት የሚገለገልበት መሆኑ ተጠቁሟል፡፡

አንድን ስነጽሑፍ ከተለያዩ ሙያዎች በሚመጡ ንድፈ ሀሳቦች እና ፅንሰ ሀሳቦች መመርመር የዘመናዊ ስነ ፅሁፍ ጥናት ልማድ ሆኗል፡፡ በመሆኑም አንድን ምንባብ በተለያዩ የሙያ መስኮች መነፅር መፈተሽና ትንታኔ መስጠት በየእውቀት ዘርፉ መካከል ያለውን ክፍተት ያጠበበና እርስ በእርሳቸው እንዲቀራረቡ ያደረገ አንድ ምክንያት ሆኗል፡፡ የኪነጥበብዘርፎች (ፎክሎር፣ ፅሁፋዊ ሥነጽሐፍ፣ሙዚቃእናትውንጥበባት ወዘተ.) በአጋጣሚምይሁን፣በልዩልዩኪናዊናነገረ-ዕውቀታዊምክንያቶችባሕርይይወራረሳሉ፡፡Wellek

እና Austen(1980)፡፡ሌሎችም ሊቃውንት እንደሚገልፁት ይህውርርስልዩልዩመልኮችናውስብስብባሕርያትአሉት፡፡በዚሁብያዝነውዘመንደግሞቁርኙቱከመ ጥበቅ፤ጥበባቱምሚናከመጋራትአልፈውመሂዳቸውንልዩልዩየነገረ-ኪንሊቃውንትይሞግታሉ (ለምሳሌ፣ Mitchell, 1986፤ Davies,2000፤ Rosenberg, 1969)

ይህ ጥናትም በስነጽሑፍና በሚቶሎጂየእውቀት መስኮች መካከል ያለው የጋራ ድንበር እንዲሁም በሚታዊ ባህሪ ባላቸው ሁነቶችና በልቦለድ ታሪክ መሀከል ያለን የእርስ በእርስ ተደጋግፎ ለመዳሰስ ጥረት ያደረገ ነው፡፡ የስነ ፅሑፍ ጥናት ከሰው ልጅ የአስተሳሰብና የአኗኗር ሂደት ጋር አብሮ እያደገና እየዘመነ የመጣ ጥበብ ነው፡፡ እንደ Rose De Angelis(1969) ስነ ጽሑፍ የማህበረሰቡን እውነታዎች ማህበራዊ ጉዳዮች የሚገልፅ ኪን በመሆኑ በማህበረሰቡ ውስጥ ከሚታይ ማንኛውም ማህበራዊም ሆነ ባህላዊ ለውጥና እድገት ተለይቶ የሚታይ አይደለም፡፡ ምክንያቱም ተመሳሳይ ባህላዊና ማህበራዊ አውድ እስካላቸው ድረስ ሁሉም ዲሲፒሊኖች እርስ በእርስ የተቆራኙና የተዋሃዱበይነ ዲሲፒሊናዊ ስለሆኑ ነው ትላለች (2002፣1)፡፡ ይህ ከሌሎች ዲሲፒሊኖች ጋር መቆራኘት የስነፅሑፍ ገናን ባህሪው ነው፡፡ በዚህም የተነሳ አንድም ከተለያዩ ዕውቀቶች የተቀዱ አስተሳሰቦች መከሰቻ ነው፡፡ አንድም ኪናዊ መዋቅሩንም ሆነ ጭብጡን ከተለያዩ እውቀቶች በመጡ ንድፈ ሃሳቦችና አስተሳሰቦች ያደራጃል፡፡

ስለሆነም የሥነ ጽሑፍ ጥናት በርካታ ሙያዎችን የሚነካካ እንጂ በሩን ዘግቶ ራሱን ያገለለ አይደለም፡፡ ቴዎድሮስ "ስነፅሑፍ የበርካታ ዲሲፕሊኖችን ድንበር እየጣሰ መሠረተ ሃሳቦቻቸውንና ንድፈ ሃሳቦቻቸውን በሚስማማው መልኩ ያለምዳል፡፡ እነሱም ተውሰው ያለምዳሉ፡፡" (2001፣xii)ሲሉ እንደገለፁት፡፡በመሆኑም ሚቶሎጂ ከተለያዩ ሰዋዊ ጉዳዬች ጋር የሚያስተሳስሩ ብዙ ግብሮች እንዳሉት ሁሉ ሥነ-ጽሁፍምየተፈጥሮንውበት፣ምስጢርናትርጉምከሰውልጅህይወት፤ከነባራዊውዕውነታናዓለምጋርአ ዋህዶበጥበብ ቀምሮ፤ምናባዊገላጭነትንተላብሶለተደራሲየሚቀርብውበት ያለው የምናብውጤትነው። ለስነ ፅሁፍ መሰረቱ ሰውና ገጠመኙእንደመሆኑየሰውን ልጅ ታሪክ ፣ገጠመኝ፣ ማህበራዊ ህይወትና ርዮተ ዓለም ታሪክ በመመዝገብ ወይም በመተንበይ በሰዎች የሚደረስና ለሰው ልጅ መማሪያ፣ ከአሰልቺው አለም ለአፍታ መከለያ እንዲሁም ማህበራዊ ሂስ መስጫ መድረክ ነው፡፡ እንግዲህ እነዚህ ሁለት ዘርፎች መሪ ጉዳያቸው ሰውና ገጠመኙ መሆኑ ከሚያመሳስሏቸው ባህሪያቶቻቸው ውስጥ አንዱ ተጠቃሽ ባህርይ ነው፡፡ በዚህም

የተነሳ በስነ ፅሁፍ ውስጥ  የሚታዩ ሚታዊ ጉዳዮችን መፈተሸና ማጥናት ፣ ለስነ ጽሑፉ ያላቸውን አስተዋጽኦ መመርመርና ያላቸውን ትዕምርታዊ ፋይዳ መተንተን ስነ ፅሁፋዊ ስራውን ለመረዳት አይነተኛ መንገድ ከመሆኑም ባሻገር ሁለቱ ጥበቦች ስለ ሰው ልጅ የሚሉትን መረዳትም ይቻላል፡፡

እንዲሁ

ልቦለድድርሰትምደራሲውመሠረታዊየሆኑየሰውልጅጉዳዮችንማለትምፖለቲካዊ፣ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊእሴቶችንመሠረትአድርጎለአንባቢአንጻችትምህርትሊሰጥበሚችልመንገድየሆነውን፣የ ተደረገውንወይምቢሆንየሚለውንምኞቱንወይምፍላጎቱንሥነ-ጽሑፋዊለዛሰጥቶየሚያቀርብበትየኪነጥበብዘርፍነው፡፡በኢትዮጵያ የስነ ፅሁፍ ታሪክ ሚታዊ ጉዳዮች በአማርኛ ልቦለዶች ውስጥ መታየት የጀመሩት ከልቦለድ ውልደት ጀምሮ ነው፡፡ከመጀመሪያው በሀገር በቀል ቋንቋ ከተፃፈው ጦቢያ ልቦለዳዊ ታሪክ ብንነሳ እንኳ የዋናዋ ገፀ ባህሪ ጦቢያ ታሪኳ የተቀዳውሚታዊ ባህሪ ካለው ከግብፃዊቷ ቅድስት እንባ መሪና[1] ህይወት ታሪክ ይመስላል፡፡(ጦቢያ 1901)

አለማየሁ ዋሴበ2007 ዓ.ምእመጓ በሚለው መፅሐፉ ከአንባብያን ጋር ከተዋወቀ በኋላ በተከታታይ ዝጎራና መርበብት የተባሉ ሶስት ስነ ፅሁፋዊ ስራዎችን አቅርቧል፡፡እነዚህ ልቦለዶች እውነተኛ ታሪኮች፣ የጉዞ ማስታወሻ ወይስ ልቦለድ ናቸው? የሚሉ ጥያቄዎች በተለያዩ የማህበራዊ ድህረ ገፆች ላይ የቀረቡ  ሲሆን  በመፅሐፍቱ ላይ እነዚህ ጥያቄዎች ሊቀርቡባቸው የቻሉባቸው ምክንቶች መኖራቸው እሙን ቢሆንም ቅሉ መፃህፍቱ ልቦለዳዊ ናቸው፡፡ ወደ ሚለው ሚዛኑ እንዲያጋድል የሚያደርጉ እንደመቅድም፣መግቢያ፣የይዘት ማውጫና ማጣቀሻ መፃህፍት፣ ለየምዕራፎቹ አርዕስት አለመሰጠቱ እና ወደ ውስጥ ዘለቅ ተብሎ ሲነበብ አቀራረቡ  የጊዜ ቅደም  ተከተለን አለመጠቀሙ፣ ዋና ገፀባህሪው(ሲሳይ) በዚህ ልቦለዱ ውስጥ ባለው አግባብ  በገሀዱ አለም አለመኖሩና በልቦለዶቹ ውስጥ በሚታየው መልኩ ገፀባህሪው የሚያከናውናቸው ተግባራት በትክክል በዚያ መልኩ የተተገበሩ

[1]ቅድስት እንባ  መሪና  በዘመነ  ፃድቃን  በምድረ ግብጽ የተወለደች፡፡ ከአባቷ ጋር መንና ወደ ወንዶች ገዳም የገባች ወንድ መስላ የወንዶችን ቀኖና በምንኩስና የጠቀበለች ፣ያለ አበሳዋ ወንድ መስላቸው ዝሙት ሰርተሻል ተብላ ብዙ መከራን በፀጋ የተቀበለች ቅድስት እናት ናት፡፡(መጽሐፈ ስንክሳር 1993፣690)

አለመሆናቸው፣ እንዲያውም ምልሰትን ደጋግሞ መጠቀሙን ስናይ መጽሐፍቱን እውነተኛ የታሪክ መፃህፍት አድርጎ ለመውሰድ ይቸግራል፡፡ ይልቅም ልቦለዳዊነቱ ሚዛን የሚደፋ ይመስላል፡፡ መፅሐፎቹ በተለያዩ መንገዶች ሊመረመሩ የሚችሉ ቢሆንም በዚህ ጥናት ለመመርመር የተመረጠው ደራሲው በመፅሐፎቹ ውስጥ በስፋት ሚታዊ ጉዳዮችን መጠቀሙን አጥኚዋ በማስተዋሏ በመፃህፍቱ ውስጥ ያሉ ሚታዊ ባህርያት ባላቸው ሁነቶች ላይ ትኩረት ተደርጓል፡፡

በአለማየሁ ስራዎች ላይ የተደረጉ ጥናቶች ካሉ በሚልበተደረጉ ፍተሻዎች መፃህፍቶቹን መሰረት አድርገው ለጥናት በተመረጠው ርዕሰ ጉዳይ ላይ የተጠኑ ሌሎች ጥናቶችን ማግኘት አልተቻለም ለአብነትምበጅማ ዩኒቨርሲቲ የሶሻል ሳይንስ ቤተ መፃህፍት በተደረገው ቅኝት በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ላይ በድህረ ምረቃ ደረጃ የተጠና አንድም ጥናታዊ ፅሁፍ ማግኘት አልተቻለም፡፡ ነገር ግን በ2007 ዓ.ምበስለሺ.አስፋው ለአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ የተደረገ አንድ ጥናታዊ ፅሁፍ በትምህርት ክፍሉ ለማግኘት የተቻለሲሆን የስለሺ ጥናት ዓላማ የ"እመጓ ረጅም ልቦለድ ፎክሎራዊ ፋይዳ ለይቶ ማሳየት ላይ ያተኮረነው" የሚል ሲሆን ፎክሎራዊ ጉዳዮችን ለይቶ በማውጣት የፎክሎርንና የስነ ፅሑፍን ትስስር ለማሳየት የተጠና ጥናት ነው፡፡የአንድ ሰው ስራን በመምረጥ ከዚህ ምርምር ጋር ቢመሳሰልም በቴክስት ምርጫም ሆነ በርዕሰ ጉዳይ ከዚህ ጥናት ጋር ልዩነት አለው ፡፡

ስለዚህ ሚታዊ ባህርያት ያላቸው ሁነቶች ለልቦለድ ታሪክ ማስኬጃነት ያላቸውን አበርክቶ ርዕሰ ጉዳዩ አድርጎ የተጠና ጥናት ባለመኖሩ በዚህ ክፍተትና በአንድ የእውቀት ዘርፍ ላይ ብቻ ተወስኖ ጥናቶችን ከማካሄድ ባሻገር የተለያዩ የእውቀት ዘርፎች ያላቸውን የጋራ ድንበር መሰረት አድርጎ፣ተደጋግፏቸውንና በውስጣቸው ከሚያነሷቸው ጉዳዮች የጋራ የሆኑትን መዞ በማውጣት የእርስ በእርስ ትስስራቸውን ማሳየት የሚቻል መሆኑን ለመጠቆም በማሰብ ጥናቱን በዚህ ርዕስ ላይ ለማድረግ ተችሏል፡፡ ይህ ጥናትም በይበልጥ ትኩረቱን ሚታዊ ባህሪ ባላቸው ሁነቶችና በልቦለዶቹ ታሪኮች ላይመሰረት ያደረገ ነው፡፡ጥናቱየተካሄደባቸውልቦለዶችዝጎራ እና መርበብትሲሆኑጥናቱ በአምስት ምዕራፎች ተዋቅሮ ቀርቧል፡፡

## 1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

ይህንን ጥናት ለማካሔድ ካነሳሱኝ ምክንያቶች ውስጥ ዋነኛው የደራሲው የአጻጻፍ ቴክኒክና የታሪክ አወቃቀር ትኩረቴን መሳቡ በተጨማሪበድህረ ምረቃ መርሐ ግብር በክፍል ውስጥ ባገኘኋቸው እውቀቶች ፎክሎር እና ሥነጽሑፍ በባሕርይ እና በግብር እጅግ ተዛምዶ እንዳላቸው ያስተዋልኩ ሲሆን፣ እነዚህ በባሕርይም ሆነ በግብር የተገለጹትፈርጀ ብዙ ዝምድናዎች በወጉ ቢመረመሩ ለዘርፉ እድገት ከፍ ያለ ጠቀሜታ የሚያስገኙ በመሆኑ እና በተለይ የኢትዮጵያ የፎክሎር ታሪክ በወጉ የተመረመረ ባለመሆኑ ከሥነ ጽሐፍ አቅጣጫ ቢጠና አንድ የሆነ ጠቀሜታ ይኖረዋል በሚል ጥናቱን ለማድረግ ተገፋፍቻለሁ፡፡

ልቦለዶቹ ለምርምር የሚሆኑ ብዙ ጉዳዮች እንዳሏቸው ባስተውልም፣ነገር ግን በዚህ ስሜታዊነት በተጫነው ግንዛቤ ውስጥ ሆኜ ጥናቱን በምን መልክ(በምን አይነት መንገድ) ማከናወን እንዳለብኝ መወሰን ትልቅ ፈተና ሆኖብኝ ነበር ነገር ግን በሁለቱም ልቦለዶች ውስጥ ሚታዊ ጉዳዮች በስፋት በልቦለዶቹ ታሪክ ውስጥ መገኘታቸውን በመገንዘቤ ሚታዊ ባህሪያት ያሏቸው ሁነቶች ለልቦለዱታሪክ ማስኬጃነት ያላቸው አበርክቶ ትንተና በዝጎራና መርበብትልቦለዶች ላይ በሚል ርዕስ ጥናቴን ለማካሄድ ወሰንኩ፡፡

## 1.3 የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ ዝጎራ እናመርበብትበተሰኙ ረጅም ልብወለዶች ውስጥያሉ ሚታዊ ሁነቶች ለልቦለዱታሪክ ቀጣይነት ያበረከቱትን አስተዋጽኦ መመርመር ሲሆን የሚከተሉት ዝርዝር ዓላማዎች አሉት፡፡

- በልቦለዶቹ ውስጥ የቀረቡትሚታዊባህርያት ያሏቸው ሁነቶችየቀረቡበትን መንገድ ይመረምራል፡፡
- በልቦለዶቹ ውስጥ ደራሲው ሚቶችን እንዴትእንደ ከየናቸው ይፈትሻል፡፡
- የደራሲውን የታሪክ አቀራረብ ስልት ይመረምራል፡፡

## 1.4 የምርምር ጥያቄዎች

ይህ ጥናት ይዟቸው የተነሳቸው አጠቃላይና ዝርዝር አላማዎችን ለመፈተሽ የሚያግዙ የምርምር ጥያቄዎች እንደ አላማው ሁሌ በዓብይና ንዑሳን የምርምር ጥያቄዎች በሚል እንደሚከተለው ቀርበዋል፡-

### 1.4.1 ዓብይ የምርምር ጥያቄ

- በሁለቱ ልቦለዶች ውስጥ የሚገኙት ሚታዊባህርያት ያሏቸው ሁነቶችለልቦለዶቹታሪክ ቀጣይነት ያበረከቱት አስተዋጽኦ ምንድነው?

### 1.4.2ንዑሳን የምርምር ጥያቄዎች

- በልቦለዶቹ ውስጥ የሚታዩት ሚታዊ ባህርያት ያሏቸው ሁነቶች በምን አይነት መንገዶድቀረቡ?
- በተመረጡት ልቦለዶች ውስጥ ደራሲው ሚቶችን በምን አይነት ኪናዊ ስርዓት አቀረባቸው?
- የደራሲው የታሪክ አቀራረብ ስልት ምን ይመስላል?

## 1.5 የጥናቱ ጠቀሜታ

የመጀመሪያውናመሠረታዊውጠቀሜታሊሆንየሚችለው፣ለምርምሩ፡መነሳሳትጉልህአስተዋጽኦያደረገውናበጥናቱዳራየቀረበውንየጥናት ክፍተትመሙላትነው፡፡ይህምበዘርፉላለውዕውቀትአንዳችክፍተትንሊሞላይችላል፡፡በተጨማሪም ፡-

- የደራሲውን ስራዎች ከሚቶሎጂ አንፃር በመፈተሽ ስራዎቹን በተሸለ መልኩ ለመረዳት ያስችላል፡፡
- ሚቶሎጂ እናሥነጽሑፍያላቸውንትስስርሊያሳይይችላል፡፡ይህምየሥነጽሑፍንበይነ-ዲሲፕሊናዊነትእና የሚትን ብዝሀ ግብርነት ያሳያል፡፡
- ደራሲው ስነ ጽሑፉን ለማደራጀት የተጠቀመባቸውን ሚታዊ ጉዳዮች ለማየት ያስችላል፡፡
- በተመሳሳይ ርዕሰ ጉዳይ ዙሪያ ለሚደረግ ጥናት የራሱ የሆነ በጎ አስተዋጽኦ ይኖረዋል ተብሎ ይታሰባል፡፡

## 1.6 የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት በአለማየሁ ዋሴዝንሪና መርበብት ልቦለዶች ወስጥሚታዊ ሁነቶች ለልቦለዶቹ ታሪኮች ማስኬጃነትላይ ካበረከቱት አስተዋጽኦ አንጻር ሚቶሎጂያዊ ፅንሰ ሃሳቦችን መሰረት ያደረገንባብ በማድረግ መፈከር ላይየተገደበነው፡፡

## 1.7 የምዕራፍአደረጃጀት

ይህጥናትበአምስትምዕራፎችየተከፈለነው፡፡ምዕራፍአንድየጥናቱመግቢያሲሆንበዋነኝነትየጥናቱ ንዳራ፣የጥናቱንአነሳሽምክንያት፣የጥናቱንየምርምርጥያቄዎች፣የጥናቱንዓላማዎች፣የጥናቱንጠቀ ሜታእናየጥናቱንወሰንአካቷል፡፡

ምዕራፍሁለትየጥናቱአብይጉዳይለሚሆነውፅንሰሃሳብትውውቅንየሰጠክፍልነው፡፡ይህምበዋነኝነት የንድፈሃሳብዳሰሳ፣የሚትፅንሰሃሳብእናየሥነጽሑፍንተዛምዶና የተዛማጅጥናቶችንቅኝትያካተተነው፡፡

ምዕራፍሦስትየጥናቱ ስነ ዘዴና ዘዴዎች የቀረቡበትሲሆን የማቅረቢያ ስልትን፣የመረጃ አሰባሰብን፣የመረጃ ምንጮችን፣የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎችን፣የናሙና አመራረጥን እና የመተንተኛ ስልትንያካተተነው፡፡

ምዕራፍአራትበሁለት ዋነኛንዑሳንርዕሶችየተከፈለነው፡፡የመጀመሪያውንዑስክፍልየሁነቶች ተለጣጣቂነት በተመረጡትሁለትልቦለዶችውስጥ የሚል ሲሆን የሚት ተረክ ባህሪያትን መሰረት በማድረግ ቅንጣቶችን ከልቦለዶቹ ታሪኮች ውስጥ መዞ በማውጣትበታሪኮቹ ቀጣይነት ላይ ያላቸውን አበርክቶ ለማሳየትየተደረገውንትንታኔየያዘነው፤ሁለተኛውክፍልእንዲሁጉዞ ትልም የሚል ንዑስ ክፍል ሲሆን ደራሲው የሚት አላባውያን አሳሳል ዘዴን በመከተል ታሪኮቹን እንዴት ምክንያታዊ በሆነ መንገድ በማዋቀር እርስ በእርሳቸው እንዲተሳሰሩ ማድረግ እንደቻለ የተገለጸበትንትንታኔያካተተነው፡፡

ምዕራፍአምስትበጥናቱአራትምዕራፎችየተብላሉትሃሳቦችማጠቃለያ፣ከልቦለዶቹ ጥናትየተደረሰበትመደምደሚያእናለጥናቱቀጣይነትየቀረቡየማመላከቻሃሳቦች የቀረበበትክፍልነው፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

# ክለሳ ድርሳናት

በዚህ ምዕራፍ ሚትን የተመለከቱ ንድፈ ሐሳቦች እና ጽንሰ ሃሳቦች እንዲሁም ከዚህ ጥናት ጋር ተዛማጅ የሆኑ ጥናታዊ ጽሑፎችና መጣጥፎች ተቃኝተዋል፡፡

## 2.1 ንድፈ ሃሳባዊ ዳራ

በዚህ ንዑስ ክፍል የሚት ምንነትና አፈጣተር፣ የሚት ጠባያትና አላባውያን፣ የሚትና የስነጽሑፍ የወል ተጋቦት እና ሚቶ ኪንን የተመለከቱ ንድፈ ሐሳባዊ ጉዳዮች የዘርፉን ምሁራን መሰረት በማድረግ ንድፈሐሳባዊ ዳራ ቀርቧል፡፡

### 2.1.1 የሚት ምንነት

ሚት በጣም ሰፊና ጥልቅ የሆነ ጽንሰ ሀሳብ ነው፡፡፡ይህ ስፋቱም በተለያየ መንገድ ሊጠናና ሊፈከር የሚችል ረጅም ስር ያለዉ የዕዉቀት ምንጭ አድርጎታል፡፡ በዘርፉ ታላላቅ ሥራዎችን ያበረከቱት Joseph Campbell (1949፣353) እንደ ሚቶሎጂ በዘመናዊ አስተሳሰብና ዕዉቀት ዉስጥ፣ በተለያየ መንገድ ሊፈከርና ሊበየን የሚችል ነገር እንደሌለ ይገልጻሉ፡፡ በተለያዩ የዕዉቀት ጎራዎች ዉስጥ ያሉ ምሁራን ስለሚት የተለያዩ ብያኔዎችን እና ትርጓሜዎችን የሰጡ ቢሆንም ዋነኛ ማጠንጠኛቸው ወደየሰለጠኑበት የእውቀት መስክ ያጋደለ በመሆኑም ሚትን ይበልጥ ለመረዳት ‹‹ሚት ምንድን ነዉ?›› በሚለው ጥያቄ ላይ መመስረት እንዳለበት ካምቤል ይመክራሉ፡፡ በዚህም ሚቶሎጂን በሰዉ ልጅ ያለፈና የአሁን ህይወት ዉስጥ እንደ ግለሰብም ሆነ እንደ ቡድን በዘመኑ የማይቀየር እና ዘወትር የሚብሰለሰል የህልዉና መሰረት መሆኑን ይገልጻሉ፡፡ የሰው ልጅ በዓለም ሲኖር ለማንነቱ፣ ለምንነቱና ለከየትመጣነቱ ፍቺ ለመፈለግ ያልሞከረበት ዘመንየለም፡፡ በየዘመኑ ለራሱ፣ ለአካባቢዉና ለቀረበዉ ዓለምትርጉም ሲፈልግና ሲያበጅ ኖሯል፤ እየኖረም ነዉ፡፡ ሰዉ ማህበራዊና እርስ በእርሱ እጅግ የተቆራኘ ፍጡር ነዉ፡፡ ይህ ማህበራዊነቱ የተፈጠረዉ በጊዜ ብዛት ባገኘዉ የህይወት ልምድና ዕዉቀት ነው፡፡ ሰዉ ከመሰሉ ጋር ህብረት ከመፍጠሩና ማህበራዊ ስርዓቱን ከመስራቱ በፊት ግን ራሱን ከራሱና ከሚኖርበት አካባቢ ማስታረቅ ነበረበት፡፡ በዚህ ምንነቱን በሚሰራበት የማሰብና ያንን እሳቤ በኑሮ ዉስጥ የመተግበር ሂደት ላይ ብዙ ጥያቄዎች ተነስተዉበታል፡፡ አንዳንዶቹ በጊዜ ሂደት የፈታቸዉና በተግባር ሊያረጋግጣቸዉ የቻላቸዉ ጉዳዮች ነበሩ፡፡ ከእነዚህ ጥያቄዎች

ዉስጥ ከአዕምሮ በላይ የሆኑ እና በደመነፍሱ ጉትጎታ መልስ ሊያገኝላቸዉ የሞከራቸዉ የመነሻዉና የመድረሻዉ ምንነት ጉዳዮች ዋነኞቹ ናቸዉ፡፡ ለነዚህም በሚቶቹ መልስ ሰጥቷል፡፡

ይህ ለረቀቁና በተግባር መረጋገጥ ለማይችሉ መንፈሳዊ ጉዳዮች በምናቡ በሚፈጥራቸዉ ተረኮች መልስ በመስጠት ራሱን ከዓለም ጋር የሚያስተሳስርበት ሂደት ሚት ይባላል፡፡ የሰው ልጅ ራሱን ከማያውቃቸዉ ትናንት እና ነገን (መነሻውና መድረሻውን) በማስታረቅ ዛሬን እንዲኖር እንደ ግለሰብም ሆነ እንደማህበረሰብ የፈጠራቸው ሚቶች የህልውና መሰረቶች ናቸዉ፡፡ለዚህም ነዉ ብዙ የነገረ ሰብእ ተመራማሪዎች በቀጥተኛ ሁኔታ ከሰዉ ልጅ ህይወት ጋር እንደተያያዘ የሚናገሩት፡፡"ሚት የሰው ልጅ የነገረ ፍጥረትና የነገረ ህላዌ እንቆቅልሾችን (cosmological and ontological questions) ለመመለስ የሚሞክርበት እየተመሰቃቀለ ለሚያስቸግረው ዓለም ህልው ሥርዓት(cosmic order) ለማበጀት የባተለበት እምነታዊና ፍልስፍናዊ ጥበብ ነው" በማለት ቴዎድሮስም የሚገልጹት(2001፣xii)

ሚትምንነቱ፡ ሚቶስ (mythos) የሚለው የግሪክ ቃል ሲሆን ትርጉሙም "ቃል"፤"ንግግር" ወይም "የአማልዕክት ተረት"ማለት ነዉ፡፡ይህንን ብዙዎቹ የሚት ተመራማሪዎች የሚሰማሙበትን የሥርወ ቃል ጣጣ የሚቀበሉትDaneis (2004፤145) "ሚቶሎጂ"የሚለዉ መጠሪያ የየባህሉ የሚት ልማድ ከመጠቆም ባለፈ ፤የሚት ጭብጥን፣ገጸ ባህሪን እና ትልምን በዘመናዊ መልክ ተስተካክለዉ መምጣትን የሚጠቁም መሆኑን ያስረዳል፡፡ሚቶስ (mythos) የቀደመዉን ሚታዊ አስተሳሰብና ሎጎስ(logos) የተጠየቃዊ ሳይንስ አስተሳሰብ ጥምረትን የሚያሳይ እንደሆነም ይጠቁማሉ፡፡ይህም የሚያሣየዉ ሚት በየዘመኑ ከሚፈጠሩ ዕውቀቶች ጋር አብሮ የሚዘምንና ለየዘመኑ በሚሆን መልኩ በድጋሚ የሚደራጅ መሆኑን ነዉ፡፡

የሰዉ ልጅ በየዘመኑ እያደገና እየሰለጠነ እንደመምጣቱ ለዘመኑ የሚሆኑ ሚቶች መፍጠርና ሚቶቹን በዘመኑ ልክ ማደራጀት መቻሉም ይታመናል፡፡ሚት ጥንታዊና የቀደመውን ዘመን ብቻ የሚወክል ተረክ አይደለም፡፡ ይልቁንስ ጥንታዊ ከሆኑ ሚታዊ ጉዳዮች ውስጥ የማይቀሩ ወይም የማይለወጡ የሚባሉ የሰው ልጅ ሁለንተናዊ ባህሪያትን በያዙ ነባር ተረኮች አሁንም እንገለገላለን፡፡በተጨማሪም ለዘመኑ እንዲሆኑ አድርጎ የበፊቶቹን ማበጀት እንዲሁም አዳዲስ ሚቶችን መፍጠር ጭምር የሚት ሂደት ነዉ፡፡ይህንን ሀሳብ በሚት ላይ ብዙ ምርምር ያደረጉ ምሁራን የሚገልፁት ሲሆን ሚት በተወሰነ ዘመን ተገድቦ የኖረ ሳይሆን በሁሉም ዘመን የነበረ እና ወደፊትም የሚኖር እንደሆነ ይስማሙበታል(ለምሳሌ

Leeming. 2002፣ Segal 2001፣ Daneis 2004፣ ወዘተ.መጥቀስ ይቻላል)፡፡ይህም የሚጠቁመን የሰዉ ልጅ በነበረበት ዘመን ሁሉ ለዘመኑ እና ለአኗኗሩ እንዲመች አድርጎ የፈጠራቸዉ ሚቶች እንዳሉ እና ወደፊትም እንደሚኖሩ ነዉ፡፡

በሌላ በኩል ከላይ በተገለጹት ምሁራን ገለጻ ውስጥ  ሚት በሁሉም ማህበረሰብ ዉስጥ በየዘመኑ መገኘቱ፣በየማህበረሰቡ ዉስጥ የሚገኙ ግለሰቦች በሚቱ በመገልገል ብቻ ሳይሆን በመፍጠርና ለዘመኑ እንዲመች በማድረግ ሂደትም አስተዋፅኦ እንዳላቸዉ የሚያሳይ ነዉ፡፡ሚትን የመፍጠር ስርዓት በሁሉም ማህበረሰብ ዉስጥ የተለመደና ወሳኝ የህይወት ሂደት ቢሆንም የሚፈጠሩ ሚቶች ማህበረሰቡ እንዲቀበላቸዉ በከፍተኛ ሁኔታ ይታሰብባቸዋል፡፡ይህም የሚሆነው ሚቶቹ የማህበረሰቡ አስተሳሰብ፣እምነትና ሞራላዊ ድንጋጌዎች ማደሪያ ከመሆናቸው ባሻገር ከፍተኛ የምናብ ርቀት ስለሚታይባቸዉ ነዉ፡፡ሚቱ ከነዚህ እና ሌሎች ማህበረሰባዊ ማንነቶች ጋር ያልተዋኻደ ከሆነ ግን ማህበረሰቡን የመግለጽ አቅም ስለማይኖረዉ ተቀባይነትንእንደ ሚያጣ ይገልጻሉ፡፡ቴዎድሮስም በተመሳሳይ "ሚት በምርምር የማይደረስበትን፣በተግባር የማይረጋገጥን ልዕለ አካላዊ ጉዳይ በመንፈስ ፣በምናብ ኃይል የምናቀርብበት የአስተሳሰብ ስርዓት ነዉ(ገጽ 68)፡፡"ሲሉ ይገልጻሉ.በተጨማሪም ሚት ብዙ ጉዳዮችን እንደሚነካና ከብዙ የሰው ልጅ የህይወት ልምዶች ጋር ጥብቅ ቁርኝት ያለው መሆኑን ቴዎድሮስ በሚከተለው መልኩ ይገልጻሉ፡፡

> ሚትየሰው ልጅ የነገረ ፍጥረትና የነገረ ህላዊ እንቆቅልሾችን (cosmological and ontological questions) ለመመለስ የሚሞክርበት እየተመሰቃቀለለሚያስቸግረው ዓለም ህልው ሥርዓት(cosmic order) ለማበጀት የባተለበት እምነታዊና ፍልስፍናዊ ጥበብ ነው፡፡ሚት የየማህበረሰቡ የእሴት ስርዓትም ነው፡፡ እንደ ጥሩና መጥፎ፣ ትክክልና ስህተት፣ጽድቅና ሀጢያት፣ንፅህናና ወንጀል ያሉ እጅጉን ምግባራዊእምነታዊ የሆኑ ኅሊናዊና አእምሯዊ ጉዳዮች ምን ማለት እንደሆኑበይኗል፡፡ ሚት የሰው ልጅ ሃይማኖታዊ፣ፍልስፍናዊ፣ማህበራዊ፣ኪናዊ ወዘተ.ሰነድ ነው፡፡
> (2001፣xi፣ xiii)

በመሆኑም ከላይ ከተገለጹት ሃሳቦች መረዳት እንደሚቻለው ሚት የሰዉ ልጅ ከየት መጣሁ? ወዴት እሄዳለሁ? ወዘተ.ለሚሉት የነገረ ህላዌ ጥያቄዎች መልስ የሚሰጥበት እና ለዚሁ መልሱ ራሱን የሚያስገዛበት ስርዓት ጭምር ነው፡፡ይህ የህላዌ ጥያቄ በግልም ሆነ

በማህበረሰቡ ደረጃ የሚፈጠር ሲሆን ከፍተኛ የአዕምሮ ርቀትን የሚጠይቅ እና ለሚነሱ ተያያዥ ጥያቄዎች ሁሉ አሳማኝ እና ልብን የሚያሳርፍ መልስ ማግኘትን የሚሻ ነዉ፡፡በመሆኑም በመልስ ሰጪነታቸዉ የላቁና የአብዛኛዉን የማህበረሰቡን ክፍል አስተሳሰብ የሚገዙ ሚቶች የሚኖራቸዉ ተቀባይነት የጎላ ነዉ፡፡በዚህ የተነሳ ግለሰብም ሆነ ማህበረሰብ ራሱን በነዚህ ሚቶች ዉስጥ በመከተት ለህይወቱ ትርጉምይሰጣል፣ራሱንም ያስገዛል፣ለኑሮዉና ለአእምሮዉ ሰላምና መረጋጋትን ይፈጥራል፡፡የሚት መኖር የሰዉ ልጅ የህይወት አቅጣጫን መስመር ያስያዘና ትናንትናን መሰረት አድርጎ ዛሬን እንዲኖርና ነገን ተስፋ እንዲያደርግ ያስቻለ ነዉ፡፡በተጨማሪም ለማህበራዊ ትስስሩ መጠንከር ፣ለማህበረሰቡ የጋራ ርእይ እና ስምምነት መሰረት ነዉ፡፡

ለብዙ የሚት ተመራማሪዎች ፣በተለይም ለJoseph,Campbell ሚታዊ ተጋዳሊ ከላይ የተዘረዘሩት እሴቶች ማደሪያ፣የማህበረሰቡም የወል ማንነት ማድሪያ ነዉ፡፡(Campbel፣1949፣18) እንደCampbel አገላለጽ ሚት በተጋድሎ የተሞላ ተረክ ሲሆን ተጋዳሊዉ (ሴትም ልትሆን ትችላለች)የሚኖርበት ማህበረሰብ ውስጥ ካለ ከፍተኛ አካባቢያዊ ተጽዕኖ ጋር ጦርነት ከፍቶ አንዳች በጎ ለውጥ የሚያስገኝበት ነዉ፡፡የማህበረሰቡ ባህልና እምነት የሚገመድበት የተጋዳሊ ሚት ረጅም ዘመን ያስቆጠሩ ፣ትዕምርታዊና ሁለንተናዊ (አርኬታይፓዊ) የሆኑ የተጋዳሊዎች ባህሪያትን የያዘ ነዉ፡፡"የተረት ተጋዳሊሚት አርኬታይፓዊ የሆነ ወሳኝ ባህሪም ለላቀ ዓላማ ራስን አሳልፎ መስጠት ነዉ"የሚለዉ Leeming. (2002፣118) ተጋዳሊውየነበረውን ስርዓት በመናድ የራሱን አዲስ ስርአተ ዓለም ያበጃል እንጂ በቀደመው ስርዓት ራሱን እንደማይዳኝም ይገልጻል፡፡

Froyidም ሆነ psychoanalysts እንደሚስማሙበት ሚት እጅግ ሰፊና ለብዙ ዲሲፕሊኖች መሰረት ነዉ፡፡በመሆኑም በተለያዩ ሙያዎች ዉስጥ ባሉ ምሁራን (በፎክሎር፣በነገረ-መለኮት፣በታሪክና በነገረ ሰብእ)ከሚሰጠው ትርጉም የላቀ እና ብዙዎቹን የሚጠቀልል ነዉ(Merku፣2005፣4)፡፡በዚህ የተነሳም ከሌሎች ሙያዎች ጋር ያለውን መስመር ለይቶ ራሱን ለብቻ የከለለበት ድንበር የለውም፡፡ለዚህ ነው ሚትን የሚበይኑ ምሁራን ከራሳቸው የዕዉቀት አቅጣጫ ብቻ በማየት ለእነሱ ሙያ እንዲስማማ አድርገው የሚያቀርቡት፡፡"ያለሚት እኖራለሁ ብሎ የሚያስብ ካለ እሱ ወፍዘራሽ ነዉ፡፡የቅድመ አያቶቹን ህይወት በሱ አይቀጥልም፣ አሁን ካለው ማህበረሰብም ተክክለኛ ግንኙነት አይኖረውም"የሚሉትCarl Yung ዮንግ ማንም ቢሆን ራሱን ከሚት ግዛት ሊያወጣ

እንደማይችል ይገልጻሉ፡፡ራሱን ከሚት ለመነጠል ቢሞክርም እንኳን ስለማንነቱ የማያውቅ እና ከዛሬ ጋር ጭምር የተፋታ ስለሚሆን ኑሮውቀውስ (chaos)ውስጥ መግባቱ እውን እንደሆነ ይናገራሉ፡፡(በHuskinson ተጠቅሶ የተብራራ፣ 2008፣3)፡፡ከዚሁበማያያዝ Huskinson ሚት የእኛነታችንን ሀረግ ከዓለም ጋር የሚያስተሳስርበት እና ሰዉ የመሆንን ትርጉም የምንፈልግበት መንገድ መሆኑን ያሳያል፡፡ይህም ሚት የሰዉ ልጅ ራሱን ከዓለም ጋር የሚያሠተሳስርበበት እና ስለራሱም ሆነ ስለሌሎች ትርጉም የሚሰጥበት ስርዓት መሆኑን ያሳየናል፡፡

ሚትየሰዎች ምናብ ዓለምአቀፋዊቋንቋ ነው፡፡ (Myth is the universal tongue of the human imagination.) የሚሉትደግሞLarsen (1990፣ XVII) ሲሆኑ ስለሚት እውነተኛ ታሪክ መሆን አለመሆን ከእምነት ጋር በማያያዝከሚገልጹት ወስጥ አንዱ የሆኑትPettazzoni (1984፣102) “ሚት እውነተኛ ታሪክ ነው፤ ምክንያቱም በይዘቶቹ ምክንያታዊነት ብቻ ሳይሆን ከቅዱሳን ኃይሎች ጋር ትስስር ያለው ነው” ይላሉ፡፡

Magoulickበበኩላቸው በተለያዩ ምሁራን የተሰጡ የሚት ብያኔዎችን በማሰባሰብ የተወሰኑ ጽንሰ ሀሳባዊ መዋቅር(conceptual framework) ለማበጀትሞክረዋል፡፡ በዚሁ መሰረት ሚት ስለ ዓለምና ሌሎች ባህላዊ ነገሮች አጀማመር የሚገልጽ ሁለንተናዊ ትርክት መሆኑን ገልጸዋል፡፡ ሚት ከመለኮታዊ ከበራዎች ጋር የተገናኘ ሃይማኖታዊ ባህርይ ያለው ትርክት በመሆኑ ከሃይማኖታዊ ጉዳዮች ጋር ይተሣሰራል፡፡ የሚለውን ነጥብ ካነሱ በኋላ ከዚህ የተነሣ ሚት እውነት ነው ተብሎ ይታመናል ብለዋል፡፡ እንደዚህም ሲባል በአንድ ባህል ውስጥ ሃይማኖታዊና ዓለማዊ (ባህሊዊ) ሚቶች አብረው እንደሚኖሩ መዘንጋት እንደሌለበትምያስገነዝባሉ፡፡

በተጨማሪም Magoulickከብዝሃ-ግብርእይታአንፃርየተሰጡየሚትማብራሪያዎችንበማቀናበርሚትየባህላዊእሴቶችወይምየማህበራዊስርዓቶችነፀብራቅወይምገላጭመሆኑንካወሱበኋላከመዋቅራዊእይታ(structural perspective) አንፃርሚትየአንድንነገርባህርይናአመጣጥእንዲሁምየአንድንሀሳብአደረጃጀትየሚወክልነውይላሉ፡፡በመሆኑምMagoulickሚትየባህላዊአላባውያንዓለማዊናሃይማኖታዊባህርይገላጭ፤የባህላዊ እሴቶችናማህበራዊሥርዓቶችነፀብራቅ፤ተፈጥሮንየሚረዱበትናሀሳብየሚደራጅበት፤ገጸባህርያትንየሚያጎላናየህይወትአቅጣጫንየሚነድፍትርክትመሆኑንያሰምሩበታል፡፡

በአጠቃላይበሚትባህርያትናተግባራትላይበመመስረትከዚህበላይየተጠቀሱትዓይነትበርካታየሚ ትብያኔዎችቢኖሩምሁሉንምየሚያስማማይህነው፡፡ብሎአንዱንብያኔእንደሞዴልማስቀመጥይከ ብዳል፡፡ምክንያቱምየዓለምህዝብባህል፣ወግናእምነትየተለያየበመሆኑለአንዱባህልየሚሠራውለሌ ላውላይሰራይችላል፡፡ስለዚህይህንንከግንዛቤበማስገባትናእስካሁንየተዳሰሱትንንድፈሐሳቦችናአስ ተሳሰቦችመነሻበማድረግ በመጠኑ ጠቅለል በማድረግሚትበተፈጥሮአዊናባህላዊ፣ቁስአካሎችናሁኔታዎችላይከሚመሠረትየሰውምናብየሚመ ነጭሆኖከተለመዱትእጅግየላቁክስተቶችናገፀባሕርያትየሚታዩበት፤ያንድንነገርአመሰራረትናአ ፈጣጠርወይምማንነትናምንነትወይምአንድነገርለምን እንደሚደረግናእንደማይደረግየሚገልፅናለገለጻውየግድማረጋገጫማቅረብየማይጠበቅበት፤እንዲ ሁምህብረተሰብንበመቅረፅናጥበብንበማስተላለፍረገድየጎላሚናያለው፤የባህሊዊእሴቶችመሠረት የሆነሃይማኖታዊወይምዓለማዊትርክትነውብሎመበየንይቻላል፡፡

## 2.1.2 የሚት አፈጣጠር

በሚቶሎጂ ምርምር ስማቸው በመጀመሪያው ረድፍ ከሚጠሩት ምሁራን ውስጥ አንዱ የሆነው Joseph Campbell (1949፤3) "በምንኖርባት ዓለም ላይ በማንኛውም ጊዜና በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ የሰው ልጅ ሚት እየበለጸገና እየተስፋፋ የመጣው ከሰው ልጅ የአካልና የአእምሮ እንቅስቃሴዎች ነው፡፡"በማለት ስለ ሚት አፈጣጠር ጽፏል፡፡ በዚህ አባባል መሠረት ሚት ከሰው አእምሮ ጋር የተቆራኘ ስለሆነ ሰው ከተፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ ሚት ነበረ ማለት ይቻላል፡፡ አካላዊና አእምሯዊ እንቅስቃሴዎች ለሚት መፈጠር ምክንያት ከሆኑ ደግሞ ከሰው አካላዊና አእምሮአዊ እንቅስቃሴዎች ጋር ቁርኝት ያላቸው ባህላዊና ተፈጥሮአዊ ነገሮች ለሚት መፈጠር መሠረቶች ይሆናሉ፡፡ እነዚህ ባህሊዊና ተፈጥሮአዊ ነገሮች የሚባሉት ከበራዎች፣ ስርዓተ-ሽግግሮች፣ ቁሳቁሶች፣ ተፈጥሮአዊ ክስተቶችና ቁስአካሎች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ እነዚህ ባህላዊና ተፈጥሯዊ ነገሮች መሰረት ሆነው አካላዊና አእምሮአዊ እንቅስቃሴዎች ለሚት መፈጠር ምክንያት ሲሆኑ፤ አካላዊና አእምሮአዊ እንቅስቃሴዎችን በምናብ መሰየም ይቻላል፡፡ ለሚቶች መቀረፅ የሰው ልጅ ምናብ ወሳኝ ሚና እንዳለው (Giambattista Vico፣1948) መጠቆሙ ይታወቃል፡፡

በ18ኛው ክፍለ ዘመን የተነሳው Giambattista Vico ምናብ ለሚቶች መቀረጽ አስፈላጊ መሆኑን የገለፀውና የሚቶሎጂ ቀኖና የሚለውንና ሌሎችንም ከሚት ጋር የተያያዙ ጽንሰ ሀሳቦችን ያብራራው በ1725 ባሳተመው "Scienza Nuova" በሚለው መጽሃፉ ሲሆን ለዚህ

ጥናት ምንጭ የሆነው The New Science of Giambattista Vico (የጂያምባቲስታ ቪኮ አዲስ ሳይንስ) የሚል ርዕስ ተሰጥቶት ከVico መጽሃፍ 3ኛ ዕትም ወደእንግሊዝኛ ተተርጉሞ በ1948 የታተመው ነው፡፡

ሌላው ስለ ሚት አፈጣጠር የሚገልጸው ከህክምና ልምድ የመነጨው የሥነ-አእምሮ ንድፈ ሐሳብነው፡፡ ይህ አስተሳሰብ በዋናነት ከሥነልቦና ጋር የሚጣመር ቢሆንም ከባዮሎጂና ህብረተሰብ ሳይንስ ጋርም ስለሚነካካ የማህበራዊ ፋንክሽናሊዝም አቀራረብ በመባል ይታወቃል፡፡ በዚህ ንድፈ ሐሳብ በግምባር ቀደምትነት የሚጠቀሱት Sigmund Freud እና Carl Jung ናቸው፡፡ ሁለቱም ሚታዊ ተምሳሌቶች በኃይማኖት ውስጥ የሚገኙ፤ በህልም ውስጥ የሚገለፁ፤ የምናብ ውጤት የሆኑ፣ ከአእምሮ (psyche) ጥልቅ ጉድጓዶች የሚገኙ ናቸው ብለው ያምናሉ፡፡

Abraham (1913፣5)የፍሮይድን ቲዎሪ የበለጠ በማብራራት በሚሰጧቸው አስተያየቶች ምኞት በሰው ንቃት አልባ ህሊና ስር ታምቆ የሚገኝ መሆኑን ያብራራሉ፡፡ በተጨማሪም የሚት ፅንሰ ሃሳብ በከፍተኛ ደረጃ ከግለሰብ ባዮሎጂ (ስነ ሕይወት) የሚመነጭ መሆኑን ይናገራሉ፡፡ ያምሆኖ ሚትን በአንድ ጭብጥ ብቻ መግለጽና በድብቅ ንቃተ ህሊና መበየኑን በእጅጉ ይተቻሉ፡፡

በ20ኛው ክፍለ ዘመን ከተከሰቱት ንድፈ ሐሳቦች ውስጥ አንዱ የሚት-ከበራ አስተሳሰብ (myth-ritual thought) በመባል የሚታወቀው ቲዎሪ መሆኑ በCatherine (1997፣5) ተጠቅሶ ይገኛል፡፡ ንድፈ ሐሳቡ የከበራንቀዳማይነት  የሚያቀነቅን ሆኖ ክርክሩም ማንኛውም ሚት ከከበራ (ritual) ወይም ከስርዓተ-ሽግግር (rite) የሚመነጭና ለዚያው ስነ-ስርዓት ትግበራ እንደመመሪያ የሚያገለግል ነው የሚል ነው፡፡ Levi-Strauss (1963፣232) ግን ሁለም ሚት ከከበራ ጋር አይጣመርም፣  በማለትየሁለቱ ጥንዳዊ ትስስር የግድ እንዳልሆነምይሞግታሉ፡፡ በተግባር እንደሚታየው የተወሰኑሚቶችከከበራወይምከሥርዓት-ሽግግርየሚፈጠሩቢሆንም፣ሁለምሚቶችከዚህውጭሊሆኑአይችሉምብሎመደምደሚያላይመድረስ ግን የማያስኬድ ስለሆነ የላቪስትራውስሀሳብ ተቀባይነትአለው፡፡

ከላይ ከቀረበው ሃሳብ መረዳት እንደሚቻለው ለሚት መፈጠር መሰረቶቹ ከሰው ልጅ የአካልና የአእምሮ እንቅስቃሴዎች ጋር ቁርኝት ያላቸው ባህላዊና ተፈጥሯዊ ነገሮች ሲሆኑ፤ የሰው ልጅ ምናብ ለሚት መቀረጽ ከፍተኛ ሚና እንዳለው እንዲሁም ሚት ከግለሰብ ስነ ህይወትና ከከበራወይምከሥርዓት-ሽግግር ሊመነጭ (ሊፈጠር) እንደሚችል ነው፡፡

## 2.1.3ሚትን የድሮ ነገር ብቻ አድርጎ መደምደም የማይቻል ስለመሆኑ

Leonardo እና Michael (2003) ሚት ድሮም የነበረ አሁንም የሚኖር ቋሚ(Static) ትረካ ነው ብሎ መከራከሩን ሁለቱም ምሁራን ጠቅሰው የእርሱ ክርክር መሻሻል እንደሚገባው ይጠቁማሉ፡፡ በእነሱ አባባል ሚቶች ባህል እንደ ቀኖና የሚወስዳቸው ከመሆናቸውም በላይ ተሰጥኦ ባላቸው ታሪክ ተናጋሪዎች የሚቀናበሩ፤ በህዝብ የሚታመኑና ለሕዝብ ትርጉም የሚሰጡ ገዥ ቁምነገሮች ናቸው፡፡ እነዚህ ሚታዊ ታሪኮች በሕዝቡ ፍላጎት የሚታደሱና የሚለመዱ ናቸው (2003፣ Retrieved on November 4, 2015, from www, Cuymaca) ፡፡ ከዚህ መረዳት የሚቻለው ሚት እንደፈለገ በራሱ ጊዜ በማንኛውም ታሪክ ውስጥ የሚወሸቅ ትርክት ሳይሆን በተጠቃሚዎቹ እየተተገበረና ለውጥ እያሳየም የሚሄድ የትውፊት ምድብ ነው፡፡

William Bascom(1965፣1) ሚትን ማሕበረሰቦች በሩቅ ጊዜ የተፈጸመ እውነት አድርገው የሚወስዱት ዝርው ትረካ ነው፡፡ በማለት ስላለፈው ጉዳይ ብቻ የሚያወሳ ትርክት አድርገውይወስዱታል፡፡ ይሁን እንጂ Lang (1897፣vIII)“ባለንበት ዘመን በጣም የታወቁት የአእምሮ ልማዶች የትወራና የትንተና ልማዶች ናቸው፡፡ ታሪካዊ መደምደሚያ የማይሰጣቸው የምርምር፣ የሙከራና የትንተና ሂደቶችና መንፈሳዊ የሆኑ ነገሮች በሙሉ ካለፈው ጋር እንዲዛመዱ ያደርጋል” በማለት የባስኮምን ሀሳብ ይቃወማሉ፡፡ ሚት የድሮ ጉዳይ ብቻ መሆን አለመሆኑን ለማረጋገጥ ስንነሳ እነዚያ ድሮ የተፈጠሩ ሚቶች በዛሬው በ21ኛው ምእተ ዓመት ዋጋ ያላቸውና አገልግሎት በመስጠት ላይ የሚገኙ ሆነው እናገኛቸዋለን፡፡ በዚህ ብቻም ሳያበቃ ሚት ዛሬም ይፈጠራል፤ በሚቀጥለው ትውልድ አማካይነትም መፈጠሩ ይቀጥላል፡፡ ስለዚህ ሚትን የድሮ ነገር ብቻ አድርጎ መደምደም ተገቢ አይሆንም፡፡

### 2.1.4የሚት ምደባ

ሚትን በሚመለከት የተለያዩ ንድፈ ሐሳቦችና አስተሳሰቦች በመኖራቸው እነሱን መሰረት ባደረገ መልኩ ሚት በተለያዩ ፈርጆች ተከፋፍሎ ተጠንቷል፡፡ የክፍፍሉ ሁኔታ እንደ የትምህርት መስኩ ባህርይና እንደ አጥኚው ንድፈ -ሀሳባዊ አጠቃቀም ልዩነት የሚያሳይ በመሆኑ በርካታ የሚቶልጂ ፈርጆች (ክፍሎች) ተመስርተዋል፡፡ አንዱ የአከፋፈል ዘዴ ሚቱ ስለ ምን ወይም ስለ ማን ይተርካል? የሚለውን መሠረት የሚያደርግ ሲሆን በዚህ መሠረት የአፈጣጠር ሚት (Cosmological or nature myth)፣የአመሠራረት ሚት (Foundation myth)፣ ሥነ-ልቡናዊ ሚት (Psychological myth)፣ መንፈሳዊ (ሃይማኖታዊ) ሚት (Spiritual or Religious myth)፣ ፍልስፍናዊ ሚት (Philosophical myth)፣ ርዕዮተ ዓለማዊ

ሚት (Ideological myth)፣ የሥነ-አረዳድ ሚት (Cognitive myth) እና የመሳሰሉት ፈርጆች ተፈጥረዋል፡፡ ሌላው የአመዳደብ ዘዴ ሚቱ በየትኛው አከባቢ ላይ ትኩረት ያደርጋል? የሚለውን ገዥ ሀሳብ መሠረት ያደረገ ሲሆን ሚትን በመልከአምድር የሚከፋፍል ነው፡፡ ለምሳሌ የግብፅ ሚቶሎጂ፣ የግሪክ-ሮማን ሚቶሎጂ፣ የኖርስ ሚቶሎጂና የመሳሰሉትን መጥቀስ ይችላል፡፡እንዴት? ተረከው፣ለምን? ተረከው (ዓላማውምንድ ነው?) የሚሉትንጥያቄዎችመነሻአድርጎለሚቶሎጂክፍፍል የሚሰጥአቀራረብምአለ፡፡እንዴት? ተረከውየሚለውአውድንእንዳይዘነጋስለሚያደርግናለምን? ተረከው (ዓላማውምንድነው?) የሚለውተግባርእንዲቃኝ ይረዳል፡፡

## 2.1.5የሚት አይነተኛ ጠባያት

Magoulickየበርካታ አጥኚዎችን ሥራዎች መርምረው ባሰፈሩት ጽሁፍ የሚከተሉትን የሚት ዓይነተኛ ጠባዮች (characteristics of myth) በዝርዝር አስቀምጠዋል( Retrieved on December 13, 2015, from Hercules.gcsu.edu/mmagouli/defmyth.htm) ፡፡ እነዚህ የሚት ባህሪያት ፍጹማዊ ወይም ሁሉን አቀፍ አለመሆናቸውንምMagoulickያምናሉ፡፡ የሚት ጠባዮች ተብለውብ Magoulick የተዘረዘሩት፡-

ሚት ስለዚህ ዓለምና አመጣጥ የሚያብራራ እውነተኛ ነው ተብሎ ይታመንበት የነበረ ወይም አሁንም የሚታመንበት ትረካ ነው፣ ገጸ ባሕርያቱ ሰዎች ሳይሆኑ ፣ እንደ አማልክትያሉ ልእለ ሰብ ናቸው፣ መቼቱ የዱሮና ከዚህኛው ዓለም የተለየ ነው፣ ምናልባትም ዓለም ሲፈጠር፣ ሴራው የዚህኛውን ዓለም ከወዲኛው ሊያስተሳስር የሚችል ነው፣ተፈጥሯዊ ሕግን የሚዛቡ ወይም የሚጥሱ ሁነቶችን ይገልጻል፣ የዓለሙ፣ ነገረ ህላዌ (Cosmogonic) ወይም ሀሳባዊ (metaphysical) ማብራሪያ ነው፣ ዶግማ ነው፡፡ ግለሰቦች፣ ቤተሰቦች፣ ማሕበረሰቦች እንዴት መኖር እንዳለባቸው፣ የሚታሰቡ መሰረታዊ ሀሳቦችንና እሴቶችን የሚያስተላልፍ የማሕበራዊ ድርጊት መመሪያ ነው፣ ያማይታወቅ ምስጢር መኖሩን ያስገነዝባል (ምስጢሩ ሀይማኖታዊ ነገር አለው)፣ በሚገባ ማገናኘት የሚገቡንን ጥንዳዊ ተቃርኖዎችመሰረታዊ መዋቅሮች አንጸባራቂና ፈጣሪ ነው ( ብርሃንና ጨለማ፣ ሰናይና እኩይ፣ ህልውና ባዶ፣ ጥሬና ብስል ወዘተ.)፣ የነገረ ህላዌን እውቀት ትእምርታዊ በሆነ መንገድ ይተርካል፡፡ ሚት፣ ለምን ወደ ዓለም እንደመጣን፣ ምን እንደሆን፣ ዓላማችን ምን እንደሆነ ወዘተ. የሚነሱ መሰረታዊ ጥያቄዎችን የሚመልስ ትርክት ነው፡፡ እና የሚት ትረካ ገጽታ

አንዳንዴ ከመሰረታዊ ከበራዎች ላይ ይመሰረታል (ማሕበረሰቦች የሚከናውኗቸው መሰረታዊ ሀይማኖታዊ ተግባራት አንዳንዴ ከእምነት ሥርዓቶች ጋር አንዳንዴ ከከበራው ምንጭ ጋር ይያያዘላሉ::የሚሉ ናቸው፡፡

ከዚህ በላይ በMagoulick የተጠቀሱት 11 የሚት ባህርያት የሚትን ምንነት በተወሰነ ደረጃ የሚገልፁ እንጂ የሚት ባህርያት አጠቃላይ መመዘኛለመባል የሚበቁ አይደሉም፡፡ እንዲሁም Doyle እና Flaten (2004) በድረ ገፅ ላይ ባቀረቡት ፅሑፍ

> ሚት በማንኛውም ህብረተሰብ ውስጥ እንደሚኖር በማመን ሚት የሰው ባህል የሚገነባበት መሰረት መሆኑኑ ካተቱ በኋላ በምእራቡ ባህል መሠረት ምሁራን ከሚት ጋር የሚያዛምዷቸው ትርክታዊ ዘውጎች ፋቡላ (fable)፣አደረባሬ ተረት (fairy tale)፣ ሀገረሰባዊ ተረት (folktales)፣ ሳጋ (sagas)፣ የጀግና መወድሳዊ ግጥም (epics)፣ አፈታሪክ (legends) ወዘተ. መሆናቸውን ይዘረዝራሉ፡፡ ተመሳሳይነታቸውንና ልዩነታቸውን ለማሳየት ሲሞክሩ፤ ለምሳሌ "ፋቡላ እንደ ሚት ተፈጥሮአዊ ቁሶችን ወይም እንስሳትን እንደ ገፀ ባህርያት ሲጠቀም ሰውኛ ባህርይ እንደሚያላብስ፤ ነገር ግን ፋቡላ ግብረ ገባዊ (ሞራላዊ) መልእክት እንደሚያስተላልፍ፤በዚህ ምክንያት አንድአንዴ ትምህርት ሰጪ (አስተማሪ) ተረት ተብሎ እንደሚጠራ ፤ ሚት በተቃራኒው ቀጥተኛ የዚህ ዓይነት ትምህርታዊ ጉዳይ (didactic aspect) የሌለው መሆኑን ያብራራሉ፡፡ ፋቡላና ሚት በትርክታዊ ገጽታቸውም ልዩነት አላቸው፡፡ እነዚሁ ጸሃፊዎች የመናፍስት ተረትንና ሚትን በማነፃፀር የመናፍስት ተረት ልክ እንደ ሚት ከመደበኛው ወጣ ያሉ ያልተለመዱ ፍጡራንና ክስተቶችን እንደ ገፀባህርያት የሚጠቀም መሆኑን ያወሳሉ፡፡ ነገር ግን እንደ ፋቡላ ግልፅ ያልሆነ መቼት የሚጠቀምና አንድ ጊዜ እንዲህ ሆነ የሚል ዓይነት አቀራረብ ስለሚከተል እዚህ ቦታ ላይ በተዘዋዋሪም ቢሆን ከሚት ጋር ልዩነት እንደሚፈጥር ይጠቁማሉ፡፡

ሀገረሰባዊ ተረትን በሚመለከት Doyle እና Flaten(2004) ሲያብራሩ "ስለትርጉሙ በምሁራን መካከል ስምምነት የሌለውን ያህል የሀገረሰባዊ ተረትና ሚት ግንኙነትን በሚመለከትም ወጥ ስምምነት አለመኖሩን ይጠቅሳሉ፡፡" ምሳሌ ሲያቀርቡም "የአሜሪካው ፎክሎረኛ Tomsen ሚትን የሀገረሰባዊ ተረት አንዱ አካል ሲያደርገው እንግሊዛዊው kirikደግሞ ሁለቱ የተለያዩ ሆነው የሚደራረቡ ናቸው እንደሚል ይጠቁማል፡፡ ተረት በአብዛኛው በሰዎች ወይም በእንስሳት ባህርያት ላይ ተመስርቶ ደግነትን ወይም ክፋትን

ለማሳየት የሚሞክር ነው፡፡ ሚት ላይ ሲሆን ግን የዚህ ዓይነት ባህርይ ጎልቶ አይታይም፡፡ እንዲሁም አገረሰባዊ ተረት እንደ ሚት የምር ተደርጎ አይወሰድም ወይም የሚትን ያህል ኃይል የለውም ወይም የሚትን ያህል አይታመንም፡፡ የጀግና መወደወሳዊ ግጥም (Epic) ደግሞ ግጥማዊ የጀግና ገድል ትረካ ነው፡፡የጀግንነት ግጥም በአብዛኛው በግጥም የሚቀናበር ነው፡፡ ከሚት ጋር ያለው ግንኙነት ደግሞ የእናትና ልጅ ዓይነት ግንኙነት ነው፡፡ ይህ ማለት የጀግንነት ግጥም በሚታዊ ትርክቶች ላይ ሊመሠረት ይችለል ማለት ነው፡፡ ስለዚህ ልዩነታቸው በግልፅ የሚታይ ነው ማለት ነው፡፡ አፈታሪክ ከሚት ጋር ሲነፃፀር ልዩነታቸውን ማመላከት ይቻላል፡፡ አፈታሪክ ታሪካዊ መሰረት ያለው ባህላዊ ትረካ ተደርጎ ይታሰባል፡፡ ከዚህም ሌላ አፈታሪክ ጀግኖች (ተዋንያን) የሚሰሩትን ተራው ሰው ሊሰራው ይችላል፡፡ የሚት ተዋንያን ሥራ ሲሆን ግን በአብዛኛው ለተራው ሰው የሚቻል አይደለም፤ ክስተቱ የሚደገምበትም አጋጣሚ በቀላሉ አይፈጠርም"፡፡ በማለት ሚት ከሌሎች ትርክቶች የሚለይበትን ባህርያት ገልጸዋል፡፡ እንዲሁም ሙሉጌታ ነጋሳ (2014፣120) የሀገረሰባዊ ተረክ ዘሮች፣ሀገረሰባዊ ተረት (folktale)፣ ሚት (myth) እና አፈታሪክ (legend) በሚሉት ዋና ዋና ምድቦች እንደሚከፈል መግለጻቸው ሚትና አፈታሪክ የተለያዩ መሆናቸውን ያመለክታል፡፡

ሚትን ከሌሎች ትርክቶች ለመለየት የሚት ተመራማሪዎች ብዙ ቢሠሩም መመዘኛ ነጥቦችን በአግባቡ አላስቀመጡም፡፡ ሙከራ ካደረጉት ውስጥ በፍጥረታት ሚቶች ውስጥ ያለውን የአስተሳሰብ ተጠየቅ "The Logics of Myth" ያጠኑት ስዊዲናዊ Stefnn Stenudd የሚትን ልዩባህርያት ይገልጻሉ ያሏቸውን ስድስት ነጥቦች አዳብረው ነበር፡፡ እነዚህ ስድስትነጥቦችተረክ (story)፣ ያለፈ (past)፣ ጠቀሜታ ያለው (significance)፣ ልበወለድያልሆነ (non fictional)፣መሆንአለመሆኑን (እውነተኛነቱን)ማረጋገጥየማይቻል(unlikliness) እና የተረኩ ፈጣሪ (ባለቤት) የማይታወቅ(noauthor) የሚሉናቸው(*www.creationmyths.org/mythlogics-1.htm*)፡፡Stenuddእነዚህንየመመዘኛነጥቦችየማያሟላሚትአይባልምየሚልአቋምቢኖረውምመ መዘኛዎቹንበአብዛኛዎቹጉዳዮችላይመጠቀምይቻላል ለማለትእንጂከመመዘኛዎቹጥቂቶቹግልጽነትእንደሚያንሳቸውአልደበቀም፡፡በመሆኑምየ Stenuddንመመዘኛዎችእንዳለ መጠቀምባይቻልምእንደ መነሻ ለመገልገል ጠቃሚ መሆኑ የሚያጠያይቅ አይሆንም፡፡

Magoulickየብዙ ተመራማሪዎችን ሥራዎች መርምረው የሚት ዓይነተኛ ጠባዮች በማለት 11 የሚት ጠባያትን ባሰፈሩት ጽሁፍ ውስጥም ሆነ Doyle እና Flaten ብዙ ምሁራን ከሚት

ጋር የሚያዛምዱቸው ትርክታዊ ዘውጎች መኖራቸውን በመጥቀስ በሚትና በዘውጎቹ መካከል ያለውን ተመሳስሎና ልዩነት ለማሳየት በሞከሩት ገለጻቸው ውስጥ እንዲሁም Stefnn Stenudd የሚትን ልዩ ባህርያት ይገልጻሉ በማለት ባዳበሯቸው ስድስት ነጥቦች ውስጥ አገላለጻቸው ቢለያይም ፍሬ ነገራቸው የሚገናኝ ሀሳቦች አሉ፡፡ በሶስቱም ጽሑፎች ውስጥ ከታዩት የጋር ጉዳዮች በመነሳት ሚት እውነታነት ያለው፣ ሐይማኖታዊነት የሚንጸባረቅበት፣ ገጸባህርያቱ በሌሎች ዘውጎች ላይ ከሚታዩት ገጸባህርያት የሚለዩና ልዕለሰባዊነት የሚታይባቸው፣ የረጅም እድሜ ባለቤት የሆነ እና የማይታወቅ ነገር (ለመግለጥ አስቸጋሪ የሆነ ክስተት) መኖሩን የማሳወቅ ጠባያት የሚታዩበት ነው፡ በመሆኑም እነዚህን ከአራቱ ምሁርን የተገኙትን የጋራ ጠባያት እንደመነሻ መውሰዱ መልካም ይሆናል፡፡

## 2.1.6የሚት ተግባራት

የአንድንሕዝብሚትበማጥናትናጥንታዊታሪኮችንበማዳበር (በማጠናከር) የራስንማንነትናአመጣጥማወቅ፣ ሃይማኖታዊ ጉዳዮችን መመርመር፣ በሰው ህይወት ውስጥ አስፈላጊ የሆኑ ነገሮችን መግለፅእንደሚቻል የዘርፉ ምሁራን ይገልጻሉ፡፡Tylor (1871፣2-3) ከሃይማኖቶችታዋቂ (ትልቁ) ዶክትሪንየሆነውንየከሞትበኋላሕይወትአስተምህሮበመተንተንከዚህጋርተያያዥነትያላቸውንሚቶችናትረካዎችንበማቅረብከቀድሞዎቹአመለካከትአንፃርትረካዎቹምክንያታዊመሆናቸውንበማረጋገጥጽፏዋል፡፡ይህምሚትበሃይማኖትውስጥየሚጫወተውንሚናያሳያል፡፡በተጨማሪም የመጽሐፍቅዱስታሪኮችበትንሹእየተቆነጠሩቅንየሚባሉትታሪኮችብቻተወሰዱናተፃፉእንጂምንጫቸው (መሰረታቸው) ሚትመሆኑንያስረዳሉ፡፡እንዲሁም Vaughan (1919) የሃይማኖትንፅፅራዊጥናትበሚለውመጽሐፉውስጥሚትበሁሉምጉዳዮች፣ሃይማኖትንጨምሮበሁሉምየትምህርትመስኮችውስጥተጠላልፎየሚገኝመሆኑንጠቅሰውሚትለእውነታመሰረትሆኖእንደሚያገለግልእምነታቸውንይገልፃሉ፡፡በተጨማሪም Spence (1921፣11) የሚቶሎጂን ተግባር ሲገልጹ ሚት ከመጀመሪያዎቹ የሰው ዘር ሃይማኖታዊና ሳይንሳዊ ልምዶች ጋር ስለተያያዘ ተረቶችን ለመመራመር የሚያግዝ መሆኑንይገልጻሉ፡፡

Lynch (2004፣Vi) የአፍሪካሚቶሎጂከ "ኤ" እስከ "ዜድ" በሚለውመጽሐፋቸውውስጥስለሚቶሎጂተግባርበአጭሩሲያብራሩ፣ሰዎችሚቶሎጂንናመንፈሳዊ ስነስርዓትንማህበረሰባዊየማንነትስሜትንለመፍጠርናበዓለምላይየራሳቸውንቦታለማወቅ

(ለመረዳት)

ይጠቀሙበታል፡፡እነዚህመሳሪያዎችማለትምሚቶሎጂናመንፈሳዊስነስርዓቶችባህላዊትውፊቶች ንለማቆየትናበሕዝቦችሕይወትውስጥበጣምአስፈላጊየሆኑነገሮችንለመግለፅያገለግላሉ፡፡ሊንች አያይዘው ሚቶችን የምናነብበትን ምክንያት ሲገልጹ“ሚትን ስናጠና ሚቱ የተገኘበትን ባህል ለማወቅ ብቻ ሳይሆን በሚት ሰሪዎች አእምሮና ልብ ውስጥ ያለውን ቁም ነገር (ጥበብ) ለማግኘትጭምር መሆኑን ያስረዳሉ፡፡ እንዲሁም የአፍሪካ ሕዝቦች ሚቶች ኑሮና ብልሃታቸውን (የሕይወት መንገዳቸውን) እና አመለካከታቸውን በጨረፍታ ያሳዩናል በማለትይጠቁማሉ፡፡

እንዲሁም Flaten(2004)በመጣጥፋቸው(article) የሚቶሎጂ ተግባራትን ሲዘረዝሩ ሚት ተፈጥሮአዊም ይሁን ባህላዊ እውነታዎችን ለማብራራት (ለመተርጎም) ይረዳል፣ በባህላዊ የትምህርት ስርዓት ውስጥም ሚት በጣም አስፈላጊ ሚና አለው በማለት ይጠቁማል፡፡ (Flaten፣2004፣Retrieved on June 15, 2015, from http://www)
ማጉሊክ ደግሞ“ሚት ተፅዕኖ የሚያሳድር ታሪክ ሆኖ ስለ ሰውና ዓለም አፈጣጠር የሚናገር ነው ይላሉ”፡፡(2015) በተጨማሪም በተለያዩ ምሁራን የተሰጡትን ብያኔዎችንበመጭመቅ ሚቶችያለፈየሩቅዘመንወይምየቅድመታሪክጊዜተምሳሌታዊተረቶችሆነውየአፈጣጠርናየዓለምተ ፈጥሮንየሚመለከቱምናልባትምከእምነትስርዓቶችወይምከመንፈሳዊስነስርዓቶችጋርየሚገናኙና ማህበራዊድርጊቶችንናእሴቶችንለመምራትየሚያገለግሉናቸውሲሉ ይገልጻሉ፡፡
ካምቤል (1949፡3) በበኩላቸው “ሚትበሰውልጅባህላዊመገለጫዎችውስጥየሚቀዳየሁለንተናየማያልቁጉልበቶችምስጥራዊአሸንዳ ነውቢባልአይበዛበትም” በማለትየሚትንምጥቀትለማሳየትሞክረዋል፡፡ካምቤልሀሳባቸውን በማስፋትሚትህብረተሰብንበመቅረጽረገድምንያህልመሠረታዊእንደሆነሲገልጹ“ሃይማኖቶች፣ፍ ልስፍናዎች፣ኪነጥበባት፣ማህበራዊቅርጾች፣ሳይንሳዊግኝቶችናቴክኖሎጂዎችከሚትምትሃታዊቀለ በትውስጥየሚፈልቁበመሆናቸው በነሱ ውስጥ የሚታየው ተግባር በብዙ መልኩ ከሚት ጋር ይገናኛል፡፡” ሲሉ ይገልጻሉ፡፡ ይህም ሚትየሃይማኖቶች፣የፍልስፍናዎች፣የኪነጥበባትወዘተ.መሠረትመሆኑንያሳያል፡፡

### 2.1.7 የሚት ተረክ አላባውያን

ሁሉም ህዝብ ባህሉን እና ማንነቱን የሚገልፅበት ፣ልዕለ ተፈጥሯዊ ሁነቶችን የሚፈጥርበትና የሚያትትበት፣ ርእዩን የሚቀምርበት የራሱ የሆነ ሚት አለው፡፡የሰው ልጅ የዝርያውን

እምነታዊ፣ ፍልስፍናዊ፣ እና ልቦናዊ ሁኔታዎችን ቀርፆ የሚያኖርበት ፣በየዘመኑ የታዩ ፈርጀ ብዙ ሰዋዊ ለውጦችን መዝግቦ የሚያቆይበት ሰነዱ ነው፤እነዚህ እምነታዊና ፍልስፍናዊ ጉዳዮች የሚንጓዙት በተረኩ የስበት ማዕከል ፣ በተጋዳሊው ሰረገላነት ሲሆን ተጋዳሊው በሚፈፅማቸው ድርጊቶች ፣ በሚገባባቸው ሁነቶች እና ከተፈጥሮና ከማህበሩ ጋር በሚፈጥራቸው መስተጋብሮች ነው፡፡የሚት ተረክ አላባውያንን ለአጠናን ያመች ዘንድ ለይቶ መጥራቱ አስፈላጊ ሆነ እነጂ በሚት ውስጥ ወገን ለይተው ለየብቻ የሚገኙ አለመሆናቸውን ልብ ማለት ይገባል፡፡ እንዲሁም አንዱ ሲጠራ ሌላውም አብሮ ብቅ በሚልበት ሁኔታ ተሳስረው ነው ያሉት፡፡ የሚት አላባውያን ከሚባሉት በአጠቃላይ ሚትና በሀዲስ ሚቶሎጂ ጠባያት ውሰጥጎልተው ከሚታዩ የሚት ፍሬ ነገሮች ውስጥየተወሰኑትን ቴዎድሮስ በ(2001) “በይነ-ዲሲፒሊናዊ የስነ ጽሑፍ ንባብ” በሚል ርዕስ ካሳተሙት መጽሐፍ ውስጥበመውሰድ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

> **ተጋዳሊ/ አርበኛ/** በሚት ውስጥ ከፍተኛውን ስፍራ ከሚይዙት ነገሮች አንዱ ተጋዳሊ ወይም አርበኛ ነው፡፡ሚታዊ ተጋዳሊ ከዘመናዊ ኪነጥበብ ጋር ባላቸው ግንኙነት ላይ ካሰፈራቸው የተጋዳሊ መገለጫ ባህርያት ውሰጥ ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡ “ተጋዳሊ ከነባሩ አቋመ ማኅበረሰብ ያፈነግጣል፣ አርበኞች ወይም ተጋዳዮች ማኅበረሰቡ በተጨነቀበት ውስጥ የሚደርሱ አካላት ናቸው፣በማኅበረሰባቸው ወይም በሚታገሉበት ዓለምበውስጥ ትልቅ ተጋድሎ ይጠብቃቸዋል፣ እነርሱም አንዳች የተለየ እርዳታ ወይም ሃይል በማግኘት ከመከራው የማምለጥ ሀይል ያላቸው ናቸው፣ በተጋድሎም አሸናፊ ይሆናሉ፣ የማሸነፍ ሂደቱ መመረጥ፣ ወደ ሆነ ቅጽር መዝለቅን እና በረከትን ወይም ድልን ይዞ መመለስንም ያካትታል፡፡(ገጽ፣44)

**መጠራት**ሌላውከጀግናው ወይም ከተጋዳዩ ጋር ተያይዞ የሚመጣውና የማይቀረው በሚት አላባውያን ውስጥ የመነሳው መመረጥ ወይም መለየት ነው፡፡ ይኸውም ተጠሪውን አካል ከሚኖርበት እውናዊ ዓለም ወይም ከተለመደው ሕይወት ውስጥ ወደ ተለየ ተጋድሎና ዓላማ ወይም ማኅበረሰቡ አልተገነዘበውም ተብሎ ወደ ታሰበው ረቂቅ ወይም ስውር ነገር የሚጠራበት ሂደት ነው፡፡ ጥሪውም የማኅበረሰቡን ወግ ባሕል እምነትና ሥርዓት ማኅበር ተከትሎ በተለያየ መንገድ ሊከናወን ይችላል፡፡የገድል ጥሪን አስመልክቶ እንደሚከተለው ይገልፃሉ፡፡

“የገድል ጥሪ ለረጅሙ የሚት ጉዞ በመነሻነት ማገልገል በሁሉም ሚቶች ውስጥ የሚታይ የጋራ ገፅታ ይሁን እንጂ ጥሪዎቹ የሚቀርቡባቸው ሁኔታዎች ፣ ጥሪዎቹ እንደዘመኑና እንደየባህሉ ልዩነት፣ ደግሞም እንደሚቱ ደረጃ እየቅልነትንን ያሳያሉ፡፡ በነብያት፣ በቅዱሳት፣ ባህሉ ባከበራቸው፣የተለየ ክህነት ባላቸው ሰዎች ወይም በመላዕክት፣ በአማልክት አንደበት በሚነገር ቃል ጥሪው በትዕዛዝ መልክ ሊደርስ ይችላል፡፡ ወይም ደገሞ በዕለት ተእለት ኑሮ በሚፈፀሙ ድርጊቶች በሚደርሱ ሁነቶች መሀል የሰርክ በመሆናቸው ተጋዳሊው ልብ በማይላቸው ጉዳዮች ትዕምርትነት ሊከሰት ይችላል፡፡ይህ አይነቱ ሁኔታ ሲከሰት ተጋዳሊው በውል ልብ አይለውም እንበል እንጂ ጉዳዮቹ ተደማምረው በሚፈጥሩት ድባብ ወይም መንፈስ አእምሮውንና ስሜቱን ለጥሪው ዝግጁ የማድረግ አቅም ይኖራቸዋል፡፡ በአጋጣሚ ወይም ባለማስተዋል አልያም በግዴለሽነት በሚፈፀሙ ስህተቶች አማካኝነት ጥሪው ሊደርስ፣ ገድሉ ሊቀሰቀስ የሚችልባቸው አጋጣሚዎች ጥቂት አይደሉም፡፡ ህልምና ራዕይም ተዘውታሪ የጥሪ ማድረሻ፣ ለገድል የመቀስቀሻ መንገዶች ናቸው፡፡ በህልምና በራዕይ ጥሪው በዝርው እንዳለ ሊቀርብ፣ አልያም በሌሎች ነገሮች ተወክሎ በትዕምርትነት ሊመጣ ይችላል፡፡ ጥሪው በየትኛውም መንገድ ይገለጥ፣ በየትኛውም ሁኔታ ውስጥ ይምጣ፣ ከጥሪው ጀርባ ግን ብዙውን ጊዜ የልዕለ ተፈጥሮ ሀይል እጅ አለ፡፡ የተጋዳሊው እጣ ከመነሻው የተቆረጠ ነውና፣ ይህ ሀይል አስቀድሞ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፡፡(ገጽ፣6)

ጉዞ እንዲሁ በሚት ውስጥ ጎልተው ከሚታዩት አላባውያን ውስጥ አንዱ አርበኛው ወይም ተጋዳሊው የሚያደርገው ጉዞ ነው፡፡ በዚህ ጉዞ ውስጥ በየትኛውም ትውፊትና ሃይማኖታዊም ሆነ ባሕላዊ ትርክት ውስጥ እንደሚታወቀው ያለ ብዙ ዓይነት ውጣ ውረድን ወይም ድካምን የሚያሳይ ጉዞ ነው፡፡ቴዎድሮስም ይህን ጉዳይ ሲገልጹት፡-

ጉዞ ለአንድ ከፍ ላለ አላማ የሚደረግ ጉዞ ፣ከዘውትራዊው ገፅታው የተለዩ አያሌ ገፅታዎች ያሉትና በጥቅሉ ግን ለአንድ ዓላማ የሚደረግ ውጫዊ እና ውስጣዊ ጉዞ ነው” በማለት ይገልጻሉ (ገጽ፣፣60)፡፡ ውጫዊ ጉዞ ስጋዊ ወይም መንፈሳዊ ይዘት ሊኖረው የሚችል ሲሆን ተጓገዡ መኖሪያውን ለጊዜው ለቆ ወደ ታለመለት ስፍራ በማምራት ስጋዊ እርካታን ለማግኘትና መንፈሳቸውን ለማንጻትና ለመታደስ ሲሉ የሚፈጽሙት ባህላዊና አምልኮታዊ ክንውን ሲሆን ውስጣዊ ጉዞ አርበኛው

ወይም ተጋዳዩ በራሱ ኀሊና በተለያዩ ሁኔታዎች ውስጥ በተመስጦ በመግባት በብዙ መልኩ የሚያደርገው ምናባዊ ጉዞና የሚደርስበት ሁኔታ ነው፡፡

በውስጣዊ ጉዞ ተጋዳሊው አካሉን ሙሉ ለሙሉ ተቆጣጥሮ ከስጋዊ ፍላጎቶቹ በላይ በመሆን ወደ ውስጡ ርቆ መጓዝ፣ የተቀደሱ ስፍራዎችን መጎብኘት፣ ከፈጣሪው ጋር መገናኘት ይቻለዋል፡፡ በምላሹ በጉዞው የሚያተርፈው ወደ ስጋው ይዞ የሚመለሰው በረከት አለ፡፡ በመንፈስ እንደመታደስ ፣ንፅህናን እንደመቀናጀት፣በዚህም ሐሴት እንደማግኘት ያለ በረከት ወይም ደግሞ ከፈጣሪው ጋር እንደተገናኘ ሰይፍ ሲያርፍበት፣ የድንጋይ ናዳ ሲወርድበት እና ሰማዕትነት ሊቀበል ይችላል፡፡ቴዎድሮስ (ገጽ፣60)

**ቅጽር ዘለቃ**ሌላኛው በሚት ውስጥ የማይቀረውና በተጋድሎው ውስጥ የሚገለጸው የሚት ፍሬ ነገር ቅጽር ዘለቃ (Crossing of the threshold) ነው፡፡

"ቅፅር መዝለቅ ከአንድ ስፍራ ወደ ሌላ ስፍራ በሚደረግ ጉዞ የሚፈጸም ድንበር ማቋረጥ፣ ከነባር ሁናቴ ወደ አዲስ ሁናቴ፣ ከነባር ልማድ ወደ እዲስ ልማድ፣ከዘውትር ዓለም ልዩ ወደ ሆነ አለም የሚደረግ ሽግግርን የሚወክል ሀረግ ነው፡፡"(ገጽ፣20)

በሚት ውስጥ ተጋዳሊው ታላቁን ገድል ለመፈፀም የሚዘልቀው ከሰው ልጆች የመኖሪያ አከባቢ ርቀው ወደሚገኙ፣ ፈፅሞ ወዳልተደረሰባቸው ወይም በወጉ ወዳልታወቁ ጨለማና አስፈሪ ስፍራዎች ነው፡፡ እነዚህ ስፍራዎች ጥብ'ቅና ክልክል ቀጠናዎች ሲሆኑ በየቅፅሮቻቸው የሚቆሙ ዘቦች (threshold guardians) አሏቸው፡፡ ቅፅር ጠባቂ ዘቦቹ እንግዳውን አለም ከመጠበቅና የአለማቱን ሚስጥር ከመሸሸግ ባሻገር ለተጋዳሊው በዓይነትም በመጠንም ልዩ ልዩ የሆኑ ፈተናዎችን ያቀርባሉ፤ ወጥመድ ይዘረጋሉ፤መውደቂያውን ይምሳሉ፡፡ ስለዚህ ጉዞውን ለሚያደርገው ተጋዳሊ ወደዚህ ስፍራ መዝለቁና ከስፍራው የሚፈለገውን በረከት ይዞ መመለሱ በቀላሉ የሚሞከር አይሆንም፡፡ የቅጽር ዘለቃው ሂደት እጅግ ፈታኝ እንደሆነና ተጋዳሊው ከብዙ ተጋድሎ በኋል ለድል እንደሚበቃ ቴዎድሮስ በሚከተለው መልኩ ገልጾታል፡፡

የሚጓዝበት መንገድ በገድልና በተአምር የተሞላ ተጋዳሊ የባህሉን አጥር ጥሶ፣ ወደ ጥብቅ ቀጠናው ዘልቆ የሚወርድበትን መከራ ሁሉ በፀጋ እየተቀበለ ተቀናቃኞቹን ያጠፋል፤ሥፍራውን ነፃ ያወጣል፡፡ ከዚህም የሞት ሽረት ትግል በኋላ ይህ ሰው የወትሮው ሰው አይሆንም፡፡ በአንድ በኩል ተጋዳሊነቱን ያፀናል፤ ለፍጽምና

ይበቃል፡፡በሌላ በኩል፣ መከራውን ከተቀበለበት ስፍራ ለወገኖቹ የሚሆን በረከት-መንፈሳዊ አልያም ቁሳዊ በረከት-ይዞ ይመለሳ (ገጽ፣29)

እንግዲህ ተጋድሎው የቱንም ያህል ፈታኝና ተደጋጋሚ ቢሆንም ተጋዳዩ እስከ መጨረሻ ድረስ ታግሎ በመዝለቅ ለድል ይበቃል፡፡ ድሉ ግን ከሞት ወዲህ ባለ ህይወት ድስታና ስኬት ብቻ የሚገለጽ ሳይሆን ተጋዳሊውን ለህልፈት ዳርጎ ከሞት ወዲያ ማዶ ባለው ህይወት መታሰቢያ ጭምር የሚገለጽ በመሆን እንጂ፡፡

## 2.1.8ሚትና ስነ ፅሑፍ

ከላይ እንደተገለጸው ሚት የማይነካው የዕውቀት ዘርፍ የለም ይሁን እንጂ ከሌሎች በተለየ ከስነ ፅሑፍ ጋር ያለው ቁርኝት እጅግ የጠበቀ ነው፡፡ለዚህምአብነቱ የሚት ተፈጥሯዊ ባህሪ እና መቅረቢያ መንገድ ስነጽሑፍን እንዲጠራ ማድረጉ ነው፡፡ ይህንን የሚትንና የስነ ፅሑፍን ዝምድና ቴዎድሮስእንዲህ ሲሉይገልጹታል፡፡

> ከሚትባህርያት መሃል ስነ ጽሑፋዊነቱ ወይም ኪናዊነቱ (literariness) የሚልቅ ይመስለኛል፡፡ሚት በመሰረቱ በጊዜ እና በስፍራ እሳቤ የማይነገሩ ከሰው ልጅ የሕውስታ አድማስ (sensation)፣ከአስተውሎቱም የረቀቁ እንደ መለኮታዊ ህላዌ ባሉ የቋንቋ ህልውናን በሚገዳደሩ ፀናን ሰማያዊ ክስተቶች (ineffable heavenly phenomena) የተሞላ ተረክ ነው፡፡ ዳሩ ግን የስነ ፅሑፍ ኪን በምናብ ኃይል አማካኝነት የቋንቋን ጉልበት እያበረታና እያፈረጠመ የቋንቋን መንፈስ እያደሰ ፣ እያዘመነ የቋንቋን ስብራት ይጠግናል የቋንቋን ህልውና ይታደጋል፡፡” (2001፣ xii)

ከላይ አንደተገለፀው በሚት ውስጥ የሚገለፁ ሀሳቦችከሰው ልጅ አስተውሎት የረቀቁ ናቸው፡፡ በመሆኑም በትርጓሜ ወቅት በሚት ውስጥ የሚመጡ ጉዳዮች ሁሉ በቁማቸው የሚወሰዱ አይደሉም፡፡ ይልቅስ የተከየኑባቸውን ትዕምርቶችና በአስተማስሎ የሚቀርቡ ሁነቶችን በትንታኔና በትርጓሜ አማካኝነት ፈትሾ ማግኘት ይገባል፡፡ይህን አይነቱን የቋንቋ አጠቃቀም ዘይቤ “የሚት ቋንቋ” የሚሉትNanette ይህም ሆኖ ግን አንድን ሚት ሙሉ ለሙሉ ተረድቼዋለሁ ለማለት እንደሚቸግር ያሳስባሉ፡፡በእርግጥ  የሚት ቋንቋ በገላጭነት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ሲኖረው የማይታወቀውንና ረቂቅ የሆነውን ልማድ በሚታወቀውና በሚዳሰሰው የሰው ልጅ ልማድ ፣ሀሳብ እና እውነታ ለመቀየር ድልድይ ሆኖ

አገልግሏል፡፡ቋንቋው በውስጡ የሚት፣የፍካሬ ልቦናና የነገረ ትዕምርት ሃሳቦችና ትዕምርቶች ስላሉበት ገለጻዎቹ እንዳይገደቡ ረድቶታል፡፡ይህም ከዚህ ቀደም ፍጹም በሰው ልጅ ልምድ እውቀት ድንበር ውስጥ የሌሉና የማይታወቁ ሀሳቦችን ለመግለጽ እንደረዳው ይጠቁማሉ( Nanette ፣2010፣9)፡፡ ይሁን እንጂ የሚት ቋንቋ ይበልጥ ትዕምእርታዊ በሆነ ቁጥር ይበልጥ ምርምርን የሚጠይቅ እና ውስብስብ እየሆነ የሚሄድ ነው፡፡ይሄ ደግሞ ለደራሲዎች የልባቸውን ለመናገር ቀና መንገድ ይከፍትላቸዋል፡፡

> ሚት በመሰረቱ በጊዜና በስፍራ እሳቤ በማይነገሩ፤የቋነቋንም ህልውና በሚገዳደሩ ጸናን ሰማያዊ ክስተቶች የተሞላ ተረክ ነው፡፡ዳሩ ግን አተራረኩ በሚፈጥረው ምናብ አማካኝነት ተረኩ አዲስ ባህርይ ይወርሳል-ኪናዊነትን፡፡ይህ የባህርይ ውርርስ ደግሞ የክዋኔውን የተስተላልፎውን ደረጃ ከፍ አድርጎ ከመረጃ ሰጪነት ሙያው በተጨማሪ ወደ ኪነጥበባዊነት ያልቀዋል፡፡ኪናዊነቱ ህጉንና ደንቡን “ዶግማውን” ወላጅ ልጁ ላይ የሚጭነው የግዳጅ ውርስ ከመሆን ታድጎ፣ትውልድ በምርጫና በፍላጎት እየተጫወተ፣እየተዝናና፣ እየተደሰተ የሚያቆየው ቅርሱ እንዲያደርገው ያስችለዋል፡፡በሚት ውስጥ የሚነሱ ሀሳቦች ከፍታ ጠልቆ የመመልከትን፣የማስተንተንን፣የመተርጎምንም ጭምር ዓይነት የላቀ ሀላፊነት ስለሚሰጥና ግዳጅን ስለሚጥል ከሚት የምናገኘው ተዝናኖት፣ከተዝናኖቱም የምናተርፈው ደስታ ፣ከድንገት ደራሹና ከአልፎ ሂያጁ ሰርካዊ ስሜት የተለየ የላቀ ደስታ(hign pleasure)ነው፡፡ ይህ ዓይነቱ የሚት ተግባር ኪናዊ ሙያ ተብሎ ይጠራል፡፡በዚህ ዓይነቱ የስሜትና የልቡና ጉዳይ ላይ ነው ነገረ ኪን (aesthetics)የሚያቀነቅነው ቴዎድሮስ (2001፣75) ፡፡

Robert Segalም በስነፅሑፍ ትምህርት ቤቶች ውስጥ አሉ ከሚሏቸው አራት ሚትን የማንበቢያ ልማዶች ውስጥ አንዱ ትዕምርታዊ ንባብ ነው፡፡ ሌሎቹ ሚቱን በዝርው ማንበብ፣ መልሶ ለማዋቀር ማንበብና ለመፍጠር ማንበብ ናቸው (Segal፣2004፣79)፡፡ ይህም የሚያሳየን ስነ ፅሑፍም ሆነ ሚት ትዕምርታዊ ሆነው መነበብ መቻላቸውን ነው፡፡ በተለይ በዘመናዊው ስነፅሑፍ ውስጥ የሚታየው አንድን ቴክስት በተለያዩ የእውቀት አቅጣጫዎች በሚገኙ ንድፈ ሃሳቦች መቃኘት እና መፈተሽ እየጎላ መጥቷል፡፡ ስለሆነም በሚቱም ሆነ በስነ ፅሁፉ መስክ አንድ መልክ ብቻ እንዳላቸው የሚታሰቡት ጉዳዮች ተደጋግመው እንዲፈተሹና በተለያዩ አቅጣጫዎች እንደገና እንዲቀርቡ አስችሏቸዋል፡፡ Segal የሚት

እና ስነፅሁፍ ተዛምዶ ብለውበዋናነት የሚያነሷቸው ጉዳዮች ስነፅሁፍ  ብሉይ ሚቶችን ጭብጥ እንደመነሻ አድርጎ መጻፉ ሚቶችን በቀጥታ በስነፅሁፍ ውስጥ አስገብቶ መጠቀም መቻሉን ነው፡፡(ዝኒ ከማሁ፣79)
እንዲሁም Levi-Straussሴጋልን ጠቅሰውእንዳብራሩትበሚት ውስጥ የሚመጡ ትልሞች የሚደረደሩት የተረኩን የጊዜ ቅደም ተከተል ጠብቀው ሳይሆን የተቃራኒ መቃለጦችን ፈጥረው ነው፡፡ እነዚህ ተቃርኖዎች በስጋ ዝምድና ውስጥ“overrating እና  “underating” የሚገለጹ መሆናቸውን Strauss በኦዲፐስ ሚት ውስጥ ሲያስረዳ “overating” በቤተሰብ መሀከል የሚደረግ ወሲባዊ ግንኙነት (ኦዲፐስ እናቱን እንዳገባው) እና በቤተሰብ ህግ የተከለከለን ጉዳይ መተላለፍ ሲሆን “underating” የሚባለው ደግሞ የወንድማማቾች መገዳደል (አቶክለስ ወንድሙ ፓሊናይስን እንደገደለው) ወይም አባትን መግደል (እንደ ኦዲፐስ) ማለት ነው፡፡በመሆኑም “overating”ተፈጥሮን ይወክላል ምክንያቱም ደመ ነፍሳዊ ድርጊት ስለሆነ “underating” ደግሞ ባህልን ያሳያል ምክንያቱም ተፈጥሯዊ አይደለም፡፡

ይህ የሚት ባህርይ በስነ ጽሁፍ ጥናት ውስጥም የሚተኮርበት ጉዳይ ነው፡፡ William Righter  ይህንን አስመልክተው ሲናገሩ ስነፅሑፍን በሚታዊ ሂስ በምንመረምርበት ጊዜ ይህ የባህርይ መንታነት አብይ ማጠንጠኛ መሆኑን ያስቀምጣሉ፡፡(Wiliam Righter.1972 329) በዚህም በተከታታይ የሚጠኑ ተቃራኒ ጥንዶች የጥናቱ ማጠንጠኛ ሊሆኑ ይገባል ይላሉ፡፡ምክንያቱም የስነ ፅሑፍ አገልግሎት ይህን ለሰው ልጅ ህልውና በጣም ጠቃሚ ግን ብዙ ያልተመረመረ ጉዳይ መግለፅም ጭምር እንደሆነ ይገልፃሉ፡፡ይሁን እንጂ ስነፅሑፍ ቀጥተኛ ያልሆነ መግባቢያ በመሆኑ የተግባቦት ችግር ሊመጣ ይችላል፡፡በመሆኑም ምናባችንን በማስፋትና እነዚህን ትዕምርታዊ የተቃሪኒ መቃለጦች በመፈተሽ ስነ ፅሑፍ በምናብ ሀይል የቀረበልንን በሰው ልጆች ህይወት ውስጥ ሊከሰቱ የሚችሉ ሁነቶችን መመርመር ያስችላል፡፡

ሌላው በሁለቱ ዘውጎች ውስጥ የሚታየው የጋራ ነገር ጥበባዊነት ነው፡፡ በሚትና በልቦለድ የታሪክ አቀራረብ ሂደት ውስጥ ስነ ፅሑፋዊነት ወይም ኪናዊነት (literariness) መታየት ሁለቱን ጥበቦች አንድ የሚያደርጋቸው የጋራ ባህሪ ነው፡፡ ከጅምሩ ሁለቱም በሰው ልጅ አእምሮ የመጠበብ ሃይል ሒደት ውስጥ መነሻቸውን ማድረጋቸው በራሱ ማሳያ ነው፡፡ልቦለዳዊ ምናብም በአካል የሌለን፣ወይም በአካል ኖሮ በጊዜ የራቀን፣ የጠፋን ነገር ወይም ጉዳይ በሀሳብ ውስጥ አግዝፈን የምንመለከትበት፣ የምንሰማበት ወዘተ. አእምሮአዊ

ወይም ህሊናዊ ሀይል ነው፡፡ በመሆኑም ልቦለድ በታሪኩ ውስጥ የማይገለጡ የሚመስሉ ታሪኮችን እንዲገለጡ የሚያደርገው እና ታላላቅ ተግባራትን የሚያከናውነው ከላይ በተገለፀው የኪናዊነት ባህሪው አማካኝነት ከሚት ጋር በመጣመር ነው፡፡

በአብዛኛዎቹ የሥነ ጽሑፍ ምሁራን ዘንድ እንደሚገለጸው ከሆነ የሚታዊ ትርክቶች በየትኛውም ማኅበረሰብ በታሪክ ውስጥ ያለፉ የማኅበረሰቡ አካላት ጀግኖቻቸውን፣ ታሪካቸውን፣ እምነታቸውን፣ አስተሳሰባቸውንና ፍልስፍናዎቻቸውን የሚያስተላልፉበት፣ የሥነ ምግባር ሕጋቸውን የሚደነግጉበትና የአኗኗር ዶግማ የሚቀርጹበት ሥርዓት ያለው ተረክ ነው፡፡ ለአብነትም (ባልዴክ Baldek164፣ 2001) እንደሚለው

በቀደመው (ዕሁፋዊ ሳይሆን ቃላዊ ተስተላልፎ በነበረነት) ዘመን የማህበረሰቡ ባህላዊ መገለጫ የሚባሉት ፎክሎርና ሃይማኖት ሚታዊ ጉዳዮችን በውስጣቸው እንደሚይዙ ያስረዳል፡፡ እንዲሁ Baltes እና Staudinger (2000)የአሜሪካየስነልቦናማህበርበሚባለውጆርናልውስጥባሳተሙትመጣጥፍ ጥበብን አስመልክቶ እንደሚከተለው ገልፀዋል፡፡

> በአጠቃላይሲታይየጥበብትርጉም (ብያኔ) በዛይላል፡፡ስለዚህየጥበብንምንነትበተለያዩመንገድችመግለጹእንደተጠበቀሆኖጥበብሁለ ገብብቃትየማዳበርናለሁሉምጉዳዮችየሚመጥንናተገቢመላ (ብልሃት) የመፍጠርችሎታነውየሚልይሆናል፡፡እንዲህዓይነቱንችሎታከሚያዳብሩትነገሮችውስጥ አንዱሚትነው፡፡ሚትበብዙዎቹየእውቀትዘርፎችውስጥተጠላልፎእንደሚገኝሁሉጥበብም በሚቶሎጂውስጥተጠላልፎይገኛል፡፡ስለዝህአንድሰውሚታዊትርክቶችንበሚሰማበትጊዜ ጥበብንምአብሮይቀስማል፡፡

ሚታዊ ጉዳዮችን ለስነ ፅሁፍ ማደራጃነት የመገልገያ ጥበቦች(መንገዶች) እንደዘመኑ ሁኔታ እና እንደ ደራሲው ቅኝትና ብቃት የተለያዩ ናቸው፡፡ የቆዩ ዘመን አይሽሬ ሚቶችን ጭብጥ መገልገል የቀደሙ ሚቶችን ሙሉ በሙሉ ስራ ውስጥ ማስገባት ፣ የቀደሙ ሚቶችን እንደገና አደራጅተው እና ለዘመኑ እንዲሆን አድርጎ መተረክ እና ሚቶችን በአዲስ መልክ ማበጀት የመሳሰሉት ይጠቀሳሉ፡፡ ከዚህ ጎን ለጎን ሚቶችን አልያም ሚታዊ ጉዳዮች ያሏቸውን ታሪኮችን እንደ ስነ ፅሑፍ መቀንበቢያነት የሚገለገሉ ደራሲያንም አሉ፡፡ ሌላው ሚትንና ልቦለድን አንድ የሚያደርጋቸው ጉዳይ የታሪክ ይዘታቸውና አቀራረባቸው

ነው፡፡የሚት ታሪክ አቀራረብ ስለህይወት በተለይም ስለሰው ልጅ ሁለንተና ስለ ማንነት ከመጠየቅ አንስቶ ህይወትን፣ አስተሳሰብን፣ አኗኗርን፣ ጥቅምን እና ጉዳትን ወዘተ. የሚፈክርበት ነው፡፡ ቴዎድሮስ "ሚት የሰው ልጅ የሚኖርበትን ዝብርቅርቅ አለም ለመረዳት እንዲሁም የተረዳውን ይህንኑ አለም መልክ ለማስያዝ የሚሞክርበት ልማድ ነው" (2001፣ 67) ፡፡ ሲል እንደገለጸው፡፡ እንዲሁ የሚት ታሪክን ምጥቀትና በሰው ልጆች የእለት ተእለት የህይወት ጉዞ ውስጥ በሚኖሩ ህቡእ ክስተቶች ወስጥ ሳይቀር ከፍተኛ ቦታ እንዳለውና ረቂቅ ጉዳዮችን የመመልከቻ መነፅር መሆኑን ለማሳየት፤ካምቤል "የሚት ታሪክ በሰውልጅባህላዊመገለጫዎችውስጥየሚቀዱ የሁለንተናየማያልቁጉልበቶችምስጥራዊአሸንዳነውቢባልአይበዛበትም"(1949 ፤3)፡፡ በማለት ይገልፃል፡፡

በአጠቃላይ ከፍ ብሎ በምሁራን እንደተገለጸው የሚት ታሪክ በየትኛውም ማኅበረሰብ በታሪክ ውስጥ ያለፉ የማኅበረሰቡ አካላት ጀግኖቻቸውን፣ ታሪካቸውን፣ እምነታቸውን፣ አስተሳሰባቸውንና ፍልስፍናዎቻቸውን የሚያስተላልፉበት፤ የሥነ ምግባር ሕጋቸውን የሚደነግጉበት የአኗኗር ዶግማ የሚቀርጹበት ሥርዓት ያለው ተረክ ነው፡፡

የልቦለድ ታሪክም እንዲሁየሁነቶችን የጊዜ ቅደም ተከተልን መሰረት አድርገው በመቀናጀት የሚቀርቡበትና በገፀባህሪያቱ የሚፈፀሙ ድርጊቶችን አነሳስ፣ አካሄድና የመጨረሻ ውጤት የሚይዝ የልቦለድ ህይወት ወይም የመፃፉ ሰበብና የህልውናው መሰረት ነው፡፡ ይህንን ሀሳብ ዘሪሁን እንዲህ በማለት ይገልፁታል፡፡

> በልቦለድ ፅሁፍ ውስጥ ታሪክ ቀዳሚው ነገር ነው፡፡ የልቦለድ መሰረታዊ ገፅታ አንድ አይነት ታሪክ መተረኩ ነው፡፡ አንድን ልቦለድ ያነበበ ሰው ስለ መፅሐፉ ቢጠየቅ ከሁሉ በፊት አሳዛኝ ታሪክ አነበብኩ ወይም አስደሳች ታሪክ አነበብኩ፣ በጣም ጥሩ የፍቅር ታሪክ ነው፣ ወይም አስለቀሰኝ እኮ ጃል! ወዘተ. በማለት ታሪኩ ያሳደረበትን ስሜት ነው እሚገልጸው፡፡ ሌላው ደግሞ ምንም የማያጓጓ አሰልቺና ደረቅ ታሪክ ሲል የቀረው አንባቢ ደግሞ በእውኑ አለም ከሚያውቃቸው ሰዎች ገጠመኝና ታሪክ ጋር በማያያዝ ይህማ የእነ እገሌ ታሪክ ራሱ ነው እያለ አስተያየቱን ይሰጣል፡፡ ይህ እንግዲህ አብዛኛው አንባቢ ከልቦለድ ገፅታዎች በቀዳሚነት የሚያሥበው ታሪኩን መሆኑን ይጠቁማል፡፡ አንባቢው የሚያነበው ድርሰት ታሪክ አልባ ቢሆንበት ንባቡን በጉጉት

ለመቀጠል ይቸገራል፡፡ አንባቢውን ይበልጥ የሚስበውና ጊዜውን አጥፍቶ እንዲያነብ የሚገፋፋው መጀመሪያ እንዲህ ሆነ፣ ከዚያ በኋላ ደግሞ እንዲህ ሆነ የሚለው የታሪኩ ጉዞና እገሌ የተባለው ሰው እንዲህ ያለ ነገር ደረሰበት ፣ ፍፃሜው እንዲህ ሆነ የሚለው የታሪኩ ገፅታ ነው፡፡ እነዚህን ጉዳዮች በማጤን ነው ታሪክ ለልቦለድ የመፃፉ ሰበብ ወይም የህልውናው መሰረት ነው የተባለው፡፡(2007፣154)

ከላይ የቀረቡት ሃሳቦች እንደሚገልጹት ለሚት ተረክም ሆነ ለልቦለድ ታሪክ ይዘት መሰረቱ ሰውና ገጠመኞቹ እንደሆኑ ነው፡፡ በልቦለድ ጽሑፍ ውስጥ ታሪክ ትልቅ ስፍራ የሚሰጠው አብይና ቀዳሚ ነገር እንደመሆኑ ታሪኩን በአንድ ሊያስተሳስሩ የሚችሉ ሁነቶች መሰረታቸው ከየት እንደሆነ መመርመሩ ተገቢ ነው፡፡ በመሆኑም  የሰው ልጆችን የእለት ተእለት ህይወት በሚታይ መልኩ ማቅረቢያ ጥበብ የሆነው ልቦለድ በታሪኩ ውስጥ የሰው ልጆችን ህይወት ያንጸባርቃል፡፡በሰው ልጅ ህይወት ውስጥ ደግሞ በገሀድ የሚታዩና የማይታዩ የህይወት ልምዶች መኖራቸው እሙን ነው እነዚህን የሰው ልጅ ሁለንተናዊ መገለጫዎች በተለይም ሚስጥራዊ የሆኑ የህይወት ልምዶችን ለመግለጥ የሚት አስተዋጽኦ ከፍተኛ ነው፡፡ በመሆኑም የልቦለድ ጽሑፍ ለታሪኩ መነሻ የሚሆኑ ሀሳቦችንና ታሪኩን የሚገነባባቸውን ሁነቶች ከነዚ የሰው ልጅ ገጠመኞች ነው የሚቀዳው፡፡እነዚህ ገጠመኞች ደግሞ ቀደም ብለው በሰው ልጅ ምናብ አማካኝነት ተቀርጸው የተቀመጡ ናቸው፡፡የሰው ልጅ እነዚህን ገጠመኞች (አካላዊና አእምሯዊ) ጉዳዮች ከቀረጻቸው በኋላ በሚት ገምዷቸዋል፡፡በመሆኑም ልቦለድ  ከዚህ የሰው ልጅ ከተፈጠረበት ጌዜ አንስቶ ከነበረ የሚት ተረክ  ለታሪኩ መነሻ ሃሳቦችን ይወስዳል በብሉይ ሚቶች ውስጥ ያሉ ተረኮችም ሆኑ በዘመኑ የሚፈጠሩት ሚቶች ለልቦለድ ታሪክ መሰረቶች (ምንጮች) ናቸው፡፡

### 2.1.9ሚቶ ኪን (mythopoesis)

ሚቶ ኪን ማለት ሚትን መከየን (መስራት)ማለት እንደሆነ የሚናገረዉ ክሪስ ባልዲክ (Chris Baladick) ይህ ሂደትም ውላዊ በሆነ መልኩ በባህሉ ዉስጥ ባለ ፎክሎርና ሃይማኖትስነ ቃላዊ በሆነ መገኛዉ አሊያም በግለሰብ ደረጃ ጸሐፊዎች ግላዊ ክህሎታቸዉ በመጠቀምና መንፈሳዊ መርሆችን በማስፋት የሚፈጥሩት ነዉ ይላል(164፣2001)፡፡ቃሉም ከዚህም ቀለል ባለ ሁኔታ የቀደሙ አሊያም መሰል ሚቶችን በርዕሰ ጉዳይነት ወይም የምናቡ መዳረሻ አድርጎ ለቀረበ ማንኛዉም ጽሁፍ መገለጫነት እንደሚዉል

ይነገራል፡፡ይሁን እንጂ በተለይ ባልዲክ በሁለተኝነት ያነሳዉ የሚቶ ኪን እሳቤ ብዙ ክርክር የሚያስነሳ ይመስላል፡፡ምክንያቱም ሚትን የመከየን ትርጓሜ እንደሚት ብያኔ ሁሉ በተለያየ የሚት ምሁራን ሰፊ የሃሳብ ልዩነቶች የፈጠረ በመሆኑ ነዉ፡፡

ብዙዎች ሚትን ያጠኑ ምሁራን እንደሚስማሙበት ሚታዊ ጉዳይን አጣቅሶ የተሰራን ማንኛዉንም የጥበብ ስራ ሚቶ ኪን ነዉ ማለት አይቻልም፡፡ ምክንያቱም የሚት ፈጠራ በኪናዊ ስራ ዉስጥ በሚታይ አንድ ሚታዊ ጉዳይ ተመስርቶ የሚዳኝ ሳይሆን በአጠቃላይ የተረኩ ትርጓሜ የሚያተኩር ስለሆነ፡፡"በስነጽሁፉ ዉስጥ በሚታየዉ አጠቃላይ የታሪኩ ጉልህነት እንጂ ለብቻዉ ተነጥሎ ሚታዊ ጠቀሜታ አለዉ የሚባል ልዩ ጉዳይ የለም፡፡"የሚሉት William Righter (1972፣327) የስነጽሁፍ ፍካሬና ትርጓሜም ቢሆን የተረኩን ፍሳኅት ተከትሎ የሚጓዝ መሆኑን ያስረዳሉ፡፡በመሆኑም የሚት ፈጠራም ሆነ ሚታዊ ጠቀሜታ የሚዳኙት በአጠቃላይ የተረኩ ስርዓት ዉስጥ በሚኖራቸዉ ፋይዳ ነዉ፡፡

በተመሳሳይ አንድ የሚት ፈጠራን ምሉዕ የሚያደርገዉ በዉስጡ ሚታዊ ጉዳይ መኖሩ ብቻ ሳይሆን አጠቃላይ የአከያየን ሂደቱም ጭምር ሲሟላ መሆኑን የሚገልጹጽNanette ፣በሚት ፈጠራ ወቅት ሚታዊ የሆነ አስተሳሰብ እና አወቃቀርን የመከተል አይቀሬነትን ይገልጻሉ፡፡ከዚህ በተጨማሪም ‹‹ሚቶ ኪኑ የቀደመዉን ሚት እንደገና በመፈከር አዲስና ምሉዕ ሃሳብ መፍጠር አለበት (Nanette 4010፣10) ፡፡ በማለት አጽንኦት ሰጥተው ያስረዳሉ፡፡ በመሆኑም በስነጽሁፍ ዉስጥ ብልጭ ድርግም የሚሉ ሚታዊ ጉዳዮች ሁሉ ለብቻቸዉ ለስነጽሁፍ ያበረከቱት ሚታዊ ጠቀሜታ አለ፤ አሊያም የሚታዊ ኪኑ አካል ናቸዉ ማለት አይቻልም፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ የሚት ፈጠራን ከርዕዮተ ዓለማዊ ፍልስፍና ጋር አጣምሮ የሚያነሱትMichael Bell ‹‹ትክክለኛዉ የሚታዊ ኪን እሳቤ ፣ጸሐፊዉ በቀደመዉና በሚታወቀዉ ሚታዊ ልምድ በመገልገል የአንባቢዎችን ምናብና መረዳት ወደ ዘመናዊዉ የራሱ ዓላማ ማድረስ ሲችል ነዉ›› ይላሉ (1997፣228)፡፡የቀደመዉ የሚት ዕሳቤ የሚያተኩረዉ ሞራላዊና ስነምግባራዊ ጉዳይ ላይ የነበረ ሲሆን በዘመናዊ ዕሳቤ ዉስጥ ይህ የሚት ዕሳቤ ተለዉጧል፡፡በመሆኑም የቀደሙ ሚታዊ ጉዳዮች ተመልሰዉ ቢመጡ እንኳን መታየት ያለባቸው በቀደመዉ ዓይነት የሂስ ልማድ ሳይሆን በአዲስ ፍልስፍናዊና ርዕዮተ-ዓለማዊ መንፈስ ነዉ፡፡በዚህ ጥናትም ደራሲዉ በስነ ጽሁፎቹ ዉስጥ የተገለገለባቸዉንሚቶች

በቀደመዉ ማህበራዊ አስተምሮ ዓይን ሳይሆን ከደራሲዉ የአጻጻፍ ቴክኒክ አንጻር ቴክስታዊ ትንተና ያደረገ ነዉ፡፡

## 2.2 የተዛማጅ ጽሁፎች ቅኝት

በዚህ ንዑስ ክፍል ከዚህ ቀደም በደራሲው ስራዎችና የአማርኛ ስነፅሁፎችን ከሚቶሎጂ አንፃር ያጠኑ እንዲሁም ከአካሄድ አንፃር በተቀራራቢነት የተጠኑ ምርምሮችን ለመቃኘት ሙከራ የተደረገ ሲሆን ከጥናቱጋርበቅርቡየሚወዳጁነገርግንለየቅልዓላማንያነገቡናያሳኩ፣በሩቁደግሞየሚጠራሩየሁለተኛ ዲግሪማሟያጥናቶች፣የጉባዔና የመፃህፍት መጣጥፎችና የመጀመርያዲግሪማሟያጥናትተቃኝተዋል፤ልዩነታቸው፣መወዳጀታቸውእናመጠራራታቸውም ተጠ.ኗል፡፡ በቅድሚያም በደራሲው ስራዎች ላይ የተደረጉ ምርምሮች ቅኝት ይቀርባል፡፡

አጥኚዋ ባደረገችው ዳሰሳ በአለማየሁ ዋሴ ስራዎች ላይ በሁለተኛዲግሪ ደረጃ የተጠኑ ጥናቶችን ማግኘት አልቻለችም ነገር ግን የደራሲውን ስራዎች ከዚህ ጥናት በተለየ መንገድ የመረመሩ አንድ የመጀመርያዲግሪማሟያጥናት እና በመቅረዝ ዘተዋሕዶ ላይ የቀረበአጭርሥነጽሑፋዊዳሰሳ ተመልክታለች ሁለቱም ስራዎች በደራሲው "እመጓ" በተባለው ልቦለድ መፅሐፍ ላይ ትኩረት ያደረጉ ናቸው፡፡ እነሱም እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

የ"እመጓ ረጅም ልቦለድን ፎክሎራዊጉዳች ትንተና" በሚል ርዕስ በስለሺ አስፋው (2009) ለአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ የተደረገ ጥናትተጠቃሽ ሲሆን፤ የጥናቱ ዓላማ የእመጓ ረጅም ልቦለድ ፎክሎራዊ ፋይዳ ለይቶ ማሳየት ላይ ያተኮረ ነው የሚል ሲሆን በመፅሐፉ ውስጥ የሚገኙት ፎክሎራዊ ጉዳዮችን ለይቶ በማውጣት ለልቦለዱ አላባውያን ያበረከቱትን ጥቅም፤ የፎክሎርንና የስነ ፅሑፍን ትስስር ለማሳየት የተጠና ጥናት ነው፡፡

ጥናቱ ገላጭ የምርምር ዘዴን የተከተለ ሲሆን በመረጃ መተንትኛነት አይነታዊ የመረጃ መተንተኛ ዘዴን ተጠቅሟል፡፡ በውጤቱም በመጽሐፉ የፎክሎርን እና የስነፅሑፍን ትስስርና አብሮነት በጉልህ እንደታየ፤ደራሲው መጽሐፉን ባልተለመደ ርዕስ ጉዳይ ይዞ በመገኘቱእና በውስጡ ያሉ ፎክሎራዊ ጉዳዮች አንባቢ ሳይሰለች ወደ ታሪኩ ፍፃሜ

እንዲደርስ ማድረጋቸውን ገልጿል፡፡በመሆኑም ይህ ጥናት ከዚህ ጥናት ጋር በቴክስት ምርጫም ሆነ በርዕሰ ጉዳይ ልዩነት አለው ፡፡

ብርሃኑ አድማስበመቅረዝ ዘተዋህዶ መፅሔት "እመጓ ላይ የቀረበ አጭር ስነ ፅሑፋዊ ዳሰሳ" (2008) በሚለው መጣጥፍ የመፅሐፉን አስደናቂነት፣ ኪናዊነት፣ከፍልስፍና ጋር ያለውን ግንኙነት በሰፊው በማብራራትና ከሐዲስ ሚቶሎጂ የአቀራረብ መርህ በመነሳት "እመጓ"ን ዘመናዊ ሚት ውስጥ ከሚያስመድበው አንዱ የቀረበበት ኪናዊ ብቃት ነው፡፡ እጅግ ልብ አንጠልጣይ ታሪክ፣ ሰውነትን ሰቅዞ በሚይዝመንገድ ለማቋረጥ በሚያስቸግር የትረካ ስልት መቅረቡ የኪናዊነቱን ደረጃ አመላካች መሆኑን ከዚህም በላይ ደግሞ እኩላዊነትን በማሳየት ደረጃ ከፍተኛ ሚና የሚጫወት በመሆኑ መፅሐፉ ሚታዊ ፍልስፍና ነው ለማለት መድፈር እንደሚቻል ገልጿል፡፡

በማጠቃለያው የእኛ ዘመን ዘመናዊ ትውልድ የደረሰበትን የባህል ግጭት ማዕከል አድርጎና ቀዳሚው የሕይወት ፍልስፍናችን ከአዲሱ የሰው ልጅ የቴክኖሎጂ እድገትና ውስብስብነት ጋር ከመስማማት አልፎ ሚያመጣውን ችግር የማስወገድና የማከም አቅም ያለው መሆኑን ለማሳየት የተዘጋጀ ሚታዊ ድንቅ የጉዞ ልቦለድ መሆኑን በማስረዳት፤ በተለይም ጽዋው መንዝ ውስጥ እመጓ ይገኛል ብሎ ሲሳይን በዚሁ አሳምኖ መጨረሱ መጽሐፉ አንደኛ በአንጻረ ጽዋ የሕይወት መገኛዎች (ለምሳሌ እንደነ አባ አክሊሉ ዓይነት ሰዎች) ያሉት እዚህ ነው፤ ማዕከሉም (መንዝ ለኢትዮጵያ ማዕከል እንደ ምትሆነው) እዚሁ ነው፤ መንዝ የሕይወት መርጫዉም፣ ተረጭውም፤ ረጪውም፣ የሚረጨውም እዚሁ ነው፡፡ እመጓ - እመ እጓል ፦ የልጆች እናትም ኢትዮጵያ ናት፤ ሌላው ከእንጀራ እናትነት አያልፍም የምትል ለኢትዮጵያ ከተሜ ትውልድ ፈውስነት የቀረበች የአእምሮ ማረጋጊያ (Mental Therapy) እንደምትመስል በመግለፅ፤ መጽሐፉ በኢትዮጵያ ዘመናዊ ሥነ ጽሑፍ ውስጥ ያለውን ቦታና ማኅበረሰባዊ ተጽእኖ ለማየት ገና ሰፊ ጥናትና ምርምርን የሚሻ ድንቅ መጽሐፍ መሆኑን ከመናገር ለማለፍ ለአሁኑ አስቸጋሪ እንደሆነ በመግለፅ ዳሰሳውን ቋጭቷል፡፡ ብርሃኑ በዳሰሳው "እመጓ" መፅሐፍ በሐዲስ ሚቶሎጂ ስነ ፅሁፋዊ አቀራረብ መቅረቡንና ሚታዊ ጉዳዮች በመፅሐፉ ውስጥ በስፋት መኖራቸውን ማሳየቱ ከዚህ ጥናት ጋር የሚያቀራርበው ቢሆንም ጠለቅ ባለ መልኩ በአቀራረቡ ጭብጡ ላይ በሰፊው መዳሰሱ እና "እመጓ" ልቦለድ መሆኑ ከዚህ ጥናት የተለየ እንዲሆን ያደርገዋል፡፡ በመሆኑም ከላይ የቀረቡት ሁለት ስራዎች

የደራሲውን ስራዎች መመርመር በመቻላቸው የተመረጡ ሲሆኑ ስራዎቹን በመረመሩበት አንፃር አንዳቸውም ከዚህ ጥናት ጋር የቀረበ ግንኙነት የላቸውም፡፡

ሌላውከዚህጥናትጋርበሩቁየሚጠራሩትየለማ ንጋቱ እና የቴዎድሮስ ገብሬ ጥናታዊ ፅሑፎች ናቸው፡፡

ለማ ንጋቱ (2008) "ብቻ…ብ…ቻ ምን ይሆና…ል!" የ "ባህታዊ" ገጸ ባህሪያት ስነ-ጽሁፋዊ ፋይዳ ፍከራ በፍቅር እስከ መቃብርና በቴዎድሮስ እንባ ልቦለዶች በሚል ርዕስ በሀዲስ ዓለማየሁ የባህል ጥናት ተቋም አራተኛዉ ዓመታዊ አገር አቀፍ አዉደ ጥናት መድብለ ጉባኤ ላይ ያቀረቡት ጥናታዊ ጽሁፍ ሲሆን ከላይ በተገለጹት ልቦለዶች ዉስጥ የተሳሉት "ባህታዊ" ገጸ ባህሪያት ለልቦለዶቹ ያበረከቱትን ስነ ጽሁፋዊ ፋይዳ ጥቃቅን ሁነቶችን እየመዘዙ በአንድምታ በመፈከር መተንተንን በዓላማነት ይዞ የተነሳ ሲሆን የመረጃ መተንተኛ ዘዴዉ በዲስኩር ትንተና (disoouse analaysis)ላይ አድርጓል፡፡ በጥናቱ የተገኘዉ ዉጤትም ደራሲ ሀዲስ ዓለማየሁና ብርሃኑ ዘሪሁን የዛን ዘመን ሃይማኖታዊና ባህላዊ ህጸጾች በኦርቶዶክስ ሃይማኖት ተከታዮች ዘንድ ታላቅ ክብር በሚሰጠዉና በሚናገረዉ ላይ ታላቅ አመኔታ በሚጣልበት ባህታዊ ገጸ ባህሪይ አማካኝነት እንደነቀሱት ያሳያል፡፡አንድ ነገር(ርዕሰ ጉዳይ) ከልቦለድ ዉስጥ መዞ አዉጥቶ በፍካሬ በመተንተን ስነ ጽሁፋዊ ፋይዳን ከማሳየት አንጻር ከዚህ ጥናት ጋር ተመሳስሎ ያለዉ ቢሆንም ፍካሬ በሚደረግባቸዉ ልቦለዶች፣በርዕሰ ጉዳይ፣በመተንተኛ ንድፈ ሃሳብና በዓላማም ከዚህ ጥናት ይለያል፡፡

ቴዎድሮስ ገብሬ በይነ ዲስፕሊናዊ የስነ ጽሑፍ ንባብ(2002) በሚለው መጽሀፉ "የአማርኛ የርእይ መነጠቅ ልቦለዶች"በሚል ርዕስ በፍቅር እስከ መቃብር ፣በየቴዎድሮስ እንባ፣በአደፍርስ እና በከአድማስ ባሻገር ውስጥ የሚኖሩ የጋራ ጉዳዮችንና ተመሳሳይ ገፅታዎችን ፈልጎ ማግኘትና ነድፎ ማሳየትን አብይ ትኩረቱ በማድረግ ድርሰቶቹ "የርእይ መነጠቅ ልብ ወለዶች" ናቸውየሚለውን መላምት ለማረጋገጥ ያደረገው ጥናት ሲሆን የተለያዩ ነገሮችን የጋራ ጉዳይ በአንድ አምጥቶ በማሳየትና ሚቶሎጂያዊ ንባብንና ሚታዊ ተረኮችን ለጥናቱ መተንተኛና መፈከሪያ ስልት በማድረጉ የሚጠራራ ቢሆንምሚታዊ ትርክቶች ለስነ ጽሑፉ ታሪክ ያላቸውን አስተዋጽኦ አይመለከትም፡፡በመሆኑም ሚቶሎጂያዊ ንባብ በማድረግ ረገድ ከዚህ ጥናት ጋር ቢገናኝም በቴክስትምርጫና በርዕሰጉዳይ እይታከዚህ ጥናትይለያል፡፡

ከዚህ በታች የቀረቡት ምርምሮችና የመመረቂያ ጥናቶች ደግሞ ከዚህ ጥናት መመርመሪያ አንፃር ጋር በተለያየ ደረጃም ቢሆን ዝምድና አላቸው ብዬ በማመኔ ያካተትኳቸው ናቸው፡፡

የመጀመሪያው ቴዎድሮስ ገብሬ ("Myth and sexuality a Mythopoetic Reading of LetumAynegalin" በሚል ርዕስ ያሳተመው መጣጥፍ ነው ቴዎድሮስ በዚህ ልቦለድ ያደረገው ሚቶ ኪናዊ ንባብ የደራሲውን የሚት ከያኒነት እንዳሳየ ገልጧል፡፡ ስብሐት በሌቱም አይነጋልኝሚቶሎጂያዊ ጉዳዮችን እንደሚገለገልና ሚቶቹን ለስነፅሑፍ ማደራጂያነት እንዳዋላቸው በመግለፅ ልቦለዱ ለሚቶ ኪናዊ ንባብ ምቹ እንደሆነም ይጠቁማል፡፡ መጣጥፉ እንደሚያስረዳው አብዛኛው የቴክስቱ አደረጃጀት በሚት የተዋቀረና ሚታዊ ጉዳዮችን ያካተተ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ነገረ ወሲብን የሚያትቱ ተረኮች፣ ፀሎቶች፣እንዲሁም ከቀደምት ሃይማኖቶች የተገኙ የተቀቀደሱ ምህላዎች ወዘተ. ያለበት ነው፡፡በመሆኑም ሚታዊውም ሆነ ነገረ ወሲባዊ ጉዳዮች ለተረኩ ፍሰት መልካም አስተዋጽኦ ከማበርከታቸው በተጨማሪ ለልቦለዱ መዋቅር መሳካትም የራሳቸው ሚና እንዳላቸው ይጠቁማል፡፡ለዚህም ልቦለዶቹ ከተከፈሉባቸው ስምንት ምዕራፎች አራቱ በግዕዝ ከተፃፉ ሀይማኖታዊ መፃህፍት ስሞች ተወስደው ነገረ ወሲብን ለመግለጫነት መዋላቸውን እንደ አንድ ማስረጃ ያቀርባል፡፡

በልቦለዱ የውቤ በረሃ ንጉስ ተደርጎ የተሳለው ጥላሁን የተሰኘው (ደፋር፣ ኩሩ፣ ወንዶች የሚፈሩት በተቃራኒው ፍቅርን የሚፈልግና የሚያሳድድ) ገፀ ባህሪ ሚታዊ ገፅታው የጎላ እንደሆነ የሚገልፀው ቴዎድሮስ የጥናቱ ዋነኛ ማጠንጠኛውም አድርጎታል፡፡ የጥላሁን እንደተለመዱት ሚታዊ ገፀባህሪያት ሁሉ በተለያዩ ተቃርኖዎች የተሞላ ስብዕና ያለው ነው፡፡ ጥላሁን የነውጥና የተንከባካቢ (የፍቅር) ባህርያትን በአንድ አዋህዶና አስማምቶ መያዝ ሚታዊ ገፅታውን ያጎላው በመሆኑ ቴዎድሮስ ሚቶሎጂያዊ መባያ ናቸው ባላቸው ስስት ጉዳዮች ማሳያነት አቅርቧቸዋል፡፡(*"the fusion of opposite", "shape-shifiting"* እና *"crossing the threshold"*) በሚል ከፍሏቸዋል፡፡ከዚህ በተጨማሪም የፍካሬ ልቡናን አቀራረብ በመጠቀም ገፀ ባህሪው በወሲብ ዙሪያ ለውን ድርጊት ኢ-ንቁ ፍትወትን (*unconscious desire*)የመሳሰሉ ጉዳዮችን በመቃኘት አጠቃላይ ትንተናውን ሚቶኪናዊነትንና ፍካሬ ልቡናን በማጣመር አከናውኗል በዚህም ድርሰቱ በሚትና በነገረ-ወሲብ ጉዳዮች መባያነት ማህበረሰቡ ከገዛ እሴቶቹ ጋር ያለውን ግጭት ማሳየት እንደቻለ ቴዎድሮስ ይገልፃል፡፡ ይህ የቴዎድሮስ መጣጥፍ ሚታዊ ጉዳዮች በመፅሐፉ ውስጥ መካተታቸውን በማሳየት ረገድ ከዚህ ጥናት ጋር ቢወዳጅም ሚቶ ኪናዊነትን መዳሰሱ፣የነገረ

ወሲብን ጉዳይ ጠለቅ ብሎ መዳሰሱና ትኩረቱ ደሞ የስብሐት ገብረ እግዚአብሔር ሌቱም አይነጋልኝ ልቦለድ መሆኑ ከዚህ ጥናት የተለየ ያደርገዋል፡፡

ሌላኛው ከዚህ ጥናት ጋር የቀረበ ዝምድና ያለው የቴዎድሮስገብሬን በ2013 እ.ኤ.አ. Reading Contemporary African Literature: Critical Perspectives በሚልስብስብውስጥየታተመው፡፡ "Mahilet: A Laboratory of Stylistic Experimentation" የተሰኘመጣጥፍነው፡፡ በመጣጥፉ በአዳም ረታ ስነ ጽሑፋዊ ስራዎቹ ውስጥ ያለውን የሚቶሎጂ አጠቃቀም አሳይቷል፡፡በተለይ በመጣጥፉ ሦስተኛ ክፍል"*Mythopoesis as a Means of self-Reflexivity*" በሚለው ንዑስ ርዕስ ስር ዋና ትኩረቱ ያደረገው የአዳም ረታ "ማሕሌት" የተሰኘ መድብልን ሚታዊ አከያየን ማሳየት በመሆኑ ለዚህ ጥናት ቀረቤታ አለው፡፡ ይህ ልቦለድ በሚታዊ ጉዳዮች የተቀናበረና የበለፀገ በመሆኑ ተደራሲያንን ከአፃፃፍ ብልሀቱ ጋር ለማገናኘት፣ ግራ መጋባቶችን ለማጥራት፣የተደበላለቀውን ስርአት መልክ ለማስያዝና ተደራሲውን ከፍተኛ ኪናዊ እርካታ ላይ ለማድረስ ሚቶኪናዊ ንባብ ተገቢ እንደሆነ ያሥረዳል፡፡በተጨማሪም የተመለከታቸው "ግልገልብላሽ"፣ "ሳምራዊው" እና "ኤልዛቤል"
የተሰኙትንአጫጭርልቦለዶችነው፡፡አዳምበስራዎቹየሰውልጅማንነቶችን፣ሁኔታዎችንና "መደናገሮችን" የሚጠሩጭብጦችን፣እንደብቸኝነት፣መነጠል፣የሰብዓዊነት "መንጠፍ" እናየሰብዕና "አለመዋሃድን" የሚቀምርጸሐፊእንደሆነ፣የሚስላቸውገፀ-ባህሪያትምብዙጊዜራሳቸውንመሆንያቃታቸው (ለራሳቸውባይተዋርየሆኑ)፣ቤተሰባቸውንናልማዳዊማንነታቸውንያጡእንደሆኑና "ጊዜ-ስፍራ-አዕምሮ" በአዲስናሚታዊበሆነየአገላለፅቅጥእንደሚቀርቡባቸውያስረዳል፡፡

እንዲሁም
ሚታዊጉዳዮችየተራኪውንጉዞእያበጁታሪኩንእንደሚያደራጁእናየጊዜናየቦታአዛማጅሆነውእንደ ሚያገለግሉ፣በተለይ "ማሕሌት" በሚታዊነቷየላቀችናበፈጠራዊሚት (Mythopoeia) ስራንየማዋቀርስልትየበለፀገችእንደሆነችሞግቷል፡፡በመጣጥፉጽንሰሃሳቦችንከትንተናጋርበማዋሃ ድ፣የቴክስቶቹንመዋቅርናአደረጃጀትደግሞሚታዊጉዳዮችንከመጽሐፍቅዱስበመጥራትተርጉሟ ል፡፡ይህየቴዎድሮስጥናትልዩ ትኩረት የአዳምን ሚቶ ከያኒነት፣ የገፀ ባህሪያት አሳሳል ጥበብ ላይ ያደረገ በመሆኑና በመፅሐፍ ምርጫውም ከዚህ ጥናት ጋር አይገናኝም፡፡

ባይለየኝ (2002) “Myth and Reality;Mind of Ethiopian poets on the Blue Nile” በሚል ርዕስ ለአስረኛው የአባይ ጉባዔ ላይ ያቀረበው ጥናት ሌላው ከዚህ ጥናት ጋር ቅርበት ያለው ጥናት ነው፡፡ጥናቱ በታሪክና በሚቶሎጂ ጉልህ ስፍራ ያለው የአባይ ወንዝ በኢትዮጵያ ገጣምያን ላይ ያሳደረው ተፅዕኖን በኪናዊ ስራቸው ዋቢነት ለማሳየት የሞከረ ነው፡፡ ዓባይ በታሪክና በሚቶሎጂዎች (በግሪክ በግብፅ) ውስጥ ያለውን ገናን ቦታ በዳራነት ያቀረበው ይህ ጥናት የኢቶጵያውያኑን የሀይሉ ገብረዮሀንስ (ገሞራው) “እናትክን በሉልኝ” እና የሎሬት ጸጋዬ ገብረመድህን “አባይ” የተሰኙ ግጥሞችን ብቻ በመውሰድ ገጣምያኑ ስለ ወንዙ ያላቸውን ስሜት በትንታኔው አሳይቷል፡፡በዚህም ገጣምያኑዓባይ በታሪክም ሆነ በሚቶሎጂ ያለውን ዝና ከመግለፅ ባሻገር ዓባይ የሀገራቸውም ሆነ የአፍሪካ ትንሳኤና የብልጽግና ተስፋ መሆኑን በተለያየ መልክ እንደገለፁ ጥናቱ አመልክቷል፡፡ ጥናቱ የሚትና ስነ ጽሑፍን ትስስር የሚያሳይ፤ ሚቶች ምን ያህል በዚህ ዘመን ስነፅሑፋዊ ስራዎች ላይ ተፅዕኖ መፍጠር እንደሚችሉ ያሳየ ይመስለኛል፡፡ ነገር ግን ጥናቱ በግጥም ስራዎች ላይ ብቻ ማትኮሩ፣መድብሎቹ እኔ ለጥናት ከመረጥኳቸው ልቦለድ መፃህፍት ልዩ መሆናቸውና ጥናቱ የቀረበበት ዓላማ ከስነጽሑፋዊነት በዘለለ በወቅቱ በወንዙ ዙሪያ ላለው ፖለቲካዊ አስተሳሰብ ማሳያነት ጭምር የታሰበ በመሆኑ ከዚህ ጥናት ይለያል፡፡

በመጨረሻም ከዚህ ጥናት ጋር በቅርብ የሚዛመደውናበጥልቀት የቃኘሁት የታደሰ ሺበሺ “ሚቶሎጂያዊ ጥናት እቴሜቴ ሎሚ ሽታ እና ይወስዳል መንገድ ያመጣል መንገድ በተሰኙ የአዳም ረታ መድበሎች” በሚል ርዕስ ለኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ በ2005 ዓ.ም. የቀረበ ጥናት ነው፡፡በ67 ገፆች የተሰናዳው የታደሰ ጥናት፣ በመረጣቸው መድበሎች ውስጥ የተደራጁ ሚቶሎጂያዊ ጉዳዮች ለሥነ ጽሑፋዊ ስራው ያበረከቱትን አስተዋጽኦ መመርመር በአብይ አላማነት፣ የሚታዊ ጉዳዮችን አቀራረብ፣ የአዳምን ሚቶ ከያኒነት እና የሚያነሳቸውን ጭብጦች መመርመር ደግሞ በንዑስ አላማነት ይዞ የተነሳ ነው፡፡ የምርምር ጥያቄዎችም ከአላማዎቹ ጋር የተሳሰሩ ሲሆኑ ጥናቱን ያካኼደበት ዘዴ “ቴክስታዊ ትንተና” ሲሆን፣ ለትንተናው የሚያግዘው ንድፈ ሃሳባዊ ዳራም አበጅቷል፡፡ ስለ ሚት ምንነትና አመጣጥ፣ ስለ በይነ ዲሲፕሊናዊነቱና ስለ ሚቶ ኪን ሰፊ ማብራሪያ ከሰጠ በኋላ የሚትንና የሥነ ጽሑፍን ግንኙነት አስፍሯል፡፡

በሚትም ሆነ በሥነ ጽሑፍ የኢ-ንቁ ልቡና ሁኔታዎች እና ማኅበራዊ ውጉዙነት የሚደርስባቸው በትዕምርት የሚቀመሩ ሃሳቦች ወደ ፍቺዎቻቸው [የምንጠጋው] በጥልቅ

ፍካሬና ትርጓሜ እንደሆነም አስረድቷል፡፡ ሚታዊ ቋንቋና ገላጭነቱ (ከሰው ልጅ ምናብ የሚረቁና የሚጸኑ እሳቤዎችንና ክስተቶችን በሰርካዊ ልማድ የመቀየር አቅም እንዳለው፣ ደራሲዎች ያሻቸውን መናገር እንደሚያስችላቸው)፣ ሳታየር፣ አስተኔ ደራሲ፣ ሚስጢራዊ የቋንቋ አጠቃቀም፣ ትንቢትና ርዕይ ህልም፣ አስማት፣ "አርኬታይፕ" የሚሉ ጽንሰ ሃሳቦችን በንድፌ ሃሳባዊ ቅንብቡ ተመልክቷል፡፡ የታደሰ ትንተና በሦስት አቢይ ጉዳዮች ላይ ያረፈ ነው፡፡ የመጀመሪያው የ"ተቃራኒዎች መቃለጥ" ነው፡፡ አዳም ሰርካዊ የሆነውን የሚት ትልም ማዋቀሪያ፣ የተቃራኒ ስሜቶችን መዋሃድ፣ ለሥነ ጽሑፋዊ ሥራዎቹ የትልም ማዋቀሪያነት እንደሚገለገልባቸው አሳይቷል፡፡ "አሞራ፣ እንደልዕለ ሰብዕ ተራዳኢ" በሚለው የትንታኔ ክፍሉ፣ በተለይም ይወስዳል መንገድ ያመጣል መንገድ፣ "አሞራ" ለዘመናዊ ሥነ ልቡና ተጋዳሊ የልዕለ ተፈጥሮ ረድኤት እንደሆነና አሮጌውን "ኑረት" በመናቅ ወደ አዲስ ህይወት እንዲሸጋገሩ እንደሚያደርግ ተንትኗል፡፡በመጨረሻው የትንተናው ክፍል "ሚታዊ ጉዳዮች በልጆች ጨዋታ" የሚል ርዕስ አበጅቶ "እቴሜቴ የሎሚ ሽታ" የሚለው የልጅነት ጨዋታ እቴሜቴ ሎሚ ሽታ የተሰኘውን መድበል እንዴት እንዳዋቀረ ተመልክቶበታል፡፡

በማጠቃለያው፣ አዳም፣ ለሥነ ጽሑፋዊ ስራዎቹ ማደራጃ ሚቶሎጂን እንደሚጠቀም፣ ሚታዊ ቋንቋን፣ ምናባዊ ደራሲና ምትሃት የአጻጻፍ ብልሃቶችን ለሃሳቡ ማሂጃነት እንደሚገለገልባቸውና ሚታዊ ትዕምርትን ለሥነ ጽሑፋዊ መዋቅርና ጭብጥ ማበልጸጊያነት እንደሚያውላቸው አሳይቷል፡፡ የቀደሙ ሚቶችን ዳግም ልደት እያጎናፀፈና እያዘመነ የሚጽፍና በአዲስ ንጽረት ለአንባቢያን እንካችሁ የሚል በመሆኑ ሚቶ ከያኒ እንዲሆን አስችሎታልም ይላል፡፡ እንደ ወሲብና ፆታ ያሉ ጉዳዮች ተደጋግመው የሚመጡ በመሆናቸው ከ"ነገረ ወሲብ" እና "ነገረ ፆታ" አንጻር ቢጠኑ መልካም እንደሆነም ጠቁሟል፡፡ የታደሰ ጥናት ሚታዊ ተረኮችን በማሳያነት በማተት መተንተኑ ከዚህ ጥናት ጋር ቢያመሳስለውም ሚቶሎጂያዊ ጉዳዮች ለአጠቃላይ ሥነ ጽሑፋዊ ስራው ያበረከቱትን አስተዋጽኦ መመርመር ላይ ማትኮሩና የኔ ጥናት ደግሞ ሚታዊ ተረኮች በተመረጡት ልቦለዶች ታሪክ ቀጣይነት ላይ ባበረከቱት አስተዋፅኦ ላይ ማትኮሩ እና በመፅሐፍ ምርጫ ጥናቱን የተለየ ያደርገዋል፡፡

# ምዕራፍ ሦስት

## የጥናቱ ሥነ-ዘዴና ዘዴዎች

### 3.1. የጥናቱ ሥነ-ዘዴ

በሳይንሳዊ ጥናት ውስጥ የተሰበሰቡትን መረጃዎች በዓይነታቸውና በይዘታቸው ለይቶ በማደራጀት ከሥነ-ዘዴው ጋር ተስማሚ በሆኑ ንድፈ ሐሳቦች መተንተን የተለመደ ነው፡፡በዚህ ጥናትም መረጃዎችን ለመተንተን ብዝሃ-ግብር አቀራረብ (multifunctionalism approach) ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ ሚቶልጂ አንድ ዓይነት ተግባር ብቻ አለው ብሎ መደምደም ተገቢ ስላልሆነ ይህንን አዲስ አቀራረብ መከተል የሚቶልጂን ጥናት የእድገት ደረጃ አንድ ተጨማሪ እርምጃ ወደፊት ይወስዳል፡፡ ስለሆነም በተግባራዊ ንድፈ ሐሳብ ላይ ተመስርቶ ገና በመዳበር ላይ የሚገኘው ብዝሃ-ግብር አቀራረብ በዋናነት ለዚህ ምርምር መረጃዎች መተንተኛ ውሏል፡፡

የብዝሃ-ግብር አቀራረብ መሠረታዊ አሠራሩ ከየተግባር ንድፈ ሐሳብ ጋር ተመሳሳይ ሆኖ ነገር ግን ለሁለም ባህል የሚሠራ ውስን የሚቶሎጂ ተግባራትን ማስቀመጥ አይቻልም ይላል፡፡ ይህ አቀራረብ ለሚቶልጂ ጥናት ተስማሚ መሆኑን Kirk (1973፣83) ሀሳብ ማቅረቡን መጥቀስ ይቻላል፡፡ ከሚት ጋር አያይዞ ስለ ብዝሃ-ግብር አቀራረብ፤ Kirk ሃሳቡን ሲገልፅ፣ Levi-Straussሁሉም ሚቶች ቅራኔዎችን ያስታርቃሉ በሚለው ንድፈ ሐሳቡ መጽናቱን ይቃወምና የተወሰኑ ሚቶች በተወሰኑ ባህሎች ውስጥ የመግለፅ ተግባር ያላቸው መሆናቸውን ማረጋገጡን ይደግፋል፡፡

እንደ Kirk ሃሳብ ለዘመኑ የሚት ተማሪ አስፈላጊ ነገር የሚሆነው በማንኛውም ባህል ውስጥ የሚገኙ ሚቶች ከተለያዩ ባህርያት የተወሰኑትን ወይም ሁሉንም እንደሚይዙ ማወቅ ነው፡፡ ስለዚህ በሰው የስሜት መግለጫና ምናብ ላይ አስቀድሞ አጠቃላይ ንድፈ ሐሳቦችን መጫን ተገቢ አይሆንም ይላል፡፡ በመሆኑም Kirk የሚቶልጂ ተግባራትን ለመግለፅ አጠቃላይ ንድፈ ሐሳብለመንደፍ (በጥቅልንድፈ ሐሳብለመግለፅ መሞከር) ተገቢ አይሆንም የሚል አቋም ያራምዳ፡፡ከዚህ ከKirkአባባል ሚቶሎጂ በርካታ ተግባራት እንዳሉት እንገነዘባለን፡፡

በተግባር ንድፈ ሐሳብስመጥርየሆነውJoseph Campbellከ1985-86 በተከታታይበተላለፈውየቴሌቪዥንፕሮግራም፣ከቢልሞዬርስጋርባደረገውቃለ መጠይቅሚቶሎጂአራትዋናዋናተግባራትእንዳሉትተናግሯል፡፡እነዚህንምአርምሚዊወይምተመ ስጧዊ፣ስነፈለካዊ፣ማህበራዊናሥነልቦናዊ (ሥነ-አእምሮአዊ) በማለት ይገልጻቸዋል፡፡እንደCampbellትንተናየሚትአርምሚዊ (ተመስጧዊ) ተግባር፤ሰውረቂቅበሆነመንፈሳዊመንገድከአምላኩጋርተገናኝቶበተራውዓለምናበተራውመንፈስ ተሁኖየማይደረስበትንጥበብእንዲያገኝማስቻልነው፡

ሥነፈለካዊውየሚቶልጂተግባርየዓለምንአፈጣጠር፣እንድናውቅየሚረዳሲሆንማህበራዊውተግባር ደግሞማህበራዊልማዶችእንዲጠበቁናእንዲቀጥሉየራሱንሚናይጫወታል፡፡ስነልቦናዊውተግባርየ ህይወትውጣውረድንወይምየዓለምንተለዋዋጭየህይወትዘይቤእንድንላመድወይምራሳችንንከሁኔ ታዎችጋርእንድናዛምድይረዳናል፡፡

በመሆኑምየብዝሃ-ግብር አስተሳሰብ አንድ ነገር ከአንድ በላይተግባራት ያሉት መሆኑን ያሳያል፡፡ሚቶሎጂምአንድተግባርብቻያለውስላልሆነበዚህአስተሳሰብሊቃኝይገባል፡፡በ Campbell ከተጠቀሱት ተግባራት ሁለተኛ ላይ የሰፈረው ይበልጥ በዚህ ጥናት ይህ አቀራረብ እንዲመረጥ አድርጎታል፡፡ስለሆነምለጥናቱ የመረጃመተንተኛብዝሃ-ግብርአቀራረብተስማሚሆኖበመገኘቱጥቅምላይውሏል፡፡

## 3.2 የጥናቱ ዘዴ

በዚህ ክፍል ለጥናቱ ስራ የሚውሉ መረጃዎች በምን መልኩ እንደተሰበሰቡ፣ናሙናዎች እንዴት እንደተመረጡና መረጃዎች በምን መልኩ እንዴት ትንታኔ እንደተሰጠ በአጠቃላይ የምርምር ጥያቄዎችን አስተማማኝና ትክክለኛ በሆነ መንገድ ለመመለስ የሚያስችሉ ጉዳዮችና የጥናቱ አካሄድ ምን እንደ ሚመስል የሚታይበት ይሆናል፡፡

### 3.2.1የመረጃ ምንጭ

ጥናቱ የተሳካ ይሆን ዘንድ ቀዳማይና ካልዓይ የመረጃ ምንጮች ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡ በመሆኑም ቀዳማይ የመረጃ ምንጭ በመሆን ያገለገሉት ዝጎራ እና መርበብት የተሰኙት ልብወለድ መፃህፍት ሲሆኑ ካልዓይ የመረጃ ምንጭ በመሆን ያገለገሉት ደግሞ ለጥናቱ የሚጠቅሙየተለያዩመጻህፍት፣ጥናታዊ ፅሑፎች፣ ፣መጣጥፎችና ሂሳዊ ፅሑፎች ናቸው፡፡

### 3.2.2የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ

የመዛግብት ፍተሻ ዘዴ በፅሑፍ ያሉ መረጃዎችን ለመርመርና ለመፈተሽ ተመራጭ ዘዴ መሆኑን ያለው (2009፣196) ይገልጻል፡፡ በመሆኑም በዚህ ጥናት መረጃዎች የተሰበሰቡት በመዛግብት ወይም መፃህፍት ፍተሻ ሲሆን መረጃዎቹ የሚገኙት በተመረጡት ሁለት ልቦለዶች ውስጥ በመሆኑ በነዚህ መፃህፍት ላይ ጥልቅ ንባብበማድረግ ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑ ሚታዊ ባህርያት ያላቸው ሁነቶች(መረጃዎች)ተለቅመዋል፡፡

### 3.2.3የናሙና አመራረጥ

ጥናቱ ዓላማ ተኮር ንሞና(purposeful,purposive,judgment or judgmental sampling) ዘዴን የተከተለ ነው፡፡ በዚህ የንሞና ዘዴ ተመራማሪው ማንን መውሰድ እንዳለበት የሚወስነው ራሱ ነው፡፡ "እነዚህ በጥናቴ ውስጥ ቢካተቱ የዳበረ፣የጠለቀና የሰፋ መረጃ ይሰጡኛል"ከሚል ግላዊ ግምገማ በመነሳት ይመርጣቸዋል ያለው(2009፣136)፡፡ በመሆኑም ጥናቱ በዋናነት ይዞት የተነሳው በሚታዊ ባህሪያት የተቃኙ ሁነቶች ታሪክ ማስኬጃነት አበርክቶ በአማርኛ ረጅም ልቦለዶች ውስጥ የማሳየት ዓላማ ነው፡፡ ለዚህም አመቺ ናቸው ተብለው የታመነባቸው የአማርኛ ልቦለዶች የተመረጡ ሲሆን ሚታዊ ጉዳዮች በስፋት የቀረቡባቸው ልቦለዶች ናቸው፡፡ ናሙናዎቹም የሚት ተረክ ባህርያትን መሰረት በማድረግ በኢላማዊ የናሙና አመራረጥ ዘዴ ተመርጠዋል፡፡

### 3.2.4የመተንተኛ ስልት

ይህጥናትበቤተ-መፃህፍትየተወሰነዓይነታዊ(Qualitative)ጥናትሲሆን የመተንተኛስልቱደግሞ ገላጭ ፈካሪነው፡፡በመሆኑምየልቦለዶቹንታሪክ ብቻከተከተለየመጀመሪያምንባብበመቀጠልደጋግሞልቦለዶቹንበማንበብ፤የምርምርጥያቄውንመ ላሽሊሆኑየሚችሉአህዶችንከልቦለዶቹበማውጣት፤የተወሰዱትንለትንታኔአመችየሆኑቅንጣቶች/ አህዶች/ከሚቶሎጂያዊፅንሰሃሳቦችጋርበማናበብና "ብዝሃ-ግብር" አቀራረብን በመከተልየልቦለዶቹንአውድሳይለቅለመፈከርሞክሯል፡፡

ብዝሃ-ግብር የመፈከሪያ ዘዴ ሚቶልጂአንድዓይነትተግባርብቻ ያለው አለመሆኑን እና ከብዙ የእውቀት መስኮች ጋር የሚሳሳብ መሆኑን በመግለጥ ለመፈከር አመቺ ዘዴ ነው፡፡

ሚቶልጂየታሪክንሚናየሚጫወት፣ልማድን፣

የድርጊትውጤቶችንናተስፋንየሚያስተምር፣የማይገለፀውንየሚገልጽ፣በባህልየሚደረጉትን

ገሮችለምንእንደሚደረጉየሚገልጽመሆኑንየሚጠቁምነው፡፡እንዲሁምያንድንነገርየይገባ ኛልጥያቄንወይምባለመብትነትንሕጋዊለማድረግ፣ከየትእንደመጣንመልስለመስጠት፣ከሞ ትበኋላምንእንደምንሆንለመግለጽናለማዝናናት ተግባር የሚውል ነውSailors(2007፣15-22)

በማለትእንደገለጸውከልቦለዶቹ ውስጥ የተለቀሙት መረጃዎች በሥርዓት የተደራጁ ሲሆን ለትንተናው የሚሆኑ ንዑሳን ርዕሶችምየሁነቶችን ተለጣጣቂነት በመፍተር እና ጉዞ ትልም (ምንን እና ለምንን) በማሳየትበሚል በሁለት ተከፍለዋል፡፡ እነዚህ የመክፈያ መንገዶች ሁነቶቹን ከርዕሰ ጉዳዩ ጋር ለማገናኘት ይረዳል በሚል የግል ምልከታ የተደረጉ ናቸው፡፡

በትንታኔው ክፍል በልቦለዶቹ ውስጥ ከሚታዮ ሚታዊ ባህሪያት ካላቸው ሁነቶች ውስጥ የተወሰኑትንና በአጥኚዋ እይታ ጎልተዋል የተባሉትን ለይቶ በማወጣት ጉዞ ትልም እና የሁነቶች ተለጣጣቂነት በሚሉ ንዑሳን ርዕሶች በመክፈል በስነፅሁፋዊ ፋይዳቸው ወይም በልቦለዶቹ ታሪኮች ሰንሰለታዊ ትስስር ላይ ባበረከቱት አስተዋጽኦ ላይ ትንታኔ ተሰጥቷል፡፡ ጥናቱ በሚታዊና ስነጽሑፋዊ ባህርያት መነሻነት የተካሄደ ሲሆን በተለይም ሚታዊ ባህርያት ያላቸው ሁነቶች በልቦለዶቹ ውስጥ ላሉት ታሪኮች ቀጣይነት ካበረከቱት ስነጽሑፋዊ ፋይዳ አንጻር ተፈትሸዋል፡፡ ትንተናው የተካሄደው ልቦለዶቹን በተናጠል በማንሳት ሳይሆን አንዱን ከሌላው በማዛመድ እና በአንዱ ትንታኔ ቀሪው እንዲጎላ በማድረግ ነው፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት የመተንተኛ መነሻ ሃሳቦቹ ለሁለቱም ልቦለዶች የሚሆኑ በመሆናቸው አንዱን አንስቶ ጨርሶ በተመሳሳይ ምልከታ ዳግም ሌላኛውን ከማንሳት በአንድ እየቋጩ መሄዱ የተሻለ ስለሆነ ነው፡፡ ይበልጥ ደግሞ ልቦለዶቹ በተለያየ ጊዜና ርዕስ ይቅረቡ እንጂ መፃህፍቱ በታሪካቸው የተሳሰሩ ናቸው፡፡ (በዝጎራ የተጀመረ ታሪክ ቀጥሎ መርበብት ላይ ሲመጣ ነው የሚታየው) በመሆኑም አንድን ዋና ታሪክ በተለያየ መንገድና አገላለፅ እንዳስኬዱ የአንድ ግንድ የተለያዩ ቅርንጫፎች በመቁጠር ነው ታሪኩ ላይ ትኩረት የተደረገው፡፡ለዚህም በመርበብት ገፅ 314 ላይ "‹እንዴ!› አለና ‹ከዚህ በፊት ፈልጌ ወደዚህ ስፍራ ያመጣኋቸው ዕፆች!› አለ ተነስቶ እየቆመ፡፡ ‹እንዴት ነው ነገሩ አንድን ስራ ሁለቴ የሰራሁት? የምን አዙሪት ነው?›አለ በመደነቅ" የሚለው ከልቦለዱ ታሪክ ተመዞ የወጣው ሃሳብ ከላይ ለቀረበው ሃሳብ መረጋገጫው ነው፡፡ በመሆኑም የዚህ ጥናት ትኩረቱ የታሪኮች ትስስር ላይ የተመሰረተ የሚታዊ ሁነቶች ፋይዳን ማሳየት እንደመሆኑ

ቀዳሚው ታሪክ ዝጎራ ልቦለድ ላይ ስለሚገኝ የዝጎራ ልቦለድ ታሪክ ላይ የተመሰረተ ትንታኔ እየቀደመ የመርበብት እየተከተለ ትንተናው ተካሂዷል፡፡

# ምዕራፍ አራት

## የመረጃ ትንተና

Mann (1968) እንደሚገልጹት፣ ሚት የሕይወት መሰረት ነው፤ በጊዜ የማይገደብ ንድፍ፣ ከኢንቂው አዕምሮ ባህርያትን እያመነጨች ህይወት የምትጓዝበት ሀይማኖታዊ ቀመርም ነው፡፡ ሥነጽሑፍ ሰዋዊ ጉዳዮችን በጊዜና ቦታ ሳይገደብ በማንሳት አቅሙ የህይወት መሰረት የሆነውን ሚት ይሆነኝ ብሎም ይሁን ሳያስብ መንካቱም ይባል ማንሳቱ የማይቀር ጉዳይ ይሆናል፡፡

በሚት ትርጎማ ስሙ የከፍታው ጫፍ ላይ የሚጠራው Frazer(1920) የሰው ልጅ ሶስት የዕድገት ዘመናት (ages) እንዳሉት ይገልጻል (የአድባሬ ፣ የሐይማኖትና የሳይንስ ዘመናት)፡፡ የሳይንስ ዘመን ገና እየገባ እንደሆነም ያስረዳል፡፡ ይህ የሚት ብያኔ፣ ሚትን ከኬትመጣው፣ ከአድባሬ፣ ከሀይማኖትና ከሳይንስ ጋር ያሉትን ግንኙነቶች ለማጥናት መንገድ ከመክፈቱም በተጨማሪ፣ ሚት የጥንት ዘመንና ያልሰለጠነ ማህበረሰብ ጥናት ብቻ ተደርጎ እንዳይታይ ዐይን ይገልጣል፡፡

በዝጎራም ሆነ በመርበብት የተነሱት ታሪኮች የሀይማኖትና ሳይንስ ዘመን አዛንቀው የያዙ፣ ባሕልና ስልጣኔን የሚያሚግቱና በእነዚህ ጥንዳዊ ተቃርኖዎች መካከል የምትውተረተረውን ህይዎት ልዩ ልዩ መልኮች በሚትና ልቦለድ ተደጋግፎ የሚፈነትዉ ናቸው፡፡ በዚህ ጥናት የተተኮረው ቀደም ባሉት ክፍሎች ተደጋግሞ እንደተጠቆመው፣ በልቦለዶቹ ውስጥ የተሰገሰጉት ሚታዊ ሁነቶች ለልቦለዶቹ ታሪክ ያበረከቱትን አስተዋጽኦ መተንተን ስለሆነ ወደሱው እንለፍ፡፡

ወደ ትንተናው በቀጥታ ከመግባታችን በፊት ግን የሚተነተኑትን ልቦለዶች ታሪኮች በአጭሩ ማስተዋወቅ ተገቢ ስለሆነ እነሱን በማስቀደም ትንተናው ይከተላል፡፡

### 4.1የልቦለዶቹጭምቀ-ታሪክ

በሁለቱም ልቦለዶች ውስጥ የሚስተዋሉት ፍልጋዎች፣ ሳይንሳዊና መንፈሳዊ እውቀቶች ተሻርበው በሚታዊና ልቦለዳዊ ትረካዎች ማሂጃነት ፍሰታቸውን መቀጠላቸው መፃህፍቱን የሚያመሳስሏቸው ጉዳዮች ቢሆኑም፣ ከዚህ ውጭ ባሉት ባህርታቸው መጻሕፍቱ ራሳቸውን ችለው ሊቆሙ የሚችሉ ናቸው፡፡ ስለሆነም የሁለቱን ልቦለዶች አፅመታሪክ ለየብቻ ማየቱ ተገቢ ስለሆነ በሚከተለው መልኩ በየራሳቸው ቀርበዋል፡፡

### 4.1.1 የዝጎራ ረጅም ልቦለድ ጭምቅ-ታሪክ

*ታሪኩ የሚጀምረው በአንድ የዱባይ ሬስቶራንት ውስጥ በሲሳይና በሚስተር ራምዚ አንቶን የምሳ ላይ ጭውውት ሲሆን ሲሳይ ሙዚየሙን በመጎብኘት ላይ እያለ ድንገት ወደ ሀገር ቤት ለመመለስ መፈለጉ ከምን የመነጨ ድንገተኛ ሀሳብ እንደሆነ በቀረበለት የሚስተር አንቶን ጥያቄ መሰረት በሳይት 09 የጥናት ቡድኑ ከገጠመው የመጀመሪያው አስገራሚ ፈተና አንስቶ ከአባ መዝገበ ስላሴ እጅ ሶስት አይነት እፆችን ከሶስት ቦታዎች እንዲያመጣ የታዘዘበትን የብራና ወረቀት ተቀብሎ እስከተለያየበት፣ በብራናው ወረቀት ላይ ከአንድ የመፅሐፍ ቅዱስ ጥቅሥ ውጭ ሌላ ምንም የሚታይ ፅሑፍ እንዳልነበረበት፣ አባ ግን ተፅፏል ማለታቸው፣ በዚህ ምክንያትም በወቅቱ በሁኔታው መገረሙንና ግራ መጋባቱን፣እንዲሁም ተመልሶ ሄዶ ስለ ሁኔታው እንዳይጠይቃቸው እፆቹን ሳይዝ ተመልሶ መምጣት እንደማይችል በጥብቅ መታዘዙን፣ ትእዛዙን እንዳይፈፀም ደሞ መልክቱን አንብቦ ለመረዳት አለመቻሉን፣በቸልተኝነት ቢተወው ደግሞ የእድሜው ማጠር ከፍተኛ ጭንቀት ውስጥ ከቶት እንደነበር፣በዚህ ጭንቀት ውስጥ እያለ ወደ ዱባይ እንደመጣና በዱባይ ሙዚየም ውስጥ በመጎብኘት ላይ ሳለ ባዶ በሚመስለው ወረቀት ላይ ልዩ መብራ በማብራት ባዱ የሚመስለው ወረቀት በፅሑፍ የተሞላ መሆኑን ሲመለከት ወዲያው የራሱ የቤት ስራ ትዝ ብሎት ሳያስበው በድንገት ወደ ሀገር ቤት የመሄድ ፍላጎት እንዳደረበት ይነግረዋል፡፡ ሚ/ር ራምዚሲሳይን በንጋታው ወደ አገሩ ይሸኘዋል፡፡ሲሳይ ቤቱ እንደደረሰ የባዶውን ብራና ጽሑፍ ተጣድፎ ብራናው ላይ ሎሚ አፍስሶ በኤሌክትሪክ ሲያሞቀው ጽሑፉ ይወጣል፡፡ለጓደኛው ክብረ በዓልም በመደወል የሆነውን ነግሮት ለመገናኘት ይቀጣጠራሉ፡፡ሲገናኙም የብራናውን ምስጢር እንዴት እንደፈታው፣ዱባይ ዜጎቿን እንዴት አንደላቃ እንደያዘች፣ በአቡዳቢ ስላሳለፈው ጊዜ፣ ከሙዚየሙ ያገኘውን ፍንጭ ለመሞከር በፍጥነት ወደ ሀገሩ እንዴት እንደተመለሰ፣ ይተርክለታል፡፡ክብረ በዓልን የዕፆቹን ስም ያውቅ እንደሁ ሲጠይቀው እንደማያውቃቸው ይነግረዋል፡፡ ብራናውን እንደ ሰጡት እንደ አባ መዝገበ ስላሴ ምስጢር ደባቂ ሆንክብኝ ይለዋል፡፡ሲሳይ በስውር የተሰጠውን ምንነትና መገኛዎች እንዳወቀ ወደ ተባሉት ቦታዎች ደርሶ ዕፆቹን ለመሰብሰብ የአስር ቀን ረፍት ከመስሪያ ቤት ይወስዳል፡፡ ወደ ማህበረ ስላሴ ገዳም ከጓደኛው ክብረ በዓልና ለስራ ወደ አይከል ከሚሄደው ሌላኛው ጓደኛው ሽፈራው ጋር ጉዞ ይጀምራሉ፡፡ ከብዙ ውጣ ውረድ በኋላ ማህበረ ስላሴ ገዳም ደርሶ ንግስት ዘውዲቱ አሰርተው ስለነበረው የውሃ ማቆሪያ፣ ስለአጼ ቴዎድሮስ አጽም እዚያ ማረፍ በአንድ አባት ገለፃ ይደረግለታል፡፡ በገዳሙ*

ስለሚገኙ ጽዋት እየገሩት ሳለም  ከክረምት ይልቅ በበጋ ስለሚለመልመው እጸሲና ሲተርኩለት የሚፈልጋትን እጽ ያገኛል፡፡ ከእርሷ ቆርጠው የሰጡትን ይዞ ከገዳሙ በፍጥነት ይወጣል፡፡ ወደ ሁለተኛው እጽ መገኛ ወደ ጰንጤሌዎን ገዳም ጉዞ ይጀምራል፡፡ ስለሚያልፍባቸው ቦታዎችና ስለተከናወኑባቸው ታሪካዊ ክስተቶች ገለጻና አስተያየት እየሰጠ አክሱም ይገባል፡፡ከማህበረ ስላሴ የተላከውን እጣን ለአባ ተክለጽዮን አስረክቦ ወደ ጰንጤሌዎን ገዳም ያመራል፡፡ አባ ወልደ አረጋዊ ስለ አከባቢው ገለጻ እየሰጡት ስለ ገዳሙ የሚነገረውን አፈ ታሪክ ሲተርኩለት እዚያ ቦታ እንዲያመጣ  የተነገረውን እጸ ኀርመትን በአጋጣሚ ያገኛል፡፡በጠዋት እንደሚሰጡትና አብረውት ወደ ይምርሐነ ክርስቶስ ደብር እንደሚመለሱ ቃል ይገቡለታል፡፡ በጠዋት ወደ ላስታ ሲመለሱ ስለአድዋ ጦርነትና ስለ እርስ በእርስ ጦርነት እየጠረኩ ስለ ጎጥ ፖለቲካ እየተቹ ከትግራይ መሬት ወጥተው ሰቆጣ አዳራቸውን ያደርጋሉ፡፡የዋንኞችን ትዝታ እያነሱና በተራቆተው የመሬት ገጽ እያዘኑ ይምርሐነ ክርስቶስ ደብር ይደርሳሉ፡፡ ሲሳይ ገዳሙ ውስጥ እጹን ፍለጋው አታክቶት ወደ ሸለቆው ሲወርድ ይወድቃል፡፡ አባ ወልደ አረጋዊ ደርሰው ጸበል ሲረጩት እጹ ይገለጽለታል፡፡ከእሱ ይዞ ፈረንሲያዊው ሸምበር በኢትዮጵያ የእጽዋት ሀብት ላይ ስለፈጸመው ደባ እየ ተረኩለት ወደ ደብረታቦር ይጓዛሉ፡፡ እርሳቸውን እናቲቱ ማርያም ትቷቸው ወደ ህብረት ሆቴል ያመራል፡፡ ህብረት ሆቴል ሲደርስ ከጓደኛው ሽፈራው ጋር ይገናኛሉ፡፡ ሽፈራው መተማ ሄድኩ ብሎ አሁን ደብረታቦር የተገኘበትን ምስጢር እንዲነግረው ይጠይቀዋል፡፡ በታሪኩ ርዝመት የማይሰለች ከሆነ እንደሚነግረው ቃል ይገባለትና ቡና ይዘው ታሪኩን ይጀምርለታል፡፡ፈረንሳይ ውስጥ ዶ/ር ሀሮልድን ሲያገኘው “የቤተ ክርስቲያኑን ደን ምስጢር ደረስክበት ወይ?” ብለው እንደጠየቁትና እንዳልሄደ ሲነግራቸው ወቅሰው እንዲሄድ እንዳበረታቱ ይነግረዋል፡፡ ሽፈራው በምን ምክንያት እንደወቀሱት ሲጠይቀው በአብያተ ክርስቲያናትና ገዳማት ደኖች ላይ ጥናት የሚያደርገው ቡድን ሳይት 09 ሲደርስ ያጋጠመውን እንግዳ ነገር ይነግረዋል፡፡ አቅጣጫ ጠቋሚ ኮምፓስ መዛባቱ፣ገመድ ጎታቹ ተዝለፍልፎ መውደቁና ሊሰሩ ካሰቡት በብዙ ርቀት መሳሳታቸውን ሲረዱ ቦታው አንዳች ችግር እንዳለበት ተረድተው ለጊዜው ለቀው መውጣታቸውን ይነግረዋል፡፡ ሲሳይ ተመልሶ በተረጋጋ ሁኔታ እንዲመረምረው ተስማምተው አሜሪካውያኑ ወደ ሀገራቸው መመለሳቸውን ይህ ከሆነ ከአንድ አመት ተኩል በኋላ ከዶ/ር ሀሮልድ ጋር ተገናኝተው ሲጠይቁት ምንም እንዳላደረገ ሲነግራቸው እንደሆነ የወቀሱት ይነግረዋል ሲሳይ ከፈረንሳይ ከተመለሰ ከሁለት አመት በኋላ ወደ ሳይት 09 ሄዶ የአፈር ናሙና ወስዶ አዲስ

አበባ ሲያስመረምር የብረት ክምችት እንደሌለበት እንደተረዳና ከብርሃን ሞገድ ውጭ በድምጽ ሞገድ እይታን የሚፈጥር ሳይንሳዊ መሳሪያ  በዶ/ር ሀሮልድ እርዳታ ከውጭ በትውስት አስመጥቶ በቦታው ተገኝቶ ሲሞክር በመጀመሪያ ነጭ ጉም የሚመስል ነገር ካሳየው በኋላ አልሰራ እንዳለ ይገልጽለታል፡፡በእልህ ወደ ፊት ሊራመድ ሲል ከኋላው አንዳች ነገር ሲነካው ተዝለፍልፎ መውደቁንና ሲነቃ ከአባ መዝገበ ስላሴ እቃ ቤት እራሱን እንዳገኘ ይተርክለታል፡፡ ማን እንዳመጣው አባን ሲጠይቅ መልስ እንዳልሰጡትና ከዚያ በኋላ የዛን ታላቅ ደን ምስጢር በራሱ ጥበብና እውቀት ኃይልና ድፍረት ሊመረምረው እንደማይችል አምኖ አባ ምስጢሩን እንዲነግሩት እንደተማጸናቸው ይነግረዋል፡፡እርሱ ወደ ባህርዳር እርሳቸው ወደ ገቢያ አብረው እየሄዱ መለያያቸው ሲደርስ የቦታውን ምስጢር ለማወቅ ከሚፈቅዱት መልእክት እንደያዙለት ነግረው ከደረት ኪሳቸው ውስጥ ብራና አውጥተው እንደሰጡትና የታዘዙትን ሦስት የምስጢር ማወቂያ እጾች ሳይዝ ወደዚያ ቤተክርስቲያን እንዳመለስ እንዳስጠነቀቁት ይነግረዋል፡፡ ሺፈራውም እጾቹን ማግኘት አለማግኘቱን ሲጠይቀው ትዕዛዙ በምስጢር መጻፉንና አቡዳቢ ሙዚየም ባገኘው ፍንጭ ወደ መተማ መሄዱን፣ አሁን ሁሉንም አግኝቶ ወደ ቅዱሱ ቦታ እየመራ መሆኑን ይነግረዋል፡፡ ሽፈራው ሲሳይን ወደ ቦታው እንዲሄድ አበረታቶ ይሸኘዋል፡፡ ሲሳይ ወደዚህ ምስጢር መማነፍነፍ እንዴት እንደገባ እያሰላሰለ ወደ ቤተክርስቲያኑ ጉዞውን ይጀምራል፡፡ አባ መዝገበ ስላሴ ተቀብለውት ወደ ቤተልሄሙ ሄደው ከተመለሱ በኋላ በሚቀጥለው ቀን ረፋዱ ላይ መሳሪያዎቹን ይዞ የሞከረበት የቤተክርስቲያኑ ቅጥር አከባቢ እንዲገኝ ይነግሩታል፡፡ሲሳይም በተባለው ሰዓት የተባለው ስፍራ ላይ በመገኘት ያለፈውን ጊዜ በምልሰት እያሰበና በቦታው ተፈጥሯዊ ውበት እየተደመመ ሳለ ከዚህ በፊት እፆቹን ፍለጋ ሲንከራተት ያገኛቸው አባቶችና የልብ ጓደኛው ዶ/ር ክብረ በዓል ምንኩስናን ተቀብሎ ከአባቶች ጋር በመሆን ወደሱ ሲመጡ ይመለከታል፡፡በጓደኛው ሁኔታም በጣም ይገረማል፤ ይህ እንዴት ሊሆን ቻለ?በሚል እየጠየቀና እየተመለሰለት ባለበት ሁኔታ ግርማ ሞገሳቸው የከበደ ረዘም ያሉ አዛውንት መነኩሴ ከወደደኑ አከባቢ ብቅ ይላሉ አባ መዝገበ ስላሴ ጠጋ ብለው በፍጹም ስውራኑና በሚታዩት መነኮሳት መካከል ያሉ አባት መሆናቸውን ለሲሳይ ነግረዉ  ማወቅ የሚፈልገውን ነገር እንዲጠይቃቸው ይነግሩታል፡፡ ትልቁ አባት ሲሳይ ፈልጎ ያመጣቸውን እፆች ቅርንጫፎችን ይዘዋቸዋል፤ እፆቹ ግን ሲሳይ ጋር በነበሩበት ጊዜ እንደጠወለጉት ሳይሆን ፍፁም የለመለሙ ነበሩ፡፡ ሁሉም ሲመለከቷቸው  በአክብሮት እራሳቸውን ዝቅ በማድረግ መስቀላቸውን ከተሳለሙ  በኋላ፣ ታላቁ አባት ቃላቸውን አክብሮ

*እያቹን ይዞ በመምጣቱ ሲሳይን ካመሰገኑት በኋላ በተሰጠን እያንዳንዷ ቀን እንዴት መኖር እንደሚገባ፣ ኢትጵያዊነት ማለት ምን ማለት እንደሆነ፣ እውቀትን እንዴት መጠቀም እንደሚገባ፣ ተመራማሪ ማለት የሁሉንም ምስጢር የሚፈታ ማለት እንዳልሆነ፣ በምዕራቡ ዓለም እውቀት ብቻ ሁሉም ምስጢር የሚደረስበትና የሚፈታ  አለመሆኑን፣ በሀገር ቤት እንደዘበት ቸል የተባለ እውቀት መኖሩን፣ ሌላውን ለመምሰል ከመጣር ይልቅ እራስን መስሎ ማደግ የተሻለ እንደሆነ፣ ወዘተ. መልእክቶችን ከተናገሩ በኋላ  ያየውንና የሆነውን"የተናቀውንና የተረሳውን ጥበባችንን የሚፈልገው ትውልድ እስከሚመጣ ድረስ በእምነት አደራችንን  በአርምሞ የምንጠብቅበት ስፍራ ነውና ከዚህ በላይ አትድፈረው"ብለው ይመክሩታል፡፡ ሲሳይ በስሜት ላቀረበው "የከናንተ ጋር ልኑር?" ጥያቄ አሁን እሱ ባለበት ሁኔታ መሆን እንደማይችል ነግረውት፣ ቦታው የድል ፈላጊዎች ሳይሆን የድል አድራጊዎች መሆኑን ይነግሩታል፡፡ እያቹን ፈልጎ እንዲያመጣ  የተደረገበት ብርቱ ምስጢር እንደሆነና ወደፊት  ወንድሙ  አባ መዓዛ ቅዱሳን እስኪነግሩት በልቡ እንዲጠብቀውና በእምነቱና በትጋቱ ልክ የስራ ድርሻ እንደሚኖረው  ነግረውትና ባርከውት በምርኩዛቸው ሲነኩት ብዥ ይልበታል፡፡ሲነቃም ማግዳሊና ሲራመድ ካየችው ዛፍ ስር ራሱን ያገኛል፡፡ ከራስጌው ያገኘውን የተጠቀለለ ብራና ገልጦ ሲያነብ "ይህ ተራራ የፀሎትና የአርምሞ እንጂ የግርግርና የወረት አይደለምና ስሙን አትግለጠው" ይላል፡፡ ትእዛዛቸውን እንደሚጠብቅ ለራሱ ቃል ሲገባ ታሪኩ ይደመደማል፡፡*

### 4.1.2 የመርበብት ረጅም ልቦለድ ጭምቀ-ታሪክ

*ሲሳይ የወዳጁን የሚስተር ሮቤርቶን ግብዣ ተቀብሎ ወደ ሮም በሚያደርገው ጉዞ ታሪኩ የሚጀምር ሲሆን፣ ሲሳይና ሮቤርቶ የተዋወቁት ሲሳይ በሮቤርቶ ድርጅት ውስጥ ተቀጥሮ በሚሰራበት ወቅት ነው፡፡በስራ አጋጣሚ የጀመሩት ትውውቅ እያደገ ሄዶ የተቀራረቡ ወዳጆች መሆን ችለዋል፡፡በዚህ ምክንያት ነውሲሳይ ወደ ጣሊያን  ሲስሊ በመምጣት የእረፍት ጊዜውን እንዲያሳልፍ የተጋበዘው፡፡ በዛም ከሚስተር እስጢፋኖ ጋር ይተዋወቃል፡፡ በሚስተር እስጢፋኖመኖሪያ ቤት መልካም የሆነ ግብዣ ከተደረገለት በኋላ የሚወያዩት ነገር እንዳለ ተናግረው ሲሳይን ወደ ቤተ መጽሐፋቸው ይዘዉት በሚሄድ በወጣትነት ዘመናቸው  ጣሊያን (ኢትዮጵያን በወረረችበት ወቅት) በምህንድስና ሙያ ኢትዮጵያ መተው  በሙያቸው ሲያገለግሉ እንደነበር ይነግሩታል፡፡ ኢትዮጵያ እያሉ አንድ ቀን ከሰዓት በኋላ በርከት ያሉ የጣሊያን ወታደሮችና ሲቪሎች በደፈጣ ውጊያ ምክንያት*

አደጋ ደርሶባቸው እርሳቸው ወዳሉበት ካምፕ እንደመጡ በመካከላቸውም አንድ ካቶሊካዊ ቄስ እንደ ነበረና ካቶሊካዊው ቄስ ይድን ዘንድ ከፍተኛ ጥረት ቢያደርጉም ጥረታቸው እንዳልተሳካና ቄሱም እንደ ማይተርፍ ሲረዳ ለብቻ አስጥርቶ ሀዘኑ ከባድ መሆኑን እንደነገራቸው ሀዘኑን ያከበደው ግን ለመሞት መቃረቡ ሳይሆን በጴጥሮስ መንበር የተሰየመችውን የቫቲካን ቤተክርስቲያን ክብር የቅዱሱን ፓፕ አደራ መወጣት ባለመቻሉ መሆኑን ተናግሮ በመጨረሻም "ከቦርሳዬ ውስጥ ያለውን ሳጥን አውጥተህ ውስጡ ያለውን መልእክት አንብበህ ፈፅመው" የሚል አደራን ተናግሮ ህይወቱ እንዳለፈ ይነግሩታል፡፡ እሳቸውም አደራውን ተቀብለው ለብዙ ጊዜ በግል የህይወት እሩጫ ምክንያት ዘንግተው ሳጥኑን ለ70 ዓመት በቤታቸው ውስጥ እንዳቆዩትናኋላ ላይ ይህንን የአደራ ሳጥን ከፍተው ሲመለከቱት ኢትዮጵያዊ ጉዳይ እንዳለውና ሳጥኑም ለባለቤቶቹ (ለኢትዮጵያዊያን) መሰጠት እንዳለበትና ምስጢሩን እራሳቸው ባለቤቶቹ እንዲፈቱት በማሰብና ለዚህ አደራ ታማኝ የሆነ ሰው በማፈላለግ ላይ ባሉበት ወቅት በሮቤርቶ አማካኝነት እሱን ማግኘት መቻላቸውን ይነግረዉ.ትከታላቅ አደራ ጋርምሳጥኑን ይሰጡታል፡፡ ልጃቸው ናታንያ ከአባቷ የተለየ አላማን ይዛ አባቷ ሳጥኑን እንዲሰጧት ብዙ ጊዜ ተማፅናቸው ነበርና ለሷ ከልክለው ለሲሳይ እንደሰጡት ስታውቅ እጅጉን ተበሳጨች፤ ተበሳጭታም አልቀረች ሳጥኑ ከጣሊያን ሳይወጣ ከሲሳይ ነጥቃ ለመውሰድ የተለያዩ ሙከራዎችን አደረገች፡፡ ነገር ግን ሲሳይ እቤታቸው በሂደበት ወቅት በናታንያ ፊትና አኳኋን ያነበበው ነገር ይህ ነገር ሊፈጠር እንደሚችል አስቀድሞ እንዲገምት አስችሎት ነበርና ዋናውን ጉዳይ በፖስታ ቤት በኩል በጥበብ ልኮት ሳጥኑን በውስጡ ከነበሩት ከአቅጣጫ አመላካች መሳሪያዎች ጋር በመተው በሻንጣው ከቶት ነበር፤ ናታንያም በዘረጋች የሴራ መረብ ይህንን ሳጥ ካለ ዋናው ጉዳይ በእጇ ለማስገባት ችላለች፡፡ ሲሳይ መረጃውን ከፖስታ ቤት ከተቀበለ በኋላ ውስጡ ምን እንዳለ ለማወቅ ጥረት ማድረግ ጀመረ፡፡ ከብዙ ጥረት በኋላ መልዕክቱን ለመረዳት ቻለ፡፡ መልእክቱም "ብዙ የተሰቃየሁበትን በኢትዮጵያ የተደበቀውን ሀያል ነገር እንድታገኘው እለምንሀለሁ፤ ባገኘኸው ጊዜም ሁላችን ለጓጓንለት ተልዕኮ ማስፈጸሚያ ታውለዋለህ፡፡በዚህም ቅድስቲቷን ቫቲካንንና ታላቋን ኢጣያን ታስከብራለህ፡፡ ምልክቶቹንና ማኅተሙን በካርታው ላይ በማስተዋል ተከተል፡፡ባገኘኸው ጊዜም ለራስህ ተጠንቀቅ!" የሚል ነበር ቀጥሎም ካርታውና ምልክቶቹን መመልከት ጀመረ፡፡ በካርታው ላይ በጉልህ የሚታየው የልብ ቅርፅ ያለው ካርታ ነው፤ የልቡ የታችኛው ሹል ጫፍ ላይ ጅራት የመሰለ መስመር ተቀጥሎለታል፤ በልቡ የላየኛው ስርጉድ ጠርዝ ላይ ደቀቅ ያሉ ምልክቶች

ይታያሉ በተጨማሪም የእንግሊዘኛ ፊደላት ኤክስ እና ፒ(XP) ተጣምረው ከልብ ቅርፁ መስመር ውጭ ተነቅሰዋል፡፡ የኤክስ እና ፒ ጥምረት የጥንት ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ምልክት እንደሆነ ከኢንተርኔት ባገኘው መረጃ መሰረት መረዳት ችሏል፡፡ቀደም ሲል ሳጥኑ ከመወሰዱ በፊት በውስጡ የአቅጣጫ አመላካች ኮምፓስ፣ማስመሪያና አጉሊ ሌንስ መኖራቸውን አስታውሶ ደቃቆቹ ምልክቶች ቁምነገር ያላቸው መሆኑንና ካርታው አቅጣጫና ርቀት ያለው መሆኑን ገመተ፡፡ መረጃዎቹን በአግባቡ በጥንቃቄ ከመረመረ በኋላ አደራውን ለመወጣት ወዲህም ሚስጥሩን ለማወቅ በብዙ ደከመ ነገር ግን በልፋቱ ልክ ምስጢሩን በቀላሉ ማወቅ አልቻለም፡፡እንደ አጋጣሚ አንድ እለት በባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ በተዘጋጀው ዐለምአቀፍ የምርምር ጉባኤ ላይ እየታሳተፈ ሳለ በአንድ ቤልጄማዊ ፕሮፌሰር አባይን አስመልክቶ ከተደረገ ገለፃ የሚስጥሩን መፍቻ የመጀመሪያ ምዕራፍ አገኘ፡፡ ፕሮፌሰሩ ገለፃቸውን ከማጠናቀቃቸው በፊት የተዘረጋውን ካርታ እያመለከቱ “so lake Tana with its famous heart shape/” በማለት የጣና ሐይቅ ልብ ቅርፅ እንዳለው ሲገልፁ በካርታው ላይ ያለው የልብ ቅርፅ ትዝ አለው፡፡ ጊዜ ሳያጠፋ ቀጥታ ወደ ሰሜናዊ የጣና ዳርቻ ወደ ጎርጎራ ጉዞውን አደረገ፡፡ በመረጃው መሰረት ጉዳዩ ከካቶሊኮች ጋር እንደ ሚያያዝ ስለተረዳ የካቶሊኮች አሻራ ያለባቸውን ስፍራዎች ማሰሱን ተያያዘው፡፡ ወደ ጥንታዊቷ ደብረ ሲና ገዳም በማምራትም የመሶለኒ ሀውልትን ተመለከተ፡፡ነገር ግን ከቆመ ድንጋይ ውጭ ይህ ነው የሚባል ለመጣበት ጉዳይ የሚጠቅመውን ነገር ማግኘት አልቻለም፡፡ከንቱ ድካም በመሆኑ ይበሳጫል፡፡ መበሳጨቱን ያየው አስጎብኚ ለምን ቅር እንዳለው ይጠይቀዋል፡፡ ሲሳይም አመጣጡ የካቶሊካውያን ቤተክርስቲያን ወይም የመቃብር ስፍራ እንዳለ ለመመልከት እንደ ነበር ይነግረዋል፡፡አስጎብኚውም አሁን የፈራረሰ ቢሆንም የካቶሊኮች የነበረ የቅድስት ማርያም ቤተክርስቲያን በአካባቢው መኖሩን ይጠቁመዋል፡፡ሲሳይም ወደ ስፍፈራው እንዲወስደው ይጠይቀዋል ተያይዘውም ወደ ስፍራው(አሮጌው ጎርጎራ) ይጓዛሉ፡፡ በዛም በአከባቢው ነዋሪ ከሆኑት አስጎብኚ አቶ አወቀ ጋር ይገናኛል አብረውም ወደ ስፍራው ይዘልቃሉ፡፡ በስፍራውም በካርታው ላይ የሰፈሩትን ነገሮች ይመለከታል፡፡የXP ምልክቶችንም በድንጋይ ላይ በተለያዩ ቀለማት ቀልመው ይመለከታል፡፡ሚስጥሩ እዚህ ስፍራ እንደሚገኝ ይገምታል በመቀጠልም ፍለጋውን ከሁለቱ ሰዎች እይታ እያራቀ ማከናወን ይጀምራል ከብዙ ጥረት በኋላ በሐይቁ ውስጥ ከብረት ችንካር ጋር የታሰረ አንድ አነስተኛ ሳጥን ያገኛል፡፡ሳጥኑንም ይዞ ወደ ባህርዳር በመመለስ ሳጥኑን በቤቱ ውስጥ ያኖረዋል፡፡ ሳጥኑ ውስጥ ያለው ነገር ምን አልባት አደጋ ሊያደርስ የሚችል ነገር ሊሆን

ይችላል በሚል ስጋት ሳጥኑን ሣይከፈት ለማየት ይረዳው ዘንድ የኤክስሬይ ማሽን ማፈላለግ ይጀምራል፡፡ በዚህ መሃል ሚስቱ ሳይታሰብ በጠና ትታመማለች ሀኪም ቤት ወስዶ ሲያሳክማት ምንም በሽታ የለባትም፡፡ እሷ ግን ህመሙ ይጠናባታል በተለይ ለሊት ላይ እንዲሁ ስታስል ታድራለች፡፡አንድ ቀን ለሊት ላይ አፍጥጦ የሚመለከታትን የሰው አምሳል በመኝታ ቤት ውስጥ ትመለከታለች፡፡በጣም ደንግጣ እያመተበች ሰላም ለኪን እየደገመች ስትጸልይ ምስሉ ወደ ፍዝ ስዕል እየተቀየረ በመምጣት በኋላም በለሊት ወፍ አምሳል እንደ ዳንቴል እየተተረተረ በመስኮት ወቶ ሲሄድ ትመለከታለች፡፡ሲነጋም የንስሀ አባቷን በማስጠራት የሆነውን ሁሉ ነገረቻቸው፡፡እርሳቸውም “አይዞሽ ይህ የክይሲው ፈተና ነው ትድኛለሽ” በማለት ለሶስት ቀን አከታትለው አጠመቋት፡፡ እየተሻላትም መጣ፡፡ሲሳይም ጉዳዩ ከሳጥኑ ጋር እንደሚያያዝ ቢያስብም ንሰሀ አባቱ በቤት ውስጥ አምጥቶ ያሥቀመጠው ለየት ያለ ነገር እንዳለ ሲጠይቁት “ምንም የለም” ሲል ደበቃቸው፡፡ በሳጥኑ ውስጥ ያለውን ነገር ለመመልከት የኤክስሬይ ማሽን ወዳለው አንድ ባለሆቴል ወዳጁ ዘንድ በመሄድ ማሽኑን ለመጠቀም ጠይቆ ፍቃድ በማግኘቱ ሳጥኑን በማሽኑ ውስጥ በማስገባት መመልከት ይጀምራል፡፡በሳጥኑ ውስጥ የተመለከተው ነገር ከዚህ በፊት ሊኖር ይችላል ብሎ ከገመተው ነገር በጣም የራቀና እጅግ አስፈሪ ነበር፡፡ሳጥኑ በሁለት ክፍል የተከፈለ ሲሆን በአንደኛው ክፍል አንድ መጽሐፍና የሸንኮራ ጉማጅ የመሰለ እንጨት ሲታይ በሌላኛው ክፍል ደግሞ አንዴ ባዶ እንዴ ደግሞ በማህፀን ውስጥ ያለ ህፃን የሚመስል ነገር እጥፍጥፍ ብሎ ተኝቶ ይታያል፡፡ ሲሳይም ባየው ነገር እጅጉን በመደንገጥ የሚስቱ ህመም በቀጥታ ከዚህ ጋር እንደሚገናኝ በማሰብ ሌላ ችግር ውስጥ ሳይገባ ሳጥኑን ከቤቱ ማውጣት እንዳለበት በመወሰን ወደ ንሰሀ አባቱ በመሄድ በባለፈው መዋሸቱንናና እስካሁን የሆነውን ሁሉ አንድ በአንድ ነገራቸው፡፡እሳቸውም በጥሞና ካዳመጡት በኋላ ሳጥኑን ይዞ ወደ ቤት መመለስ እንደሌለበት ነግረውት ይህንን ጉዳይ ይበልጥ ወደ ሚያውቁት ሊቀጠበብት አስተርዓየ ዘንድ መልእክት ጽፈው ይልኩታል፡፡ ሲሳይም እንደታዘዘው ሊቀጠበብት አስተርዓየ ጋር በመሄድ የመጣበትን ጉደይ በዝርዝር ይነገራቸዋል፡፡በጥሞና ካዳመጡት በኋላ ሲሳይን በዕህፈት ቤታቸው አስቀምጠውት ወደ ጓሮ በመሄድ ድጋም እየደገሙ ከአንድ ብሳና ስር የበቀለች እፅ ይዘው በመመለስ ሲሳይን የሆነ የሚያሥፈራ ነገር ቢመለከት ችግር ላይ የሚጥል እንዳልሆነና መፍራት እንደሌለበት ነግረውት ሳጥኑን እንዲከፍተውያዙታል፡፡ ሲሳይም በእሽታ ከሱ የማትለየውን የመስክ ሴንጢ አውጥቶ ዙሪያውን ሰቅስቆ በአንድ ጎን መክፈት ሲጀምር ድንገት ጥቁር እባብ ሽር ብሎ ወጣና በእግሩ ስር አቋርጦ ወደ ውጭ ተፈተለከ፡፡

ሲሳይም በድንጋጤ ሳጥኑን ወርውሮ ቆመ፡፡ ሊቀ ጠበብትም "አይዞህ አትደንግጥ የእውነት አባብ አይደለም በምትሀት ሊያስደነግጥህ ነው" አሉት፡፡ሳጥኑም ሲከፈት በአንደኛው ክፍል መፅሐፍና አንድ ቅርፊት የሌለው እፅ ያለ ሲሆን ሌለኛው ክፍል ግን ባዶ ነበር፡፡ሊቀጠበብትም መፅሐፉን ከሲሳይ እጅ ተቀብለው እያገላበጡ መመልከት ጀመሩ መፅሐፉ በግዕዝ ቋንቋ የተፃፈ ቢሆንም በተጨማሪ በርካታ የዕብራይስጥና የዐረበኛ ቃላትን ይዟል፡፡ ስለ ሊቀጠበብት አስተርዓየ ያለፈ የህይወት ታሪክ፣ ስለ መፅሐፉ ምንነት፣አጠቃቀም፣አገልግሎት ፣ስለ እፁና ተያያዥ ታሪኮች በስፋት ከተጨዋወቱ በኋላ ይህ ነገር ከእርሱ ዘንድ መቆየት እንደሌለበትና ጠንካራ አባቶች ወዳሉበት ጋዳም ወስዶ እንዲሰጥ ያሳሥቡታል፡፡ ሲሳይም ከዚህ በፊት የሚያውቀው ገዳም እንዳለና ወደዛ እንደሚወስደው ነግሯቸው ይሄዳል፡፡ በማግስቱ ወደ ሳይት 09 (መካነ ህርመት) ጉዞውን አደረገ፡፡ በጉዞ ላይ እያለ ሊቀ ጠበብት ጋር የነገሩትን የመፅሐፉንና የእፁን አገልግሎት በተግባር ለመሞከር (ለ49 ጊዜ ድጋሙን በመድገም ሰይጣንን ጠርቶ በማናገር) የተለያዩ ተግባራትን የሰይጣናት አለቃ ሩሙኤል እንዲያከናውን አስደርጎትና በምን እና እንዴት ለብዙ (350) ዓመታትከሐይቁ ስር እንደቆየ፣ማን እንደዚህ እንዳደረገ እንዲናዘዝ አድርጎት ሲያበቃ ወደ ገዳሙ ዘለቀ፡፡ገዳሙ አቅራቢያ ባለው ሜዳ ላይ ሲደርስም አመጣጡ ከየት እንደሆነ የማይታወቅ የኡ..ኡ..ኡ...ታ ድምፅ መሰማት ይጀምራል፡፡የአካባቢው ሰዎችም በሰሙት ጩኸት በመደናገጥ ወደ ስፍራው በመትመም ጩኸቱ የማን እና እንዴት እንደሆነ ለማረጋጋጥ እርስ በእርስ መጠያየቅ ጀመሩ፡፡ ነገር ግን፤ "ኡ.ኡ.ኡ. አስጥሉኝ" የሚል የጩኸት ድምፅ እንጂ ከየትና እንዴት እንደሆነ ማወቅ አልቻሉም፡፡ "ምን ጉድ ነው" እያለ አገሬው ሲገረም ከመሀል አንዱ "ይህ ነገር ጋኔን ነው "ሲሉ አንዲት አሮጊት ደሞ "የለም ቆሌ ነው" አሉ፡፡ጥይት በመተኮስ ጩኸቱ ፀጥ እንዲል አደረጉት፡፡በዚህ መሀል አባ መዝገበ ስላሴ ከደኑ ውስጥ ብቅ በማለት"አይዟችሁ ቀላል ነው፡፡" በማለትህዝቡን ሲያረጋጉ ሁሉም እርሳቸውን ሲያዩተረጋጉ፡፡ አባም ፀልየውና ባርከው ህዝቡን ከሸኙ በኋላ ከድንዛዜው ወዳልነቃው ሲሳይ ዘወር ብለው "ህይለ ጊዮርጊስ አንተ ጉደኛ "ብለው አቅፈው ከሳሙት በኋላ አይዞህ ብለውት ወደ ውስጥ ይዘውት ዘለቁ፡፡ወደ ቀኝ በመታጠፍም ወደ ትልቁ የሎል ዛፍ አመሩ፡፡ ከዛፉ ስርም ትልቁ አባት በሌሎች አባቶች ግራና ቀኝ ተከበው ፀሎት እያደረጉ ነበር፡፡ሲሳይም ሳጥኑን ከአባቶች ፊት አስቀምጦ የትልቁን አባት ቡራኬ ተቀበለ፡፡ የተጀመረው ጸሎት ለግማሽ ሰዓት ያህል ቀጥሎ ከቆየ በኋላ ሳጥኑ በአባ መዝገበ ስላሴ እንዲከፈት ተደረገ፡፡ ትልቁ አባት በበትረ መስቀላቸው አማተቡና ከመሬት አፈር

ዘግነው እንደመርጨት ሲያደርጉ እንደ ጭስ ትጉልል በማለት ከሳጥኑ ወጥቶ ትልቅ ቀንድ ያለው አስፈሪ ዘንዶ መስሎ ቆመ፤ አካባቢውን እንደ መገላመጥ አለና ከአስፈሪ ድምጽ ጋር የእሳት ነበልባል ካፉ ለቀቀ፡፡ታላቁ አባት በድጋሚ በመስቀላቸው ሲያማትቡበት ተቀየረና ራሙኤል እጅና እግሩ በሰንሰለት በታሰረ ሰው አምሳል ቆመ፡፡ድጋሚ ሲያማትቡበት ይጨስ ጀመር፡፡እጅግ የሚያስጠላ ጠረንምበአካባቢው ላይ ለቀቀ፤ አከባቢው ቀረና፤ ደግመው ሲያማትቡበትም መለፍለፍ ጀመረ፡፡እንዳይሰቃይ ይለምንና የፈለጉትን እና ያዘዙትን ሁሉ ሊፈፅም ቃል እንደሚገባ በብዙ ተማፀናቸው፡፡ነገር ግን ታላቁ አባት "የአምላካችን የጸሐዬ ጽድቅ ኢየሱስ ክርስቶስ የፍርድ ቀን እስክትደርስ ወደ ጥልቁ ጨለማ በርባሮስ ትወርዳለህ፡፡በዚያ ማንንም እንዳታስት ታስረህ ትኖራለህ!!!"አሉና በትረ መስቀላቸውን ሶስት ጊዜ ከፍ ዝቅ አድርገው እርሱ ከቆመበት አንጻር ወደ መሬት ሲያመለክቱ ድንገት መሬቱ ተከፈተ፤ ዋይ..ዋይ..ዋይ ብሎ እየ ጮሀ ቁልቁል ሲወርድ ኩኩኩ…የሚል ገደል ሲናድ የሚሰማ አስፈሪ ድምፅ ተሰማ፡፡መሬቱ ተናወጠ ፤ ዛፎቹም ግራና ቀኝ ተወዛወዙ፤ ከሲሳይ በስተቀረ የፈራና የደነገጠ አልነበረም፡፡ታላቁ አባት ወደ ፊት ራመድ አሉና አባ መዝገበ ስላሴ ከሳጥኑ ውስጥ እፁን እንዲያወጡና መፅሐፉን ግን ሳጥኑ ውስጥ ዘግተው ከጉድጓዱ እንዲጥሉት ነገሯቸው፡፡አባም እንደተባሉት አደረጉ፤ ታላቁ አባት በመስቀላቸው የጉድጓዱን ጫፍ ሲነኩት ጉድጓዱ ከመቅፅበት ተደፈነና መሬቱ ታተመ፡፡ በእግራቸው መታመታ አድርገው በፀሎት አሳረጉ፡፡ወደ አባ መዝገበ ስላሴ ዘወር ብለውም ፍትሐት ዘወልድን፣መፅሐፈ ኪዳንን እና ትምርተ ኅቡዓትን እየደገሙ ለሦሥት ቀን እንዲያጠምቁትና እሱም እንዲፀልይ ተናግረውና አሳልመው ወደ ደኑ ሔዱ፡፡ሲሳይ መካነ ኀርመት በሄደ በሁለተኛው ቀን ከአባ መዝገበስላሴ ጸሎት መጽሐፍ ጎን ከሳጥኑ ውስጥ ያገኘውን እጽ(እፀ ምኩናን) ሲመለከተው ከዚህ በፊት ፈልጎ ወደ እዚህ ስፍራ ያመጣቸው እፆች በአንድ ተጣብቀውና ተቀርፀው መሰራታቸውን አስተውሎ ተገርሞ እንዴት አንድ ነገርን ሁለቴ ደግሞ ሊሰራ እንደቻለ ሲናገር የሰሙት አባመዝገበስላሴ የህይወትን አዙሪትነት በማስረጃ አስደግፈው በደንብ አብራርተው ይገልጹለታል፡፡በሦስተኛው ቀን ሲሳይ አባመዝገበ ስላሴ ተሰናብቶ ወደ ቤቱ ሲመለስ ሰይጣን ሰርቶት የነበረው (ራሙኤል በአየር የሞላው ጎማ ተንፍሶ፣ተክሎት የነበረው የዶንጋ ዛፍ ከላይ እስከታች ደርቆ) ነገር ሁሉ ከንቱ ሆኖ ያገኘዋል፡፡ በመጨረሻም ስለ በደሉ ምህረት ይደረግለት ዘንድ እየጠየቀና እየተፀፀተ በለቅሶ ይጸልያል፡፡

## 4.2 ለልቦለዶቹ ታሪክ ማስኬጃነት የሚታዊ ሁነቶች ፋይዳ ትንተና

ሚታዊ ባህርያትያሏቸውን ሁነቶች ለልቦለድ ታሪክ ተለጣጣቂነት ከተጠቀሙ ልቦለዶች መካከል የአለማየሁ ዋሴ ዝጎራና መርበብት ልቦለዶች ተጠቃሾች ናቸው፡፡ የልቦለዶቹን ታሪኮች በአንድ የሚያስተሳስራቸው ጉዳዮች እንዳሉሆነው ግላዊ የታሪክ አወቃቀራቸው ሲታይ በዝጎራ፣ የሐይማኖታዊ ጉዳዮችና እውቀቶች ሳይንሱን መሞገት እንብርት ሆኖ ኢትዮጵያዊ ማንነት፣ የማወቅ ጉጉት፣ አንድን ነገር ለማግኘት የሚከፈል መስዋእትነት በአጎላማሽነት ተዋህደው የቀረቡ ሲሆን፣በመርበብት ደግሞ ኃይለ መንፈስና ኃይለ ዕፅን ማዕከል አድርጎስለ መገዛትና መታሰር፣ ስለ ኢትዮጵያና ጣልያን፣ ስለ እውነትና እውነት መሰል ድንቁርናእና ጦርነት በስፋትታትቷል፡፡እነዚህሁነታዊ የታሪክ ሂደቶች በሰመረ መልኩ ትስስር እንዲፈጥሩ ለማድረግሚታዊ ባህሪ ያላቸውሁነቶች በተገቢቦታቸውአግባባዊ በሆነ መልኩ በመምጣት ለትልም ማጠንከሪያነትና ለታሪክ ተለጣጣቂነት ደራሲው ተጠቅሞባቸዋል ለማለት ይቻላል፡፡ ምክንቱም ሚታዊ ሁነቶቹ በፈልጎ ማግኘት ሂደትየተዋቀሩበት ስልት ይህን ለማለት ያስደፍራል፡፡ በልቦለዶቹ ውስጥ የተነሱት የተለያዩ ሚታዊና ሐይማኖታዊ ታሪኮችም ዘመኑን በሚገልፅ መልኩ ተሰናስለው ቀርበዋል ለማለት ይቻላል፡፡

Huskinson"ሚት የእኛነታችንን ሀረግ ከዓለም ጋር ያስተሳሰርንበት እና ሰዉ የመሆንን ትርጉም የምንፈልግበት መንገድ ነው" ስትል እንደገለፀችው የሰው ልጅ እንደ ግለሰብም ሆነ እንደ ማህበረሰብ ሚትን ሲፈጥር የሚሄድበት መንገድ ራሱን ካለፈው ታሪካዊና መንፈሳዊ ስርዓት ጋር በማስተሳሰር ለእያንዳንዱ ታሪካዊ፣ ቁሳዊም ሆነ መንፈሳዊ ጉዳዮች ማጠየቂያ የሚሆኑ መልሶች ለመስራት መጣር ነው፡፡ በዚህም ሂደት ውስጥ እስከቻለው ድረስ በተጠየቀ ሂዶ የቀረውን(በተጠየቅ የማይሞላውን) በሚት አማካኝነት በምናብ በመሙላት ባዛኝ አእምሮውንና ልቡን ያሳርፋል፡፡ ደራሲው በስራዎቹ ውስጥ በተራኪው አንደበት አማካኝነት በልቦለዱ ታሪክ ውስጥ ያለፉ ሁነቶች ያለፉበት ሂደት ምን እንደሚመስል፣ መልስ የሌላቸው የሚመስሉ ጉዳዮች በሚት እንዴት ሊመለሱ እንደሚችሉ፣ሚታዊ ሁነቶቹን በምክንታዊነት ከልቦለዱ ታሪክ በማዋቀር በአግባቡ ተጠቅመውባቸዋል፡፡ ይህም ሳይንስ ሊፈታለት ለማይችላቸው እንቆቅልሽ ጥያቄዎቹ ሳይንስን አንግቦ መልስ ፍለጋ ሲማስን ለነበረው የመጽሀፎቹ ዋና ገጸባህሪ አድቦ እንዲቀመጥ፣ አምኖ እንዲቀበልና በከንቱ እንዳይባዝን የሚያስችል መልስ እንዲያገኝ

ያደርገዋል፡፡ የመንፈሳዊና የሳይንሳዊ እውቀቶች ፅንፍ እምን ድረስ እንደሆነ፣ ምን እንደሚመስልና እንዴት ቢወሰዱ ከአካልና ከመንፈስ ሊሰርጹም ይባል ሊዋሃዱ እንደሚችሉ ለማሳያነትም ደራሲው ተግልግሎባቸዋል፡፡

"…አባታችን ስለድፍረቴ ይቅርታ ያድርጉልኝ ከመጀመሪያው ጀምሮ በሳይንስ አግባብ የምፈታው ተራ የተፈጥሮ ክስተት መስሎኝ ብዙ ሞከርኩ፡፡ አሁን ግን ከአቅሜ በላይ እንደሆነ አምኛለሁ፡፡.."(ዝጎራ፣281)

"ያም ሆኖ ግን ከሳይንስ ውጭ የሆኑ ክንዋኔዎች በዚህ አለም መኖራቸው ሌላው እውነት ነው፡፡ ሳይንስ ሀቅና ማብራርያ፣ አመክንዮ ሊቀርብለት የሚችል መረዳትን ብቻ ያካትታል፡፡ ከዚህ ውጭ ያሉ ክስተቶች በሳይንስ ተቀባይነት ባይኖራቸውምመኖራቸውን መካድ ግን ከባድ ይሆናል፡፡"(መርበብት፣286)

ቀደም ሲል እንደተገለጸውና ከላይ ከቀረቡትሃሳቦችመረዳት እንደሚቻለው የሰው ልጅ በህይወቱ ውስጥ በተለያየ መልኩ ለሚፈጠሩ ጥያቄዎች ለእውቀት ማበልጸጊያ ተብለው ከተሰየሙ ተቋማት በሚያገኛቸው እውቀቶች(ሳይንሳዊ በሆነ አግባብ) መልስ ሊያገኝላቸው የማይችላቸው ጉዳዮችመኖራቸውን ነው፡፡ በዝጎራና መርበብት ልቦለዶች ውስጥም ይህ ጉዳይ ተደጋግሞ ሲነሳ ይታያል፡፡ገጸባህሪዎቹየተቸገሩበትን ጉዳይ ወይም የታሪክ ሽንቁር እነሱ ዘንድ ባለው እውቀት ለመሙላት አለመቻላቸው ለችግሮቻቸው መፍቻ ቁልፍ ለማግኘት ወደ ሌላ የጥበብ ስፍራ ወይም ወደ ሌላ የጥበብ ሰዎች መሄድና ደጅ መጥናት ግድ ይሆንባቸዋል፡፡ በልቦለዶቹ ውስጥ ለተነሱት እንደነዚህ አይነት አእምሮን እረፍት ለሚያሳጡና ልብን ለሚያውኩ የታሪኩ ክፍሎች መልስ የሚያገኙትና ባዛኝ አእምሯቸውንየሚያሳርፉጥበቦችን የሚያገኙትከሚታዊ ትርክቶቹነው፡፡

### 4.2.1 የሁነቶችን ተለጣጣቂነት በመፍጠር

በምዕራፍ ሁለት Doyle እና Flaten(2004) የሚት ተረኮች ከሌሎች ትርክቶች የሚለዩባቸው ባህርያት ብለው ባስቀመጧቸው ጽንሰ ሃሳቦች እና Magoulick የሚት ዓይነተኛ ጠባዮች (characteristics of myth) በማለት ባሰፈረቻቸው መመዘኛዎች ላይ እና ሌሎች ምሁራንም ባነሷቸው ፅንሰ ሀሳቦች ላይ በመመስረት ከተጠኑት ልቦለዶች

ውስጥ ሚታዊ ባህርያት ያሏቸውን ሁነቶች ለይቶ በማውጣት፤ በልቦለዶቹ ታሪኮች ቀጣይነት ላይ ያበረከቷቸው አስተዋጽኦዎች ቀጥለው ተተንትነዋል፡፡

በአቡዳቢሬስቶራንት ጀምሮ በሞገደኛው ቤተክርስቲያን ደን(ሳይት09) ፍፃሜውን ያደረገው ዝጎራ ልቦለድና ከጣሊያን ሲሲሊ ተነስቶ መካነ ህርመት ላይ መቋጫውን ያደረገው መርበብት ልቦለድ ዓብይና ንዑሳን ታሪኮቻቸው እንደ ባቡር ፉርጎ ትስስር ፈጥረው አብሮነታቸውን ያጎለበቱ ሲሆን በሂደቱ ውስጥ ከላይ እንደተገለጸው ሚታዊ ባህርያት ያሏቸው ሁነቶች በየመሀሉ እየገቡ ለጎለበተው አብሮነት ስምረት ፈጥረዋል፡፡

እንደ ጆሴፍ ካምቤል ሚት በተጋድሎ የተሞላ ተረክ ሲሆን ተጋዳሊው በብዙ ውጣ ውረዶች ውስጥ ያልፋል፡፡ በአለማየሁ ስራዎች ውስጥም የህይወትን ልዩ ልዩ መልኮች በተጋድሎ ውስጥ የማሳየት ጥበባዊ ሂደት ይስተዋላል፡፡የዝጎራው ዋና ገፀባህሪ ሲሳይም ከመጀመሪያው የልቦለዱ ታሪክ አንስቶ ብዙ ውጣ ውረዶችን በየታሪኩ እየተጋፈጠ ወደ ፊት ሲሄድ ታሪኩም እሱን ተከትሎ በተለያየ መልክ የተስተናገዱ ውጣውረዶችን ሲያትት ይታያል፡፡

በዝጎራ ልቦለድ ታሪክ ገና ከመነሻው ሲሳይ ለሚስተር ራምዚ እንቶን በብራናው ላይ የተፃፈው መልእክት በግልፅ የሚታይ አለመሆኑን ግን ደግሞ በአባመዝገበስላሴ ሶስት ዕፆች ከነመገኛ ስፍራቸው ተፅፈውበት እንደሚገኙ መገለፁ እጅግ አስገራሚና ፈታኝ ጉዳይ ከመሆኑ ባሻገር ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል?ወደ ፊትስ ምን ሊፈጠር ይችላል? ለሚሉት ጥያቄዎች መልስ የሚሆኑ ታሪኮች እንዲመጡ ይጋብዛል፡፡ አንባቢም ተመሳሳይ ጥያቄን በማንሳት የታሪኩን ጉዞ እንዲከተል ያደርገዋል፡፡

> ማወቅ የምትፈልገው ምስጥር እንዲገለፅልህ ልብ ብለህ ስማኝ!..ከዚህ ብራና ላይ ስማቸው የተፃፉ ሶስት እፆች አሉ፡፡ከተጠቀሱልህ ቦታዎች ብቻ ሄደህ ይዘህ ተመለስ፡፡ያን ጊዜ ማወቅ የምትፈልገው ምስጢር ይገለፅልሃል፡፡ እፆቹን ሳትይዝ ግን ድጋሚ ወደ ተቀደሰው ቦታ በምንም ምክንያት እንድትመጣ አልተፈቀደልህም!፡፡(ዝጎራ፤301)
>
> ብራናው ላይ የተፃፈው አንድ የመፅሐፍ ቅዱስ ጥቅስ"ከእንግዲህ ወዲህ ሌሊት አይሆንም፤ ጌታ አምላክም በእነርሱ ላይ ያበራላቸዋልና የመብራት ብርሃንና የፀሐይ ብርሃን አያስፈልጋቸውም፤ለዘላለም እስከ ዘላለም ይነግሳሉ፡፡"የዮሐንስ ራእይ22፥5 ብቻ እንጂ ሌላው ባዶ ነበር፡፡" (ዝጎራ፤14)

ሲሳይ መልእክቱ በስውር የተጻፈ መሆኑን ከተረዳ በኋላ ስውሩን መልእክት ለመግለፅ (የብራናውን ምስጢር ለማወቅ) ምን ያደርግ ይሆን? የሚለው ጥያቄ እንደገና ሌላ አዲስ ሁነት ታሪኩን እንዲቀላቀል ያደርጋል፡፡ እንዲሁም ገፀባህሪው ስውሩን መልእክት ለመረዳት የሚያልፋቸውን ችግሮች ያሳያል፡፡ በመሆኑመም ሲሳይ የመጀመሪያ ተግባሩ ያደረገው የትእዛዙን መልእክት ምንነት መረዳት ነበር፡፡ ዳሩ ግን በብራናው ላይ ያለውን ትእዛዛዊ መልእክት በቀላሉ ለመረዳት የሚቻል አይነት አልነበረም፡፡ በተደጋጋሚ ብራናውን ቢመለከትም ከላይ እንደ ተገለፀው ከአንድ የመፅሐፍ ቅዱስ ጥቅስ ውጪ ምንም የተፃፈ ነገር ማየት አልቻለም፡፡ይህ ግልፅ ያልሆነ መልእክት ሲሳይን እጅግ በጣም ግራ መጋባትና ጭንቀት ውስጥ ከቶታል፡፡ ምክንያቱም ትእዛዙ ለመፈፀም ግልፅ አይደለም ለመተው ደግሞ ትእዛዙ እድሜን እንደምንጣፍ የሚጠቀልል አሳሳቢ ጉዳይ ያለበት ሆነበት፡፡ "ኃይለ ጊዮርጊስ ልብ በል! ሌላም ትእዛዝ አለ… በፍለጋው በመድከምም ሆነ በመሰላቸት በዚያው መቅረትም አልተፈቀደልህም፡፡ ወደ ቅዱሱ ቦታ ለመመለስ በዘገየህ ቁጥር የኋለኛው ዘመንህ እንደ ምንጣፍ ወደ አንተ እየተጠቀለለ ይቀርባል፡፡"(ዝጎራ፣302)

ይህ ፈታኝ ሁነት ፍፃሜው ምን ሊሆን ይችላል? የሚል ጉጉት ከመጫሩም በላይ ገፀ ባህሪው በሁነቱ አማካኝነት ከባድ አጣብቂኝ ውስጥ መግባቱን የሚያሳዩ ታሪኮች ወደ ታሪኩ እንዲታከሉ እድል ይፈጥራል፡፡

> …በቃ በጣም የተመሰቃቀለ ፈተና ውስጥ ገባሁ፡፡ ተመልሼ ሂጄ እንዳልጠይቃቸው ዕፆቹን ካልያዝኩ በስተቀር ባዶዬን እንዳልሄድ ጥብቅ ትእዛዝ ሰጥተውኛል፡፡ ትእዛዙን እንዳልፈጽም መልእክቱ ብራናው ላይ አይነበብም፡፡ በቸልተኝነት ብተወው ደግሞ እድሜዬ እንደሚያጥር አስታውቀውኛል፡፡ በዚህም የተነሳ ሰላም አጣሁ፣ እንቅልፍ ጠፋ፣ ለመተውም ለማድረግም የማልችልበት አጣብቂኝ ውስጥ ገባሁ፡፡… (ዝጎራ፣17)፡፡

በዱባይ ባደረገው ጉብኝት ከአል-አይን ብሔራዊ ሙዚዬምመልእክቶች በስውር እንደሚፃፉና በተለየ ስልት እንደሚነበቡ ካስተዋለ በኋላ በብዙ ድካምና አስገራሚ ሁኔታ የስውሩን መልእክት ምንነትማለትም የእፆቹን አይነትና የሚገኙበትን ስፍራ ቢያውቅም እፆቹን ከሚገኙበት ቦታ ፈልጎ የማምጣቱ ሂደትም በጣም ፈታኝ ነበር፡፡በዚህ ፈተና ሰበብ ደግሞ የገፀባህሪው ቀጣይ እጣፈንታ ምን ሊሆን እንደሚችል የሚያሳዩ ታሪኮች የታሪኩ አካል

ሆነዋል፡፡የመጀመሪያውን ዕፅ (ዕፀ ሲናን ) ለማግኘት ወደ ማኅበረ ስላሴ ገዳምያደረገው የመጀመሪያው ፍለጋ ከመንገዱ አስቸጋሪነት፣ ከአካባቢው ሙቀት ከፍተኛ መሆን እና ከገዳሙ ጥብቅ ህግጋት ጋር ተደማምሮ ጉዞው በአስቸጋሪ ሁኔታዎች የታጀበ እንደነበር ያሳያል፡፡

> አሁን ባለሁበት ሁኔታ ሰውነቴ በበረሓው ጥማት ውስጥ(Dehydrated) ነው፡፡ እንኳን ጫማ አውልቄ ቀርቶ እስከ ጫማዬም እግሮቼ ዝለዋል፡፡ ይባስ ደሞ ጫማ አውልቆ መሄድ…ወይ ፈጣሪዬ! አሁን እንዳመጣ የታዘዝኩት ዕፅ ከቅፅር ግቢው ውስጥ ቢሆን እዚህ ቦታ ሰባት ቀን ልቆይ ነው ማለት ነው? ሥራዬስ? ኑሮዬስ?ብዬ በጣም ተማረርኩ …(ዝጎራ፣88-90)

ከላይ ከቀረቡት ሃሳቦች መረዳት እንደሚቻለው ሲሳይ (ተጋዳሊው) የመጀመሪያውን ዕፅ ለማግኘት እያደረገ ያለው የፍለጋ ጉዞ በጣም ከባድና ፈታኝ ነው፡፡ በግል ህይወቱ ላይም ሳይቀር ችግር የሚፈጥር አይነት ጉዞ ይህ ፈተና ጉዞው ስኬታማ ይሆን ይሆን? ወይስ ምን ያጋጥመው ይሆን? የሚሉ ጥያቄዎችን ከማስነሳት ባለፈ መልስ ሰጪ ታሪኮች ወደ ታሪኩ እንዲዘልቁ ይጋብዛሉ፡፡በተመሳሳይ መልኩ አክሱም አቅራቢያ ወደ ሚገኘው ጥንታዊው አባ ጰንጠሌዎን ገዳም ሁለተኛውን ዕፅ (ዕፀ ኅርመት)ን ለማግኘት ያደረገው ሁለተኛ ጉዞ እንዲሁ በፈተናዎችና በአስቸጋሪ ውጣ ውረዶች የተሞላ ነው፡፡

> … የተከዜን ወንዝ ተሻግሬ እንደገና ከፍታ መውጣት ጀመርኩ፡፡ የመኪናው ጎማ መቀርናት ይዟል፡፡ የመኪናው መሪ ሳይቀር እጅ ይጠብሳል፡፡ መኪናዬ ከሙቀቱ ጋር ተደምሮ ከፍታ መውጣት አዳገታት መሰል አልፎ አልፎ ታቃስታለች፡፡ ዳገቱ ማገባደጃ ላይ ‹እንደ አባጉና› የተባለችውን ከተማ አልፌ አንድ አምስት ኪሎ ሜትር እንደነዳሁ ጥቂት ቤቶች ያሉበት አካባቢ ስደርስ ድንገት የመኪናው ሞተር ጠፍቶ ጉልበቱ አቅመ ቢስ ሲሆን ታወቀኝ በፍጥነት ወደ ዳር ወጣ አድርጌ አቆምኳት፡፡ ከፍተኛ ጢስ ከመኪናዋ የሞተር ኮፈን ሲወጣ ተመለከትኩ፡፡ በፍጥነት ወረድኩና ኮፈኑን ከፍቼ ሳይ ራዲያተሩ ጭሥ መሳይ እንፋሎት በኃይል እየወጣ እንደሆነ ተረዳሁ፡፡…የፈጣሪ ያለህ የፈራሁት ደረሰ…(ዝጎራ፣123)

አሁንም ከመተማ እስከ አክሱም ያደረገው ጉዞ አስፈሪ ከሆነው የሊማሊሞ ቁልቁለት እና ከሙቀቱ ወበቅ ጋር በጣም ፈታኝ ከመሆኑም በላይ የሚንቀሳቀስባት ተሸከርካሪው እርዳታ

ሊያገኝ በማይችልበት ጥቂት ቤቶች ብቻ ባሉበት በረኃ ውስጥ ተበላሽታበታለች፡፡ ይህ በገጸባህሪው ላይ እየደረሰ ያለው ፈተና ልብን ከመንካቱና ከማሳዘኑ ባለፈ በምን መልኩ ከዚህ ፈተና ሊወጣ ይችላል? ለሚለው ጥያቄ መልስ ሰጪ የሆኑ ታሪኮች በመጥራት የታሪኩ አካል እንዲሆኑ አስችሏል፡፡ እንዲሁ ወደ አድዋው ይምርሐነ ክርስቶስ ደብር ያደረገው የሦስተኛው ዕፅ (ዕፅ ተክህኖ)ፍለጋም ከዚህ በፊት ካደረጋቸው ጉዞዎች የበለጠ አታካችና ፈታኝ ነበር፡፡

> …በዚህ መሰረት በአብዛኛው በህበሻ ጽድና በሌሎች ሀገር በቀል ዕፅዋቶች የተሞላውን ደን ከሰሜን አቅጣጫ በኩል ጀምሮ ከምዕራብ ወደ ምስራቅ የተዘረጉ የሐሳብ መስመሮችን በያዝኩት ጂፒኤስ እየታገዝኩ እንደ ዝሀ ዘጊ እየተመላለስኩ ፍለጋዬን ጀመርኩ፡፡ የደኑን ሶስት አራተኛውን ክፍል አስሼ ስጨርስ …ይሁን እንጂ ‹ዕፅ ተክህኖ› የሚባል ዕፅ ምልክቱም አልነበረም፡፡.. ድካምና ርሃብ ወደ ተስፋ መቁረጥ እያንደረደሩኝ...(ዝጎራ፣165)
>
> … በተቃራኒው አቅጣጫ ስለፋ መዋሌ ቆጨኝና እየተንደረደርኩ ወደ ሸለቆ ስወርድ ሳላስበው የረገጥኩት ድንጋይ ተፈንግሎ ወደ ሰማይ ጉኘ መሬት ላይ ተዘረርኩና ከቁጥጥር ውጭ ሚዛኔን ስቼ እንደ ሙቀጫ እየተንከባለልኩ ቁልቁል ወረድኩ፡፡ በቃ እተርፋለሁ የሚል ግምት አልነበረኝም፡፡ ረጅም ርቀት ተንከባልዬ ሳበቃ ከአንድ ከሸለቆው ጥግ ካለ የደደሆ ቁጥቋጦ ሥር ሄጄ ተወሸቅኩ፡፡ በቃ ድካም፣ ርሃብ እና ድካም ተጋግዘው በእጅጉ እንደተነሳቀልኩ ተሰማኝናወይ መከራዬብዬ ለደቂቃዎች እዛው እንደተጋደምኩ ቆየሁ፡፡ (ዝጎራ፣167)

ከላይ በምንመለከተው የጉዞ ሂደትም ብዙ መንገዶችን ተጉዞና አስቸጋሪ የሆነውን የዋግን ተራራ በብዙ ድካም አልፎ ይምርሐነ ክርስቶስ ደብር ቢደርስም ዕፁን ማግኘት ከባድ ፈተና ሆኖበታል፡፡በአጠቃላይ ትእዛዙን ለመፈፀም ከመተማ እስከ አድዋ ያደረጋቸው ፈታኝ ጉዞዎች እንዲሁም ቀደም ብሎ ከአባ መዝገበ ስላሴ እጅ የተቀበለው ብራና ግልፅ አለመሆንና እሱን ተከትሎ ፅሁፉን ለመረዳት ያደረጋቸው ውጣ ውረዶች የሚት ተጋዳሊ ከሚያደርገው ተጋድሎዎች ጋር የሚመሳሰል ነገር አለው፡፡

በዚህ መልኩ ብዙ ውጣውረዶችን ያተቱ ታሪኮች እራሳቸውን እያስፋፉ በ186 ገፅ ከተገለፁ በኋላ ይሄ ሁሉ የሆነው ለምን ነው? የሚሉ በአንባቢ አእምሮ ውስጥ ሊፈጠሩ ለሚችሉ ጥያቄዎች መልስ ሰጪ የሆኑ ሁነቶች በምልሰት ወደ ታሪኩ ሲቀላቀሉ ይታያሉ፡፡ በነዚህ ታሪኮች ውስጥ በሚታተቱ ሁነቶች ውስጥም ሚታዊነት ይስተዋላል፡፡ በመሆኑም Magoulick

(characteristics of myth) በማለት በዝርዝር ካሰፈረቻቸው ሃሳቦች ውስጥ "ሚት ከስረ መሰረቱ ከእምነት ሥርዓት ጋር የሚያያዝና የህብረተሰብ ሐይማኖታዊ ድርጊቶች እምብርት ነው፡፡" በማለት የገለፀችውን እና "ሐይማኖት ፅኑ እምነት ሲሆን ሚት ደግሞ የፅኑ እምነት መሠረት ነው"፡፡ ሐይማኖት ሰዎች ለመንፈሳዊ ወኪሎቻቸው ያላቸው መታመን ሲሆን ሚት ደግሞ የመንፈሳዊ ወኪሎች ትርክት ነው፡፡ በዚህ መሰረት በትርክቶቹ አማካኝነት የተጣለ መሠረት የጸና ሆኖ እምነትን ያስገኛል፡፡ ያለውን የJamesንሃሳብ መነሻ በማድረግ ምንም እንኳን መፃህፍቱ በስፋት መሰረታቸውን ሐይማኖታዊ ጉዳዮች ላይ አድርገው ታሪኮቻቸውን ያስኬዱ ቢሆንም በዚህ ንዑስ ክፍል ግን ሳይንሱን የሚሞግቱ ሐይማኖታዊ ይዘት ያላቸውን ዋና ዋና ሚታዊ ባህሪያት ያኗቸውን ሁነቶች ለአብነት ለመግለፅ ነው የተሞከረው፡፡ ምክንያቱም ሳይንስን መሞገትና ሁነቶችን ከእምነት ጋር ማያያዝ ከሚት ባህርያት ውስጥ አንዱ ስለሆነ፡፡

ስለሆነም ከላይ ለታየው ውጣውረድ ሰበብ የሆነው ጉዳይ የጀመረው ሲሳይና ሌሎች የውጭ ሀገር የሙያ አጋሮቹ በአስር በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ አብያተ ክርስቲያናትና ገዳማት ለዘመናት ተጠብቀው በቆዩት ቅሪት የተፈጥሮ ደኖች ላይ ስነ ምህዳራዊ ጥናት በማድረግበደኖቹ ውስጥ ያሉትን ዕፅዋት ዝርያ፣ ያሉበትን ሁኔታ፣ ችግርም ካላቸው ለመለየትና ወደፊት ተጠብቀው እንዲቆዩ የሚያሥፈልግ ነገር ካለም ለሚመለከተው አካል ሳይንሳዊ መፍትሂ ለመጠቆም በሚል መነሻ የስምንተኛ ሳይታቸውን ጨርሰው ወደ ዘጠነኛው ደን(ሳይት 09)ባመሩበት ወቅት ነው፡፡

> በዚህ ደን ውስጥም ሃምሳ ሜትር ያህሉን ጨርሰው እንደገና ወደ ፊት ለመዘርጋትና አቅጣጫቸውን ለማየት ሲሳይ ኮምፓስ፣ ማግዳሊና ጂፒኤሷን አውጥታ መልካሙ ደግሞ በግምት ሜትሩን እየጎተተ እንዲወርድ በመነጋገር የተለመደ ግብራቸውን በማከናወን ላይ እያሉ ዶ/ር ማግዳሊና ድንገት "ኡፍ" አለች በመበሳጨት መልክ፡፡ ሲሳይም ምነው? በማለት ሲጠይቃት "የሳተላይት ሽፋኑ ጠፋ ጅፒኤሱም አይመልስም" አለችው፡፡ ሲሳይም ችግር እንደሌለውና በኮምፓሱ መጠቀም እንደሚችሉ በመግለጽ ኮምፓሱን መዳፉ ላይ አድርጎ ለማየት ሲሞክር የአቅጣጫ አመልካቹ ቀስት ወይም መርፌ ግራ ቀኝ ይርገበገባል፡፡ ብዙ ጠበቀው ነገር ግን የኮምፓሱ ቀስት አንድ ቦታ ላይ ሊረጋለት አልቻለም፡፡ ምን አልባት እጄ እየተንቀጠቀጠ ይሆናል በማለት ለዶ/ር ማግዳሊና ሰጣት፡፡ በእሷ እጅ ላይም ሆኖ

መወዛወዙን አላቆመም፡፡ ሲሳይ ኮምፓሱን ተቀብሎ እንደገና ቢሞክርም አሁንም ለውጥ የለውም፡፡ በመሃሉ የፍርሀትና የአድናቆት በሚመስል ቃና ዶ/ር ማግዳሊና "ሲሳይ" አለችው፡፡ "አቤት" ብሎ ፊቱን ወደ እርሷ ሲያዞር ፊት ለፊት ወደ ታች እጇን ዘርግታ "Oh my God, I think that tree is moving! (ኦ አምላኬ! ያ ዛፍ ይንቀሳቀሳል" አለችው፡፡)" "Yaa every tree moves with the wind (አዎን ማንኛውም ዛፍ በነፋስ ይንቀሳቀሳል)" አላት ቀለል ለማድረግ ብሎ ውስጡ የነበረውን ከፍተኛ ፍርሀት እየደበቀ፡፡ማግዳሊና ግን ኮስተር ብላ "No, no I mean it is moving not swinging (አይደለም አይደለም ! መወዛወዝ ሳይሆን ይንቀሳቀሳል ነው ያልኩህ)" አለችው፡፡ "ምን አልሽ" ብሎ ሲጠይቃት "በእርግጥ አይቸዋለሁ! አንድ ጊዜ ወደ ግራ ሌላ ጊዜ ወደ ቀኝ ከነስሩ እንደ ሰው ሲንቀሳቀስ አየሁት" አለችው አፏን ከፍታ በመገረም፡፡ ሲሳይም በውሰጡ የደበቀውን ፍረሃት ባይገልጽም ከዚህ አካባቢ በፍጥነት መውጣት አለብን አላት፡፡ "I think so (እኔም የማስበው እንደዚያ ነው) አለች እሷም፡፡..." (ገጽ፣213-214)

እንግዲህ ከላይ በተገለፀው ሰበብ ምክንያት የተጀመረው ምርምር ከፍ ብሎ እንደሚታየው ያልተለመዱና ከተፈጥሮ ህግ ውጭ የሆኑ ክስተቶች መታየት ከዛም አልፎ ቀደም ሲል ሲያከናውኗቸው በነበሩ በሳይንሳዊ መንገዶች ስራቸውን ለማካሄድ ሲያደርጓቸውየነበሯቸውጥረቶች ፈታኝ ሲሆንባቸው ይታያል፡፡ በተደጋጋሚ የተለያዩ መላምቶችን እያስቀመጡ መልከ ብዙ ሙከራዎችን ቢያደርጉም ነገሩ ግን የሚቻል አልሆነም፡፡

እንደውም እየሆነ ያለው ነገር ሌላ ችግር ከማስከተሉ በፊት አካባቢውን ለቀው መውጣት እንዳለባቸው ሲስማሙ ይታያል፡፡ በመሆኑም ስፍራው የእምነት ስርዓት የሚከናወንበት ቦታ እንደመሆኑ፤ እንዲሁም በተለያዩ ስፍራዎች ላይ የቤተክርስቲያኑ አገልጋዮች በየትኛውም የቤተከክርስቲያኑ ስፍራ ላይ ማንም እንዳሻው መገኘት እንደማይችል በተለያየ መንገድ ሲናገሩ እንደሚታየው፡፡ሐይማኖታዊ ቦታዎች ላይ የሚገኙ ነገሮችን ሁሉ ሳይንሳዊ በሆነ ዘዴ ብቻ መመርመርና ማንም እንደፈለገ በስፍራው መገኘት የማይችል መሆኑን ያሳያል፡፡ በተጨማሪም ይህን ጉዳይ ሲሳይ ዕፆችን ፈልጎ እንዲያመጣ ከታዘዘው ትእዛዝ ጋር የሚያገናኘው ጉዳይ ምንድነው?የሚል ጥያቄን በመጫር የፊተኛውን ታሪክ ከአሁኑ ጋር

የሚያወዳጁ ታሪኮች እንዲፈጠሩአድርጓል፡፡እንዲሁም የነሲሳይ ሳይንሳዊ ምርምር ቀጣይ ሂደት ምን እንደሚሆን ለሚያሳዩ ታሪኮች በር ከፍቷል፡፡

በድጋሚ ከዚህ በፊት የጥናት ቡድኑን ያጋጠመው ችግር ሊፈጠር የቻለው፤ "በአካባቢው ከፍተኛ የብረት ማዕድን ክምችት ካለ የኮምፓሱ ቀስት ወይም መርፌ በከፍተኛ መግነጢሳዊ ኀይል በመሳብ ሊያሽከረክረው ወይም ሊያርገበግበው ይችላል፡፡ወይም ደግሞ የዩራኒየም ክምችት ካለም ከመግነጢሳዊ ኃይል ውጭ የሆነ ጨረር በመልቀቅ ኮምፓሱን ሊያዛባው ይችላል፡፡" የሚለውን የዶ/ር ክርስቶፈር መላምት ተገቢነት ለማረጋገጥ ከአንድ አመት ተኩል በኋላ ሲሳይ የጥናት ቡድኑን ወክሎ ወደ ሳይት 09 ደን ተመልሶ ይሄዳል፡፡ ከፍ ሲል እንደተገለጸው የሳይንስ ምርምሩ ወደፊት ቀጥሎ የጥናት ቡድኑ ያሰበውን ተግባር በተለመደው መልኩ ለማከናወን አለመቻሉ ታይቷል አንድ መላምት ሲከሽፍ ሌላ መላምት ማስቀመጥና በዛ መነሻነት ሌላ መንገድ መሞከር ባህሪው በሆነው የሳይንስ ልምድ መሰረት ከላይ ለተፈጠረው ችግር ሰበብ ሊሆን ይችላል በሚል በሳይንስ እግባብ የተቀመጠውን መላ ምት ተገቢነት ለማረጋገጥ ሲሳይ በድጋሚ ወደ ደኑ ተመልሶ በመምጣት ባለፈው ቸኩለው የዐፈር ናሙና ሳይወስዱ መሄዳቸውን እና እርሱን በመውሰድ አዲስ አበባ ለማስመርመር መምጣቱን ለአባ መዝገበ ሥላሴ ይነግራቸዋል፡፡አባም "ታዲያ በየት በኩል ነው የምትወስደው?" በማለት ላቀረቡለት ጥያቄ ፍላጎቱ በስተሰሜን አቅጣጫ በኩል ቢሆንም ፍቃድ ላላገኝ እችላለው በሚል ስጋት ቀልጠፍ ብሎ በዚህ በምዕራብ በኩል ወይም በስተደቡብ ሊሆን ይችላል አላቸው፡፡

> አባ መዝገበ ሥላሴም ፍቃዳቸውን ይሰጡታል ሲሳይም ወደ ምዕራብ አቅጣጫ በመሄድ ከሁለት ቦታዎች ላይ የዐፈር ናሙና እና አነድ አራት የሚሆኑ ድንጋዮችን በከረጢት በመክተት በፍጥነት አካባቢውን ለቆ በመምጣት የፈለገውን መውሰዱን ለአባ ነግሯቸው እየተቿከለ ተሰናብቷቸው እረፍትም እንቅልፍም የነሳውን የቤተክርስቲያነኑን ደን ምሥጢር ለማወቅ የተንጠለጠለ ልቡን አዲስ አበባ አስገብቶ ወደ ባሕር ዳር ይመለሳል፡፡በበንጋታው ጉዞዉን ወደ አዲስ አበባ በማድረግ ወደ ኢንስቲትዩቱ ሄዱ ናሙናውን ለማስመርመር የናሙና ከረጢቶቹን ለባለሙያ ይሰጣል፡፡በቀጠሮ ሰዓትም በስፍራው በመገኘ ውጤቱ ይቀበላል፡፡በውጤቱም አፈሩ የብረትም ሆነ የሌላ ማዕድን ክምችት የሌለውና እንደ ማንኛውም አፈር ኖርማል የጫካ ዐፈር ብዙ ካርበንና ናይትሮጂን ያለው ሲሆን ድንጋዮቹም ከቀለጠ ዐለት የሚፈጠረው ኢግኒዮስ ሮክ የሚባሉት ዐይነት

መሆናቸውን እና ይህ ነው የሚባል የተለየ ነገር የለው መሆኑን ይረዳል፡፡የሰማውን ነገር ለማመን እየተቸገረ እንዲህ በማለት እራሱን በራሱ መጠየቅ እና ወደ ኋላ ተመልሶ አንድ አንድ ነገሮችን በማስታወስና በመገጣጠም ስዕል መፍጠር ይጀምራል፡፡(ገጽ223-247)

የዶ/ር ክርስቶፈር መላምት ዜሮ ገባ ማለት ነው፡፡" ታዲያ የጂፒኤስ ሞገድ የሚዘጋ፣ የኮምፓስ መርፌ ሲፈልግ የሚያሽከረክር፣ ሲፈልግ የሚያቆም፣ ዶ/ር ማግዳሊና እንዳለችው ዛፍ የሚያንቀሳቅስ፣ ወጣቱን መልካሙን ዛፍ ስር የሚያሥተኛ፣ የእኔን ልብ ደግሞ በፍርሀትና ሽብር የሚንጥ ምን ኃይል ነው?"

"…ሲጀምር መልአከ ሰላም ለምን በዚያ በኩል እንዳናልፍ ጠየቁን?

መልካሙ ፤የሆኑ መነኩሴ በበትር ትከሻዬን ሲነኩኝ ወደቅሁኝ› ያለው ደሞ ትዝ አለኝ እውነቱን ከሆነ ለምን በአካባቢው አላየኋቸውም?

አባ መዝገበ ስላሴ ደግሞ ‹ብቻዬን ነኝ ማለት አይደለም›ያሉት ደግሞ መጣ፡፡ ብቻቸውን ካልሆኑ ታዲያ እነማን አብረዋቸው እየኖሩ ነው?

ከእረኞቹ መካከል ‹ደነቹ› ያለው ልጅ ደግሞ ትዝ አለኝ፡፡ በቤተክርስቲያን ደነች የሚባሉት እነማን ናቸው? ውስጥ ካሉስ ያን ያክል ስንዳክር እንዴት ሳናያቸው ቀረን? አይታዩም ማለት ነው? ሰው ሆነው እንዴት ነው የማይታዩት? አቅጣጫችንን ያሳተን የተፈጥሮ የብረት ክምችት ወይም ሌላ ማዕድን ካልሆነ የእነርሱ ኃይል ነው ማለት ነው? ለመሆኑ እውነት እዚያ ደን ውስጥ የሆነ ግዙፍ የነሳ እካል ካለ ለምን አይታይም? አልኩና ደጋግሜ ባስብ ጠብ የሚል ፍንጭ አጣሁ…" (ገጽ፣ 247)

ከላይ ከሰፈረውሃሳብ እንደምንረዳው ምርምሩ በሚደረግበት ደን (ሳይት 09) ውስጥ በተመራማሪዎቹ ላይ የደረሰው አስፈሪና አስደማሚ ክስተት፣ በዕፅዋቱ ላይ የሚታዩት ከጠፈጥሮ ህግጋት ውጭ የሆኑ ክስተቶች፣ ግራ አጋቢ የሆኑ የነአባመዝገበስላሴ ንግግሮች በተገለጸው መልኩ ጠቅለል ብለው ቢቀርቡም በየደረጃው ጉዳዩ በሚነሳበት ቦታ ሁሉ ያልተፈቱ እንቆቅልሾችን ሚስጥር ለማወቅ በመጓጓት ጠያቂው ሲጠይቅ እንጂ መልስ ሲሰጠው አይታይም፡፡Stefnn Stenudd "The Logics of Myth" በሚልርዕስባሰፈረው ፅሁፍየሚትንልዩባህርያትየሚገልጹናቸውብሎ ካሰፈራቸው ስድስትነጥቦች ውስጥ አንዱ "መሆንአለመሆኑን (እውነተኛነቱን) ለማረጋገጥ የሚያሥቸግር፤ ጥያቄ ለሚጭሩ ሃሳቦች ምላሽ መስጠትም ግድ የማይለው ተረክ ነው፡፡" የሚለው ሃሳብ ይገኛል፡፡ በዚህ መሰረት ከላይ

በቀረበው  የልቦለድ ታሪክ  ውስጥ ይህን አይነት ሚታዊ ባህርያት ያላቸው ሁነቶች ይታያሉ፡፡እነዚህ ሚታዊ ባህርያት ያላቸው ሁነቶችም ታሪኩን አጓጊ እንዲሆን በማድረግ ከአንዱ ታሪክ ወደ ሌላኛው ታሪክ የሚደረገው ሂደት መሳጭ እንዲሆን አድርገውታል፡፡ እንዲሁም የተዓምረኛውን ደን ምስጢር እና እጅ አልሰጥም ያለው የነሲሳይ ሳይንሳዊ ምርምር መጨረሻ ምን ሊሆን እንደሚችል የሚያሳዩ ሁነቶችን ወደ ታሪኩ በማስገባት የታሪኩ ይዘት ትስስሩን በጠበቀ መልኩ ወደ ፊት እንዲሄድ አስችለዋል፡፡

…ወዲያውኑ ፕሮፌሰር ሃሮልድ ትዝ አሉኝ፡፡…ጊዜ አላጠፋሁም ደወልኩና ተገናኘን፡፡ ከተለመደው ሰላምታ በኋላ ሳይት 09 እንደሄድኩ ነገርኳው፡፡

Excellent and what did you find?›(ግሩም ነው! እና ምን አገኘህ?›አሉኝ በጉጉት ወደ ኮምፒተሩ ስክሪን እየተጠጉ፡፡

ምንም የተጨበጠ ነገር የለም አልኩና ይባስ ብሎ የኮምፓሴን የአቅጣጫ መርፌ ከመስታዎቱ ጋር አጣብቆ እንዳቆመው ነገርኳቸው፡፡

Incredible›(አስደናቂ ነው!) አሉ፡፡

ዶ/ር ክርስቶፈር እንዳሰበው የዐፈርና ድንጋይ ናሙና አምጥቼ እንዳስመረመርኩና ምንም የተለየ የብረት ወይም ሌላ ንጥረ ነገር ክምችት እንዳልተገኘ ነገርኳቸው፡፡

ያ ቦታ አንዳች ከባድ ምስጢር ይኖረዋል አላልኩህም?›አሉ፡፡

…ከዚያ ደን ውስጥ እኛ የማናየው ወይም የማናያቸው ሰዎች ወይም ሌላ ፍጥረታት ሊኖሩ ይችላሉ፡፡ ከሰው እይታ ሊሰወሩ የሚችሉበት ጥበብ ይኖራቸዋልብዬ ገምቻለሁ፡፡ እናም እነርሱን ለማየት አንድ እድል አለ አልኳቸው፡፡

Interesting! Now we are thinking a classic research›(አጓጊ ነው! አሁን መሰረታዊ ምርምር እያሰብን ነው ማለት ነው)› አሉ፡፡

…እንዲያው የሚቻል ከሆነ ከእናንተ ዩኒቨርሲቲ ወይም ገበያ ላይ ካለ ይህንን መሳሪያ/መነፅር/ የማገኝበት መንገድ ቢያመቻቹልኝ ብዬ ነው፡፡ አልኳቸው፡፡

… የሰሜኑን አቅጣጫ እንደያዝኩ ወደ ፊት ተራመድኩና የዐፈር ናሙና የወሰድኩበት አካባቢ ስደርስ መሳሪያውን አስቀመጥኩ፡፡

…እየተንቀጠቀጥኩ መነፅሩን አነሳሁና ፊት ለፊት ለማየት ከዐይኖቼ ላይ አደረኩ፡፡

ዋው! አልኩ ...የተባዘተ ጥጥ የሚመስልና በእጅ ቢዳስሱት እንደ ግድግዳ የሚዳሰስ የመሰለ ጉም/ጭጋግ ደኑን ሞልቶታል፡፡ የሚጉለመለመውን ጉም አይቼ ሳልጠግበው፡-

ግን እንዴት አልኩና መነፅሩን አውልቄ በዐይኔ ሳይ ምንም የለም፡፡ግራ ተጋባሁና እንደገና መነፅሩን ዐይኔ ላይ አድርጌ ሳይ ደነገጥኩ፡፡

ለምን? ድቅድቅ ጨለማ ሆነ! በፍጥነት መነፅሩን አውልቄ ወደ መሳሪያው ስመለከት አረንጓዴው መብራት ጠፍቷል፡፡ አይደረግም አልኩና መሳሪያውን ሁሉንም ቁልፎች አጠፋፍቼ እንደገና አስነስቼ ሞከርኩ...ቀይ መብራት የለ፣ ድምፅ የለ፣ በቃ መሳሪያው ስራ አቁሟል፡፡...ድንገት ብድግ ወደ ፊት በወኔ ልራመድ ስል...ከኋላዬ ከትከሻዬ ላይ የሆነ ነገር...ነካ አደረገኝ፡፡ ዘወር ብዬ ለማየት ስሞክር ሰማይ ምድሩ ዞረብኝና መሬት ላይ ዝልፍልፍ ብዬ ወደቅሁ..."

...አባታችን ስለድፍረቴ ይቅርታ ያድርጉልኝ ከመጀመሪያው ጀምሮ በሳይንስ አግባብ የምፈታው ተራ የተፈጥሮ ክስተት መስሎኝ ብዙ ሞከርኩ፡፡ አሁን ግን ከአቅሜ በላይ እንደሆነ አምኛለሁ፡፡.."

(ዝጎራ፣253-281)

በተለያዩ መላምቶች ላይ በመመስረት በሳይት 09 ደን ውስጥ ያጋጠሙ ያልተጠበቁ ክስተቶችን ምንነት ለመረዳት በተመራማሪዎቹ በኩል ልዩ ልዩ ሙከራዎች ሲደረጉ እንደነበር ቀደም ባሉት ክፍሎች መመልከት ተችሏል፡፡ በዚህ ለሦስተኛ ጊዜ በተደረገው ሙከራም በሰዎች እይታ የማይታዩ ሰዎች ወይም ሌላ ፍጥረታት ኖረው ሊሆን ይችላል፡፡ በሚል መላ ምት ላይ በመመስረት ከሰው የማየት ገደብ ውጭ የሆኑ ሞገዶችን ሊያሳይ የሚችል የእይታ መሳሪያ (መነፅር) ከአሜሪካን ሀገር ድረስ በማስመጣት ለማየት የተደረገው ሙከራ ከዚህ በፊት እንደነበሩት ሙከራዎች ሁሉ ጠብ የሚል ነገር ያልተገኘበት ከንቱ ልፋት እንደ ነበር እና እንዲያውም ሌላ ተጨማሪ ችግር ሲያከሰት ታይቷል፡፡ በመሆኑም ከላይ የተገለፁት ሚታዊ ባህሪ ያላቸው ሐይማኖታዊ ጉዳዮችም በልቦለዶቹ ታሪኮች ውስጥ እንዲሁ የተገኙ ሳይሆኑ ለሚነሱ ጥያቄዎች መልስ የሚሰጡ፣ ከሃሳብ ወደ ሃሳብ የሚደረገውን ሽግግር የሰመረ የሚያደርጉ፣ የልቦለዶቹ ትልሞች የጠበቁ እንዲሆኑ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያበረከቱ ሲሆኑ በይበልጥም ሚታዊ ባህርያት ያላቸው ሁነቶች ሳይንሱን እየሞገቱ ሐይማኖታዊ ጉዳዮችን ሁሉ በሳይንስ መነፅር በመመልከት ለእውነተኛ ምልከታ ቀጥተኛ

ምላሽ ማግኘት ከባድ መሆኑን ሲያሳዩ ይታያሉ፡፡በዚህ መልኩ ሳይንሱ በሐይማኖቱ መረታቱን በገፀባህሪው አንደበት ደራሲው ከገለፀ በኋላ ሚሥጥሩን ለማወቅ ከላይ በትንተናው መነሻ ላይ በተገለፀው መልኩ ለሲሳይ ለፍላጎቱ መልስም ቀኖናም የሚሆን ትእዛዝ እንዲሰጠው ሆኗል፡፡

በመርበብትም እንዲሁ ልክ እንደ ዝጎራው ተጋዳሊ ሁሉ የመርበብቱ ተጋዳሊ (ሲሳይም) በሚስተር እስጢፎ የተሰጠውን አደራ ከግቡ ለማድረስ ብዙ ፈታኝ ሂደቶችን ሲያልፍ ይታያል፡፡ገና ከጅምሩ አደራውን ከሚስተር እስጢፎ እጅ ከተቀበለበት ዕለት ጀምሮ በሚስተር እስጢፎ ሴት ልጅ ናታንያ በኩል የአደራ ሳጥኑን ለመቀበል በተቀነባበረበት ሴራ አማካኝነት ከተጀመረው ፈተና (መርበብት፣83) ጀምሮ ከባህርዳር አድዋ፣(152) ከአድዋ ጎንደር፣ (163) ከጎንደር ወደ ጎርጎራ የጣና ሐይቅ(218) ካደረጋቸው አድካሚ ፍለጋዊ ጉዞ መካነ ህርመት እስከሚደርስ ያደረገውን አልህ አስጨራሽ ጉዞበተጋድሎ የታጀበ ታሪክ ነው፡፡ በታሪኮቹም ከላይ በዝጎራ እንደተገለጸው ገጸ ባህሪው አንዱን ችግር የምፈታበትን ዘዴ አገኘው ሲል ሌላ ችግር እየተፈጠረበት እንደገና ሌላ መላ እየዘየደ በዚህ መሃል ሐይማኖታዊ ባህሪ ያላቸው ሁነቶች በየመሀሉ እየገቡ ለችግሮቹ መፍትሄ እየሰጡ ታሪኩ ወደ ፊት እንዲቀጥል ሲያደርጉ ይታያሉ፡፡ በአጠቃላይ በሁለቱም ልቦለዶች ውሰጥየሲሳይ ያለመታከት መሞከር እና እየወደቁ እየተነሱ መታገልና በመጨረሻም በመሸነፍ ውስጥም ቢሆን እረፍት ማግኘትበሚት ውስጥ ከሚታየው የተጋድሎ ሂደት ጋር ቀጥተኛ ዝምድና ይታይበታል፡፡

ሌላው በዝጎራ ልቦለድ ታሪክ ውስጥ ያልታየ ከመደበኛው ወጣ ያሉ ያልተለመዱ ፍጡራንን እንደ ገፀባህርያት መጠቀም በመርበብት ልቦለድ ታሪክ ውስጥ ታይቷል፡፡ በክለሳ ድርሳናት ላይ "የሚት ትርክቶች ከሌሎች ትርክቶች የሚለዩባቸው ባህሪያት" በማለት Doyle and Flaten ካሰፈሯቸው መመዘኛዎች ውስጥ አንዱ ተዘውትረው ከተለመዱት ገፀባህርያት ወጣ ባለ መልኩ መናፍስታዊ ገፀባህርያትን መጠቀም በሚት ተረክ ውስጥ የሚስተዋል መሆኑን ገልፀዋል፡፡ እንዲሁም ከሌሎች መናፍስታዊገፀባህርያትን ከሚጠቀሙ እንደ የመናፍስት ተረት ካሉት ትርክቶች አንድ ጊዜ እንዲህ ሆነ የሚል አቀራረብን አለመከተሉና ግልፅ የሆነ መቼትን መጠቀሙ ልዩ እንደሚያደርገው ገልፀዋል፡፡ በመርበብት ልቦለድ ውስጥም ይህንን ጉዳይ እንመለከታለን፡፡

…ኩ..ኩ..ኩ..የሚል ድንጋይና ድንጋይ ሲፋጭ የሚሰማ አይነት ድምፅ ወደ እሱ እየቀረበ መጣ፡፡ ድጋሙን ሲጨርስ ከመቅጽበት የንፋሱም የድንጋዩም ግጭት ድምፅ አስፈሪ ንውጥውጥታ ፈጠረ፡፡ ተከድኖ የነበረው ሳጥን ተከፈተና እንደ ጢስ ቡንን ብሎ ወደ ላይ ወጣና የሰው አምሳል ያለው ግዙፍ አካል ከፊቱ ቆመ፡፡ እርቃኑን የቆመ ሲሆን መልኩ ወደ ጥቁር ሰማያዊ (Blue black) ያደላ ነበር፡፡የሌሊት ወፍ የመሰለ ክንፍ አለው፡፡ እንደ መንጠራራት ሲል ቁመቱ በትልቁ ዛፍ ልክ የሆነ መሰለ፡፡ አካባቢው እጅግ አስቀያሚ በሆነ ጠረን ተበከለ፡፡ ተንጠራርቶ ሲጨርስ ዝሆን የሚያክል መጠን ይዞ፡- ‹ስምንተኛው ሺ ዘመን እስኪያልፍ ለሚፈቅደኝ ፈቃድ የምሞላ በባህር፣ በየብስና በአየር የሠለጠንኩት የመናፍስት አለቃ ራሙኤል እባላለሁ፡፡›አለና ምን ፈቃድ ልሙላልህ አለው፡፡…

እሽ ምን ልታዘዝ?› አለ ጎንበስ እንደማለት ብሎ

…ማነው በዚህ ሳጥን ያሰረህ ?› አለ ሲሳይ…

በድጋሙ ያለውን ኅቡዕ ስም ለሚጠሩ እገለጥ ዘንድ ፣ያሻቸውን እፈጽም ዘንድ ለታመኑኝ ለቃየል ልጆች ቃል አለኝ›፡፡አለ

እንዴት ወደ ኢትዮጵያ መጣህ? ከየት መጣህ? ማነው ድጋሙን ያዘጋጀው? አለ ሲሳይ፡፡…

ረጅም ነው ታሪኩ፡፡ከፋርስ ቃል በገባሁለት ሰው ጀምሮ ድጋሙን አንዱ ከአንዱ በጉልበትም በስልትም እየተቀባበለ ወደዚህ ሀገር መጣሁ፡፡ ብዙ ዘመን በሚስጥራውያን የኢትዮጵያ ሊቃውንት ስታዘዝ ኑሬያለሁ አለ፡፡›

ማነው ሐይቅ ውስጥ ያሥቀመጠህ ? እንዴት ከጣልያኖች እጅ የፍሊጋው ካርታ ገባ?› አለ ሲሳይ፡፡

ምን ያደርግልሀል ብሎ በቁጣ ነበልባል ዓይኑን አጉረጥርጦ ሊጠጋ ሲል ድጋሚ ሲሳይ ዕፁን ወደ እርሱ አቅጣጫ ዘረጋ፡፡ እንደገና ሰብሰብ አለና ‹ለምን የማደርግልህን ነገር አታዘኝም?› አለ፡፡

ይኸም የምፈልገው ጉዳይ ነው› አለና ‹ጥያቄዬን መልስልኝ!› አለ ሲሳይ፡፡”

በሱስንዮስ ዘመን ከዚያም ቀደም ብሎ በጀመሩት ጥረት አውሮፓውያኑ ሚስዮናውያን ንጉሡን የካቶሊክ እምነት ተከታይ ማድረግ ችለው ነበር፡፡ የካቶሊክ እምነት ብሔራዊ ሐይማኖት ሆኖ ሲታወጅ ቅጣት የፈሩ አንድ አንድ የኦርቶዶክስ ደባትራን ካቶሊክነትን ተቀብለው ነበር፡፡ በዚህ አጋጣሚ ይሄ ሳጥን ከነሚስጥሩ

> ከካቶሊክ ሚስዮናውያኑ እጅ ገባ፡፡ ግእዝን ጠንቅቀው ያውቁት የነበሩ ሚስዮናውያን ምስጢሩን ደረሱበትና እኔን ማናገር ጀመሩ፡፡ እኔማ ጭካኔን በንጉሡ ልብ ውስጥ በማሳደር፣ ሲያስፈልግም አንድ አንድ አስደናቂ ምትሀቶችን እያሳየሁ ንጉሡ በኦርቶዶክሶች ላይ እንዲጨክን አደረኩ(መርበብት 292-304)

ከዚህ ሃሳብ እንደምንረዳው ከሲሳይ ጋር ቃለ ምልልሱን የሚያደርው የመናፍስት አለቃ ራሙኤል ሲሆን የገፀባህሪያቱ ቃለ ምልልስም ግልጽ በሆነ ጊዜና ቦታ (መቼት) የተደረገ ነው፡፡ እንዲሁም የሚት ተጋዳሊዎችለአብዛኛው ተራ ሰው የማይቻለውን ከባድ ተግባር እንደሚያከናውኑ በKirk እንደ ተገለጸው ሁሉ ሲሳይም ከራሙኤል ጋር ሲያደርገው የነበረው ንግግር ማንኛውም ሰው ሊያደርገው የሚችለው አይነት ተግባር አይደለም፡፡ በዚህ ሚታዊ ባህሪ ባለው ሁነት አማካኝነትም በልቦለዱ ታሪክ በስፋት የሚተረክለት ሳጥን በውስጡ ከያዛቸው መፃፍና ዕፅ ጋር ለ350 ዓመታት በሐይቅ ውስጥ ለምንና እንዴት እንዲሁም በማን እንዲቀመጥ እንደተደረገ፣ ከየት እንደመጣ፣ የጣሊያኖች ኢትዮጵያን መውረር፣የንጉስ ሱስንዮስ የካቶሊክ ሐይማኖትን መቀበልና ኋላም ወደ ቀድሞ ሐይማኖታቸው መመለስ፣የአክሱም ሀውልት ወደ ሮም መጓዝና መመለስ ሰበብ፣የፍሊጋው ካርታ በጣሊያኖች እጅ እንዴት እንደገባና የመፅሐፉና የዕፁ አገልግሎት ወዘተ.ጥያቄዎች መልስ እንዲያገኙ ያስቻለ የታሪኩ አካል ሲሆን የፊት ለፊቱን ታሪክ ከኋላ ከሚመጣው ታሪክ ጋር በመወዳጀት ከፍተኛ አስተዋጽኦን አበርክቷል፡፡

## 4.2.2 ጉዞ ትልም (ምንን እና ለምንን) በማሳየት

የአንድልቦለድ ትልም መሰረት የልቦለዱ ታሪክ ቀጥተኛ ባለቤት የሆነው ገፀባህሪ የሚፈፅማቸው ድርጊቶችና የደራሲው ዋነኛ ዓላማ ናቸው፡፡ በዚህ መሰረትነት በልቦለዱ ውስጥ ያሉት ሁነቶች በምክንያትና ውጤት ግንኙነት በውል ተቀናጅተው ጥምረት የሚፈጥሩበት ሂደት ትልምን ይፈጥራል፡፡ በመሆኑም በምዕራፍሁለትየፅንሰሃሳብማብራሪያላይስለ ሚት አላባውያን ባህሪያት እንደተጠቆመው የሚት ታሪክ የራሱ የሆነ ስርዓት፣ የአወቃቀር ጠባያትና መንገድ ያለው መሆኑ ተመልክቷል፡፡ በዚህ ንዑስክፍልምከነዚህየሚት አላባውያን ጠባያትየተወሰኑትን በማንሳት የዋናው ገፀባህሪ አጠራር እንዴትና ለምን እንደሆነ፣ የሚያደርጋቸው ጉዞዎች እና የሚያልፋቸው ውጣውረዶች በምን ሳቢያ እንደሆኑ በማሳየት በልቦለዶቹ ታሪኮች ቀጣይነት ላይ ስላላቸውሚናበተመረጡ ዝጎራና መርበብትልቦለዶችለማሳየትተሞክሯል፡፡”ታሪክ በጊዜ ቅደም ተከተል የተቀናጁ ሁነቶች ትረካ

ነው፡፡ትልምም የሁነቶች ትረካ ሲሆን ዋነኛ ትኩረቱ ግን በምክንያትና ውጤት ላይ ነው"(2007፣158) በማለት ኢ.ኤም ፎርስተርን ጠቅሶ ዘሪሁን እንደፃፉት ታሪክና ትልም ጥብቅ ግንኙነት አላቸው፡፡

ልቦለዶቹን ከመጠራት ፅንሰሃሳብአንፃርለማየት ዋናገፀባህሪውሲሳይ የተወሰደሲሆን፣ የአጠራር ሁኔታውና አመራረጡ እንዴትና በምንመልኩ እንደተካሄደ አሳይየሆኑሁነቶችን ከልቦለዶቹ በመምዘዝትንታኔተሰጥቷል፡፡ በመጠራት ፅንሰ ሃሳብ ላይ እንደተገለጸው ጥሪው በተለያዩ መንገዶች ተግባራዊ ሊሆን ይችላል፡፡ ከአጠራር ሁኔታዎች ውስጥ አንዱ በዕለት ተእለት ኑሮ በሚፈፀሙ ድርጊቶችና በሚደርሱ ሁነቶች አማካኝነት የጥሪው ድምፅ እንደሚሰማ ተገልጿል፡፡ በመሆኑም የዝጎራውና የመርበብቱ ሲሳይ በሰርክ ተግባሩ ተጠምዶ ባለበት ሁኔታ ውስጥ ለተጋድሎ ሲጠራ ይታያል፡፡ ለአብነት በዝጎራ ድንገት ባጋጠመው የ"ሳይት 09" ያልተለመደ ክስተት አማካኝነት ወደ ዋናው ገድል የመጠራት መንገዱ ይጀመራል፡፡

> እ.. በዚህ ስፍራ ያጋጠመን ጉዳይ ጥልቅ ምርምር የሚጠይቅ አስደናቂ ክስተት ነው፡፡ በሌላ ጊዜ በተረጋጋ መንፈስ ሲሳይ ተመልሶ መጥቶ የተለያዩ መላ ምቶችን አስቀምጦ ጉዳዩን በጽሞና ይመርምረው፡፡ በእኔ ግምት ሲሳይ ለዚህ ስራ ብቁ ነው፡፡" (ዝጎራ፣219)

በዚህ የመጀመሪያው ለተጋድሎ የመታጨት ሂደት ላይ ላዩን ስናየው የጥናት ቡድኑ ያጋጠመውን ጉዳይ የመፍታት አደራ ለሲሳይ የሰጠበት ምክንያት ቀሪዎቹ የቡድኑ አባላት ኢትዮጵያዊ ባለመሆናቸውና ጉዳዩ ከሚገኝበት አካባቢ ርቀው የሚገኙ በመሆኑ ቢሆንም ቅሉ ውስጥ ውስጡን ግን Joseph Campbell እንደሚለው ሚታዊ ተጋዳሊ ከማህበረሰቡ የሚወጣና የማህበረሰቡ የወል ማንነት እና የልዩ ልዩ እሴቶች ማድሪያ እንደመሆኑ ከፍለፊት ላለው ተጋድሎ የማህበረሰቡን ባህልና እምነት በአንድ ገምዶ በባለቤትነት ስሜት ተጋድሎውን ለማስኬድ የሚችል መሆን አለበት ይላል፡፡ በመሆኑም የመመረጥ እድሉ ለሲሳይ መሰጠቱ ከሚት ተጋዳሊ አመራራጥ አንፃር ተገቢነት ያለው ነው፡፡ ኋላ ላይም ለተቀበለው አደራ ሃላፊነቱን ለመወጣት በብዙ መልኩ ሲለፋበት ለነበረው ጉዳይ መፍትሄ ማጋኛ መንገድ ወይም ለዋናው ተጋድሎ ጅማሬ የሆነውን ትእዛዝ በአባ መዝገበ ስላሴ በኩል የተላለፈለት እንዲሁ አልነበረም፡፡

> ምኞትህና ፍላጎትህ ምን እንደሆነ አውቃለሁ፡፡ የተማርከው ትምህርት ብዙ እንድትጠይቅ እንደሚገፋህ እረዳለው፡፡ የሆነው ሆኖ ማወቅ የምትፈልገው ነገር በእኔም በአንተም

ፍላጎትና እውቀት የሚሆን አይደለም፡፡ ለማንኛውም ፍላጎትህና ጉጉትህ ከክፉት የመነጨ ባለመሆኑ የቦታውን ምስጢር ለማወቅ ከሚፈቅዱት መልእክት ይገፎልሃለው፡፡(ዝጎራ፣ 299)

"ለማንኛውም ፍላጎትህና ጉጉትህ ከክፉት የመነጨ ባለመሆኑ..."የሚለው የአባ መዝገበ ስላሴ ንግግር የራሱ የሆነ መልእክት አለው፡፡ ምሁራን እንደሚገልፁት ሚታዊ ተጋዳሊ የወገኖቹን ስጋዊ እጦት የሚሞላ ፣መንፈሳዊ ድቀታቸውን የሚጠግንና እምነት የሚጣልበት መሆን አለበት፡፡ በመሆንም (በዝጎራ 173-179) በጀርመናዊው ሽምበር በአገረ ኢትዮጵያ በመረብና በተከዜ ሸለቆ፣ በአድዋና በላስታ እንዲሁም በሰሜን ተራሮች ላይ የደረሰው ከ2400 በላይ የሆኑ የእፅዋት ናሙናዎች ዝርፍያ በገዳማውያኑ (በአባቶቹ) ላይ ያደረሰውን ትልቅ የመንፈስ ስብራት ለመጠገን ይችላል እንዲሁም እንደ ሽምበር አስነዋሪ ተግባር አይፈጽምም ተብሎ በገዳማውያኑ ዘንድ እምነት ስለተጣለበት ነው የተመረጠው:: በአባ መዝገበ ስላሴ ንግግር ውስጥም ይህ ነው የሚስተዋለው፡፡

> "...አሳዛኙ ትዝብት ግን ሽምበር እንዲህ ባለ አኳኋን የተከፈተለትን እድል ተጠቅሞ በአካባቢው የሚገኙትን እፅዋት ዝርዝር መረጃ ከናሙና ጋር አድርጎ በምሥጢር ፈረንሳይ ፓሪስለሚገኘው ጃርዲን ደስ ፕላንቲስ (Jardin des plantes)፣ ጀርመን ሙኒክ ለሚገኘው ቦታንስቼስሙዚዬም(Botanisches Museum)ለእንግሊዝ ደግሞ ሎንዶን ኪው ለሚገኘው ሮያል ቦታኒካል ሶሳይቲ(Royal Botanical Society) እና ለሌሎችም እየላከ ሀብት ይሰበስብ ነበር" (በዝጎራ፣ 174)

ከላይ ከተገለፀው የአባ ወልደ አረጋዊ ንግግር መረዳት እንደሚቻለው በሽምበር በተደረገው ዝርፊያ ምክንያት ታሪኩን በሚያውቁት አባቶች ዘንድ ሐዘንና ቁጭት መኖሩን ነው፡፡

ሌላኛው የሚት ተጋዳሊ የገድል ጥሪ የማህበረሰቡን ወግ፣ ባህል፣እምነትና ስርዓት ማህበር ተከትሎ በተለያየ መንገድ ሊከወን ይችላል፡፡ በመርበብት ልቦለድ ውስጥም የምንመለከተው የአጠራር ሂደት ማህበረሰባዊ ወግን የተከተለ ነው፡፡ የትኛውም ማህበረሰብ ውስጥ ባለ ልማድ ለአንድ ትልቅ ጉዳይ የትኛውንም ሰው የመምረጥ ነገር አይታይም ይልቁንም ጊዜ ወስዶ ይህንን ጉዳይ ማን በተገቢው መልኩ ሊወጣ ይችላል ብሎ ካሰበ በኋላ ነው ወደ መምረጡ ሂደት የሚገባው በመርበብትገጽ 13 ላይም የሲሳይ በሚስተር ሮቤርቶ ለእረፍት የሚመስል ግብዣ ይልቁንም ግን ለአንቱ ሚስተር እስጢፋኖ የቤት ስራ ሲሳይን በማጨት ወደ ጣሊያን

ሲሲሊ እንዲመጣ መጋበዝ ውስጥ የሲሳይ በሮቤርቶ አመኔታን ማግኘት ለጥሪው ሰበብ ሆኖ ይታያል ፡፡

…ይሁን እንጂ ሲሳይ እንደሚያስበው ሚስተር ሮቤርቶ የጋበዘው እንዲሁ ለእረፍት ብቻ አልነበረም፡፡ይልቁንም በውስጡ ይዞት የቆየው የአንድ አጎቱን የቤት ስራም ለማሳካት ሲሳይን በልቡናው ስላጨውም ጭምር ነው፡፡" (መርበብት፣13)

ከላይ የቀረበውን ሃሳብ በሚያበለጽግ መልኩ ጥሪው ደግሞ ለምንና እንዴት እንደሆነ በሚከተለው መልኩ በሚስተር እስጢፋኖ ለሲሳይ ሲብራራ ይታያል፡፡

> ሚስተር ሲሳይ! ለረጅም ዘመን ሳልፈፅመው የቀረሁት ከእኔ ጋር የሚኖር አደራ አለብኝ ፡፡ይህን አደራ እኔ እንድፈፅመው የተጠየኩ ቢሆንም በተለያዩ ምክንያቶች አልቻልኩም፡፡ እድሜዬ እየገፋ ሲሄድ ደግሞ አደራው ለኔ መሆን እንደሌለበት የሞራል ጥያቄ ፈጠረብኝ …እናም ይህን አደራ መወጣት ያለበት ኢትዮጵያዊ ነው ብዬ ካመንኩ ቆየሁ፡፡ ይሁንና ታማኝ ሰው ለማግኘት በኔ በኩል የማይቻል ሆነብኝ፡፡… ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ግን ወንድሜና ወዳጄ ሮቤርቶ ከሀገራችሁ ኢንቨስት ለማድረግ መወሰኑን ስረዳ ይህንኑ የቤት ስራ እንዲሰራልኝ በማለት የሚታመን ሰው እንዲፈልግልኝ ጠይቀው ነበር፡፡… እናም አደራዬን ሊወጣ የሚችል ሰው አንተ ልትሆን እንደምትችል ጠቆመኝ…" (መርበብት፣58)

ከላይ ከቀረበው ሃሳብ እንደምንረዳው ገፀባህሪው ለተጋድሎ የተጠራበት ሂደት እንዲሁ በዘፈቀደ እንዳልሆነና በጠሪው ዘንድ ማህበረሰባዊ አደራን በታማኝነት ተቀብሎ ከግብ ማድረስ ይችላል የሚል አመኔታን ማግኘት በመቻሉ ነው፡፡ በመሆኑም ጥሪው ለተጠሪው የቀረበለት በሚት የተጋዳሊ ጥሪ ስርዓት መሰረት ተጋዳሊ ሊያሟላ በሚገባው መመዘኛ ተመዝኖ መሆኑን እንረዳለን፡፡ በዚህ የሚት ተጋዳሊዎች ለተጋድሎ በሚጠሩበት አግባብ የገጸባህሪው መጠራት ለልቦለዱ ታሪኮች ተአማኒነትን ከማላበሱ ባሻገር ቀደም ባሉት ጊዜያት በአብያተ ክርስቲያናት ደኖች ላይ የተደረጉ አሳዛኝ የሚባሉ ሁነቶች ወደ ታሪኩ ተቀላቅለው የልቦለዱ ታሪክ ይዘት እንዲሰፋ አድርጓል፡፡

ሌላው የሚት አላባ ጉዞ ነው፡፡ ጉዞው የተጋድሎ አካል ሆኖ አርበኛው ወይም ተጋዳዩ ያደረገውን ሂደት የከፈለውን ዋጋና መሥዋዕትነት እንዲሁም ይዞት የሚመለሰውን ድል ወይም በረከት የሚያሳይ ነው፡፡ ከላይ የሚት ታሪክ በተጋድሎ የተሞላ መሆን በሚለው ሃሳብ ስር እንደ ተገለጸው በዝጎራ ረጅም ልቦለድ ሲሳይ በየገዳማቱ፣ በመተማ፣ በሊማሊሞ ቁልቁለትና በተከዜ በረሀ፣ በአክሱምና በደብረ ታቦር ፣ እንዲሁ በመርበብት በጣሊያን ሲሲሊ

ከሚስተር እስጢፋኖ ልጅ ከናታንያ ጋር ካደረገው ትግል ጀምሮ መካነ ህርመት እስከሚደርስ ያደረገውን አልህ አስጨራሽ ትግል ለውጫዊ ጉዞ አብነት ነው፡፡ በመሆኑም ቀደም ሲል የተጠቀሱት ፈታኝ ሂደቶችና በእያንዳንዱ ፈታኝ ጉዞ ይዞት የሚመለሰው ድል ወይም ውጤትበተለይም በድምሩ በፍለጋ የተሰማራባቸውን ዕፆች እና የመዳብ ሣጥን በማግኘት የተፈጸመው አስደማሚ ጉዞ ማሳያ ነው፡፡ በዚህም ለምን ብዙ ውጣ ውረዶችን አለፈ? በመጨረሻስ ምን አገኘ? ለሚሉት ጥያቄዎች መልስ ተሠጥቷል፡፡ሌላው በዚህ ጽንሰ ሃሳብ ውስጥ የሚነሳው ነው፡፡ ውስጣዊ ጉዞ በአንድ ቀን ውሎ አንድ ስፍራ ተቀምጦ በሃሳብ ብዙ ቦታ መድረስ፣ የተለያዩ ነገሮችን በማሰብ ረጅም መንገድ የመኳዝ ሂደት እንደሆነ በምዕራፍ ሁለት ላይ እንደተጠቀሰው፡፡ በዚህ መሰርት በተለያዩ ቦታዎች ላይ ወጣ ገባ የሚሉ ምናባዊ ጉዞዎች በበልቦለዶቹ ውስጥ የታዩ ሲሆንለምሳሌ በመርበብት ልቦለድ ሲሳይ በምናብ ምጥቅ ብሎ በመሄድ ጎረጎራ ከሐውልቱ ስር ቆሞ የጣና ሐይቅ ሰፊ ክፍል በእንቦጭ አረም መጠቃት ከሲስፈስ መርገምት ጋር በማነፃፀር የሚተርክበትን ሂደት ተጠቃሽ ነው፡፡

> …በዚህ መሀል ስሜትን የሚጎዳ አንድ እይታን መሸሽ ግን አይቻልም፡፡ የሲሳይ የመንፈስ እርካታ ከብት እንደረገጠው ምንጭ ወዲያው ጎሸና ተረበሸ፡፡
>
> በስተተሰሜንና በስተምስራቅ ያለው የጣና ሐይቅ ሰፊ ክፍል በእንቦጭ አረም መጠቃቱ በግልፅ ይታይ ነበር፡፡
>
> በንዝሕላል ዘመን፣በነግዴለው ትውልድ ፣ በቢሮክራሲግርሻት፣ በፉክክር ዛር በቅዱሱ ሐይቅ ላይ የተፈፀመ የቃል ኪዳን ጥሰት ነው፡፡ እንቦጭ! በአንድ ሀሳብ የማይሥማማው አመንዝራው እሳቤያችን ያመጣው ቂጥኝ፣ ችግርን በወቅቱ ለመፍታት የሚያንደፋድፈን ስንፍናችን ያስጫረው እከክ፣ በደንቆሮ ግብርናችን በተራሮቻችን ላይ የፈፀምነው ግፍ ያሳደገው ካንሰር ነው፡፡ እንቦጭ! ሳይንሳዊ ስልትና ግብ የማያውቀው የታይታው ስራችን የምስኪኑን አርሶአደር ልፋት ጭምር "የሲሲስፈስ መርገምት" ስራ አደረገበት እያለ ያልጎመጉም ጀመረ፡፡
>
> ሲስፈስ በግሪክ አፈታሪክ ውስጥ በአማልክት መርገምት የተፈረደበት ሰው ነበር፡፡ ፍርዱም ትልቅ ቋጥኝ ከተራራ ጥግ አንስቶ እየገፋ ወደ ተራራ ጫፍ ማውጣት ነበር፡፡ ቋጥኙ ከተራራው አናት ሲደርስ ተንከባሎ ወደ ነበረበት ይመለሳል፡፡ ሲስፈስ እንደገና ወደ ተራራው አናት መግፋት ይጀምራል፡፡ ቋጥኙ አሁንም

መልሶ ይንከባለላል፡፡ እንደገና ይገፋል፤ ለዘላለም! ማብቂያና መቋጫ የሌለው ስራ፣ ውጤት የሌለው ተግባር ያከናውን ዘንድ የተፈረደበት ሰው ነበር ሲስፈስ፡፡ በማያዳግም ሁኔታ ነቅሎ መጣልና ማጥፋት ሲገባን እንደ ብጉንጅ ቁስል ዳርዳሩን ነካክተን እንተዋለን፡፡ እንቦጭ ሆዬ እንደ ሲስፈስ ዘላለም እንድንገፋው በሰራነው ልክ መልሶ ይተካል… (ከ176-177)

ከዚህ በላይ በቀረበው ሃሳብ የጣና ሐይቅ በእንቦጭ አረም በስፋት መጠቃቱን፣ በሲሳይ መላምት አረሙ ወደ ሀገረ ኢትዮጵያ ሊገባ የቻለባቸውን ምክንያቶችን፣ ለችግሩ ሳይንሳዊ በሆነ መልኩ እልባት መስጠት አለመቻሉ፣ በትውልዱ ዘንድ ምን ቸገረኝነት በስፋት መታየቱ በሀገራዊ ጉዳዮች ላይ የጋርዮሽ አስተሳሰብ ማጣትና በቶሎ አፋጣኝ መፍትሄ ካልተወሰደ አረሙ በሐይቁ ላይ ከፍተኛ ጉዳት እንደሚያደርስና ብዙ ዋጋን ሊያስከፍል እንደሚችል ወዘተ. በገፀባህሪው ህሊናዊ ጉዞ ውስጥ ታይተዋል፡፡ይህ ለእያንዳንዱ በአእምሮ ውሰጥ ለሚመላለስ ምርምር ቀመስ ጥያቄ መልስ ለመስጠት መፈለግና መዘጋጀት ሲገፋም ንቡር ጠቃሽ ለማድረግ መሞከር የነበረ፣ ያለና የሚቀጥል የሰው ልጆች ባህርይ ነው፡፡ይህንን ሰዋዊ ባህሪይ በመንተራስም አለማየሁ እንደ ደራሲ በስራዎቹ ውስጥ ሰዋዊ ጥያቄዎችን እየፈጠረ እና ሚታዊ ተረኮችን በማጀቢያነት እያበጀ ታሪኩን ሲያወዳጅ ይስተዋላል፡፡

ቅጽር መዝለቅ ነውቅጽር መዝለቅ ተጋዳሊው ከመጀመሪያው ተጋድሎ ጀምሮ እስከ መጨረሻው የተጋድሎ ደረጃ የሚያልፋቸውን ሂደቶች የሚመለከት ሽግግር ነው፡፡ ተጋዳሊው የሚጋደልለትን ጉዳይ ከግቡ ለማድረስ የሚደርስበትን መከራ ሁሉ ችሎ እስከ ሞት ድረስም ቢሆን ታምኖ መኳዝ የግድ እንደሚለው በተጋድሎው በስጋውም ሆነ በነፍሱ አያሌ መከራዎችን ሊያስተናግድ እንደሚችልምራፍ ሁለት ላይ ተገልጿል፡፡በአጥኚዋ እምነት በዝጎራ የሞገደኛውን ደን የሳይት 09ን ሚስጥር ለመፍታት፣ በመርበብት ደግሞ ለ350 ዓመታት ከነምስጢሩ በሐይቅ ውስጥ ተደብቆ የቆየን ሳጥን ፈልጎ ለማግኘት የሲሳይ መታጨት በራሱ እንደ መጀመሪያ ሽግግር ሊቆጠር ይችላል፡፡ ምክንያቱም ከዚህ በፊት ከሚያውቀው አለም ተለይቶ እንግዳ ወደ ሆነው ዓለም ሊቀላቀል በመሆኑ፡፡ በተጨማሪም የእነ አባ መዝገበ ስላሴን ቁልፍ ምስጢር ጠባቂነትና ይህን ለማለፍ የገጠመው ፈተናና እልህ አአስጨራሽ ትግልም ሌላው ማሳያ ነው፡፡

…ተነስቼ እግራቸው ስር ተደፋሁና ‹አባ በፈጣሪ ይዤዎታለሁ ይንገሩኝ አልኳቸው፡፡

ኧረ በፈጠረህ ተነስ፣ ምነው ልጄ ምን አደረኩህ?› አሉ በእጃቸው ጭንቅላቴን ይዘው እንድነሳ እየገፉኝ"

ተነሳሁና ቆሜ ‹ለምን ነግረው አያሳርፉኝም? አልኩ በምሬት፡፡

ልጄ እኔ የቤተ ክርስቲያኑ ዕቃ ቤት ጠባቂ የሆንኩ ተራ መነኩሴ ነኝ፡፡ ወደዚህ ምስጢር ዘልቄ የመናገርና የማስረዳቱ ዕውቀቱም ስልጣኑም የለኝም አሉ፡፡› ፈርጠም ብለው፡፡

ከመጀመሪያው ጀምሮ ሁሉንም ያውቃሉ፡፡ ከወደኩበት አንስተው ያመጡኝ፣ምን እንደሆንኩም የሚያውቁ እርስዎ ብቻ ነዎት፡፡

አባታችን ሊነግሩኝ ስላልፈለጉ እንጂ ያውቃሉ፡፡

ለምን አልከፉ አባታችን ፣ ትናንት ያየኋቸውን ቅዱሳን ማንነታቸውን ንገሩኝ ብልዎት እርሶም ፍቃደኛ አልሆኑም…

…የተለመደው የስራ ዜማ ተጀመረ፡፡ እኔም ማስታወሻ አውጥቼ መሞነጫጨር ጀመርኩ፡፡ በመጣሁበት ጉዳይ ላይ አባ ምንም ዐይነት ፍንጭ እንደማይሰጡኝ ተረዳሁ፡፡ (ዝጎራ፣282-294)

ከፍ ብሎ የቀረበው ሃሳብ እንደሚያሳየው ሲሳይ በተለያዩ ጊዜያት በተደጋጋሚ ማወቅ ስለሚፈልገው ነገር አባ መዝገበስላሴን እየደጋገመ ቢጠይቃቸውም ከሳቸው ዘንድ ስለ ጉዳዩ የሚሰጥ ምንም ምላሽ ግን አልነበረም፡፡ይህም የሚያሳየው ቅፅሩን ማለፍ ምን ያህል ከባድ እንደነበረ ነው፡፡ አንድም የቅፅሩ ጠባቂዎች (እነ አባ መዝገበስላሴ) በቅፅር ጠባቂነት የቆሙለትን ዓለም ከመጠበቅና ምስጢራቱንም ከመሸሸግ ባሻገር ተጋዳሊው ቅፅሩን መዝለቅ የሚችል ሰው እንደሆነ መፈተኛ መንገድም ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ በመሆኑም ይህም የቅጽር መዝለቅ አንዱ ሂደት ሆኖ ይታያል፡፡

ኃይለ ጊዮርጊስ› አሉኝ በክርስትና ስሜ፡፡ መጀመሪያ እንደመጣሁ አስቡኝ ብዬ ነግሬያቸው ነበር፡፡ እስካሁን አንድ ጊዜም ሳያነሱት አሁን በዚህ ስም ሲጠሩኝ ልቤ ድንግጥ አለ፡፡

ምኞትህና ፍላጎትህ ምን እንደሆነ አውቃለሁ፡፡የተማርከው ትምህርት ብዙ እንድትጠይቅ እንደሚገፋህ እረዳለሁ፡፡ የሆነው ሆኖ ማወቅ የምትፈልገው ነገር በእኔም በአንተም ፍላጎትና እውቀት የሚሆን አይደለም፡፡ ለማንኛውም ፍላጎትህና

ጉጉትህ ከክፋት የመነጨ ባለመሆኑ የቦታውን ምስጢር ላማወቅ ከሚፈቅዱ መልእክት የገሮልሃለሁ› አሉ ፈገግ ብለው፡፡ (ዝጎራ፣ 299)

በዚህ መልኩ ቀደም ሲል የተገለፁትን ፈተናዎች በትዕግስት አልፎ ምክራቸውን እየሰማ በብዙ ትዕግሥት የምስጢሩን መፍቻ ቁልፍ ከአባ መዝገበ ስላሴ እጅ ለመቀበል መብቃቱም እንዱ ቅፅር መዝለቅ ነው፡፡ ከዚህ የሚከተለው ደግሞ የሞት ሽረት ትግልን የሚጠይቀው የመጨረሻ ቅጽር መዝለቅን የሚመለከተው ጉዳይ ነው፡፡ ይህ ቅጽር የሚፈለገው ነገር ቅርስም ይሁን በረከት ወይም አንድ ውድ ተፈላጊ ነገር ያለበትን ቦታ ማግኘትና መግባትን የሚመለከት ሂደት ነው፡፡ ተፈላጊው ነገር የሚገኝበት ጥበቃው ጠንካራ የሚሆንበት አደገኛ ጠባቂዎች የሚበዙበትና ልዕለ ተፈጥሮ ሃይልም የሚከሰትበት አደገኛ ቦታ ሊሆን ይችላል፡፡ አርበኛውም በዚህ የሚያደርገው ተጋድሎና ውጤቱ የትልሙ ወሳኝ አካል ነው፡፡ በተመረጡት ልቦለዶች ውስጥም ይህ ሂደት በግልፅ ይታያል፡፡ በዝጎራ ቀደም ሲል እንደተገለፀው ሲሳይ በመጀመሪያው ቅፅር ዘለቃ ከአባ መዝገበስላሴ ብራናውን ከነትእዛዙ ከተቀበለ በኋላ ይዟቸው እንዲመለስ የታዘዛቸውን ዕፆች ለማግኘት በተለያዩ ስፍራዎች በሚገኙ አድባራትና ገዳማት በመሄድ ብዙ ውጣ ውረዶችን ሲያልፍ ይታያል፡፡ በመርበብትም እንዲሁ ከጣሊያን ሲሲሊ ከሚስተር እስጢፋኖ እጅ የአደራ መልእክት ተቀብሎ፣የናታንያን ወጥመዶች አልፎ ወደ ኢትዮጵያ ከገባበት ሽግግር ጀምሮ፣የመልእክቱን ምንነት ለመረዳት ስሄድባቸው የነበሩ መንገዶች አድካሚነት፣ መልእክቱን ከተረዳ በኋላ የተባለውን ነገርና ያለበትን ስፍራ ለማግኘት ሲያደርጋቸው የነበሩ መውጣትናመውረዶች፣ የመዳቡን ሳጥን ካገኘም በኋላ ያጋጠሙት ፈተናዎችና ፈተናዎቹን ለማለፍ የሚያደርገው ትግል ምን ይመስል እንደነበር በስፋት በሚታዊ ሁነቶች አማካኝነት ታትቷል፡፡ በተጨማሪም ቅጽሩን የማለፍ ሂደቱ ምን ያህል እየ ከበደና እየ ተውሰበሰበ እንደ ሄደና ተጋዳሊው እንዴት አሸናፊ ሆኖ እንደ ዘለቀ በልቦለዶቹ ልብን በሚያንጠለጥል መልኩ ቀርቧል፡፡

በመጨረሻም ቅጽርን የማለፍ ሂደቱ የሚጠናቀቀው በታዘዘው መሰረት እጾቹን ከተባሉበት ስፍራ፣ ሳጥኑን ከሐይቅ ውስጥ አውጥቶ ይዞ በቅዱሱ ስፍራ በመገኘት እና በተጨማሪም ደግሞ ተመራማሪ ማለት ሁሉንም ምስጢር የሚፈታ ማለት እንዳልሆነና ምርምር ሁሉን ነገር ለማወቅ ብቻ እንደማይደረግ ይልቁንም ከሳይንሳዊ እውቀት በላይ

የሆኑ ነገሮች መኖራቸውን፣ ሳይንሱ ከሚያስገነዝበው ጥበብ በላይ የመጠቀ ኩነት መኖሩንም ማወቅ በራሱ አንድ የምርምር ውጤት መሆኑን በተደጋጋሚ በተደረገው ያልተሳካ ሳይንሳዊ ሙከራ መረጋገጡና የሲሳይም ይህንን አምኖ መቀበል በራሱ እንደ መጨረሻ ቅፅር መዝለቅ ሆኖ ሊወሰድ ይችላል፡፡ ደራሲው እነዚህን ከላይ የተገለጹትን የሚት ዓላባውያን በልቦለዶቹ ውስጥ በመገልገሉ ከጅምሩ ገፀባህርያቱ ወደዚህ ጉዳይ እንዴት ሊገቡ እንደቻሉ፣በእያንዳንዱ ታሪክ ውስጥ ያሉ ድርጊቶች በምን ምክንያትና እንደተደረጉና ለምን እንደ ተደረጉ በማሳየት ከመነሻ እስከ መድረሻ ያሉት የልቦለዶቹ ታሪኮች ውል እንዲኖራቸውና አንዱ ታሪክ ሌላኛውን ታሪክ እንዲስብ ወይም እንዲጠራ እንዲያደርግ አስችሎታል፡፡

ባጠቃለይ ባለ መልኩ ሲሳይ ሳይት 09 ብለው በሰየሙት አንድ የቤተክርስቲን ደን ውስጥ ሳይንሳዊ ጥናት ለማካሄድ በሄደው ቡድን ላይ በገጠመው ፈተና መነሻነት የሚሽከረከረው የዝጎራ ልቦለድ እና የኢትዮጵያ ንብረት የሆነን ውድ ቅርስ የያዘን የተቀበረ መዝገብ በመፈለግ ላይ የሚያጠነጥነው የመርበብት ልቦለድ ፍለጋን (ምስጢር ገለጣን) ማዕከላዊ ጉዳያቸው አድርገው በሚያጠነጥኑባቸው ልቦለዳዊ ታሪኮች ምስጢሮቹ የሚፈቱት በሚታዊ ሁነቶች ነው፡፡ ለምሳሌ በዝጎራ ልቦለድ ሲሳይ ከአባ መዝገብ ሥላሴ የብራናውን ጥቅል በሚቀበልበት ታሪክ፣ የልቦለዱ ውስብስብ ታሪክ መፍቻ የሆኑት ምስጢሮች የሚፈቱበት ሚታዊ ሁነት የሚሰጠው በምስጢር ነው (ገጽ፣14)፡፡ እዚህ ቦታ ላይ ብራናውን ዋጋ የሌለው አድርጎ እንዳያይም ይባል አስተውሎ ቢመረምር የወደፊት መድረሻውን እንዲተነብይ የቀረበው የዮሐንስ ራዕይ፣ ‹‹ከእንግዲህ ወዲህ ሌሊት አይሆንም፤ ጌታ አምላክም በእነርሱ ላይ ያበራላቸዋልና የመብራት ብርሃንና የፀሐይ ብርሃን አያስፈልጋቸውም፤ ለዘላለም እስከ ዘላለም ይነግሳሉ›› (ገጽ15)፡፡ የሚለው የልቦለዱን ታሪክ ከሚታዊ ልቦለዶቹ አስተሳስሮ የሚያስኬድ በአንድ በኩል ጠንካራ ማገር በሌላ በኩል ብሩህ ተስፋ ያዘለ ንግር ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል፡፡

‹‹ከእንግዲህ ወዲህ›› ሲል፣አንድም ከዘመናዊ እውቀት ውጭ ባሕላዊና ሀይማኖታዊ እውቀት መኖሩን በሲሳይ የተወከለው ወጣት ትውልድ መመርመር ከጀመረ ወዲህ፣ አንድም የሰው ልጅ እየገጠሙት ያሉትን ችግሮች የሚፈታውና የተደበቁትን ምሥጢራት የሚገልጠው፣ በራሱ የፈጠራ ውጤት በሆነው ሳይንስ ብቻ ሳይሆን፣ በፈጣሪው ረዳትነትና ፈቃድ መሆኑን ከተረዳበት ጊዜ ጀምሮ ማለቱ ይሆናል፡፡ለዚህ

ማስረጃ የሚሆነው ደግሞ ገጽ 15 ላይ የተተነበየው የዮሐንስ ራዕይ፣ ሲሳይ ሶስቱን እጸች ለመሰብሰብ በኳተነባቸው ቦታዎችና እነሱን አሰባስቦ ዘመናዊ የሳይንስ ውጤቶችን ሁሉ ሞክሮ ጥረቱ ከንቱ በሆነባቸው ቦታዎች ሁሉ የትርጎማ ጥረት ሲደረግበት ቆይቶ ገጽ 313 ላይ በፍጹም ስውራኖቹና በገዳማውያኑ መካከል ካሉት አባት መገለጥና መገናኘት ጋር የሚፈታ መሆኑ ነው፡፡

በዚህ የታሪክ ጉዞ ልቦለዱ አፈታሪክን በስነቃል እያዋዛ ሲጓዝ ከተጨባጩ እውነታና ከዓለማዊው እውቀት ውጭ በሆነ መንገድ የተሳጉት በእምነት የታሹ ሚታዊ ሁነቶች የልቦለዱ ታሪክ እንዲያጓጓ፣ ባህላዊ ለዛን በተላበሰ ቃና ትስስር ፈጥሮ እንዲጓዝ ጉልህ ድርሻ ተወጥተዋል ለማለት ይቻላል፡፡

ለምሳሌ በዝጎራ ረጅም ልቦለድ ሳይት 09 ደን ላይ ሳይንስን የገጠመውን ፈተና ለመፍታት ሲሳይ ምስጢራዊ እጸቹን የሚያገኝባቸው በአጋጣሚ ላይ የተመሰረቱ ሚታዊ ሁነቶች የልቦለድ ታሪኩ እድገት እድገቱን ጠብቆ እንዲገሰግስ ቁልፍ ሚና ተጫውተዋል ለማለት ይቻላል፡፡

> የማሕበረ ሥላሴው ገዳም አባት ስለቦታው ሲተርኩለት፣
> የሚገርምህ ይህ ዛፍ ከክረምት ይልቅ በበጋ እጅግ ይለመልማል፡፡ ...
> አጋጣሚውን ተጠቅሜ ወደ እኔ ጥያቄ ለመንደርደር ፈለኩና፡-
> ስሙ ምን ይባላል?›› አልኳቸው፡፡
> ሲና እንለዋለን›› ሲሉ ሰውነቴ ስንጥቅ አለ፡፡ (ገጽ፣106)

የልቦለዱ ታሪክ እንዳይቋረጥ ወይም በጥቅጥቅ ጫካ ውስጥ ይህንን እጽ ለመፈለግ በሚጠይቀው ረዥም ጊዜ እንዳይጓተት ይህ በዘመናዊ ልቦለዶች እንደሚታዩት ሁነቶች በምክንትና ውጤት ሳይሆን በአጋጣሚ የሚፈጠር ሁነት ለታሪኩ መቀጠል ብቻ ሳይሆን ተንዛዝቶ አሰልች እንዳይሆን የሚኖረው ሚና ቀላል አይሆንም፡፡

ሲሳይ እጸ ሲናውን ይዞ ወደ ሁለተኛው እጽ መገኛ ወደ አባጸንጠሊዎን ገዳም ተጉዞ አባወልደአረጋዊ ስለአካባቢው ገለጻ እየሰጡ ስለገዳሙ የሚነገረውን የዐፄ ካሌብን አፈታሪክ ሲተርኩለት[2]፣ እዚያ ቦታ እንዲያመጣ የተነገረውን እጸጎርመትን በአጋጣሚ ያገኛል፡፡

---

[2]ይኸ አፈታሪክ ራሱ ሚታዊ አፈታሪክ መሆኑን ልብ ይሏል፡፡

እናም ዐፄ ካሌብ በዚህ ሁኔታ ሠራዊታቸውን ካሰናበቱ በኋላ ዙፋናቸውንና በትረ መንግሥታቸውን ለልጃቸው ለዐፄ ገብረ መስቀል አውርሰው እዝች ድንጋይ ላይ ...የተቀመጥንባትን ድንጋይ እያሳዩ ‹‹ልብሰ-መንግሥታቸውን አውልቀው ጸጉራቸውን ተላጭተው የምንኩስና ቆባቸውን ጭነው ወደ ምናኔ ዓለም ገቡ›› አሉኝ፡፡

በጣም ይደንቃል!›› ስል

‹እና በዚህ የተነሳ ይህች ስፍራ ‹መካነ ኀርመት› ትባላለች!›አሉኝ፡፡ (ገጽ 144-5)፡፡

ይህ በአጋጣሚ ላይ የተመሰረተ ሚታዊ ሁነት ወደሌላ ሶስተኛ ሚታዊ ሁነት እንዲሻገር ሲያደርገው የታሪኩ ጉዞ ፍጥነት ይጨምራል፡፡ ይህም የአንባቢውን ጉጉት ከፍ ያደርገዋል፡፡

ሶስተኛውን እጽ ወደሚያገኝበት ወደ ይምሃረነ ክርስቶስ ገዳም አምርቶ ገዳሙ ውስጥ እጹን ፍለጋው አታክቶት ወደሸለቆ ሲወርድ ይወድቃል፡፡ አባወልደአረጋዊ ደርሰው ጸበልሲረጨት እጹ ይገለጽለታል፡፡(ገጽ፣ 168)፡፡

ሲሳይ እነዚህን በተዓምር ወይም በቅዱሳኑ እርዳታ በተሞሉ ሚታዊ ትርክቶች (የልቦለዱ ታሪክ ማገናኛ ድልድዮች  ሊባሉ በሚችሉ ሁነቶች) አልፎ የተሰጠውን ግዳጅ ተወጥቶ በዘገየ ቁጥር እንደምንጣፍ እየተጠቀለለ ወደእርሱ የሚጠጋውን እድሜውን ለማርዘም ይጣደፋል፡፡

በአጠቃላይ ከዚህ በላይ ከልቦለዶቹ ታሪኮች ማስረጃዎችን እየወሰድን ለማየት እንደሞከረነው በድንገትና በሌላ ሀይል እርዳታ የተፈጸሙት ሚታዊ ድርጊቶች ለልቦለዱ ታሪክ ትስስር፣ ተቀባይነት (በልቦለድ ያለምክንያት በድንገት የሚፈጸሙ ሁነቶች ተአማኒነትን ስለሚያሳጡ እንዲገቡ እንደማይመከር ልብ ይሏል) እና ፍጥነት (አጓጊነት) የራሳቸውን ጉልህ አስተዋጽኦ አድርገዋል ለማለት ይቻላል፡፡

# ምዕራፍ አምስት

# ማጠቃለያ እና አስተያየት

## 5.1ማጠቃለያ

ጥናቱ በዝጎራና መርበብት ረጅም ልቦለዶች ውስጥ ያሉ ሚታዊ ባህሪ ያላቸው ሁነቶች ለልቦለዶቹ ታሪክ ማስኬጃነት ያላቸውን አበርክቶ የመረመረ ነው፡፡ ጥናቱ በሚቶሎጂና ስነፅሑፍ ትስስር ዙሪያ ባሉ ንድፈ ሃሳቦች መነሻነት ሁለቱን ልቦለዶች መርምሯል፡፡ ለዚህም ከልቦለዶቹ ታሪክ ውስጥ ለማሳያነት በተመረጡ ሚታዊ ባህሪ ባላቸው ሁነቶች ላይ ተመስርቶ ትንታኔ ተደርጓል፡፡ደሪሲው ስነፅሑፋዊ ስራዎቹን ለማደራጀት እና የልቦለዶቹ ታሪክ በሰመረ መልኩ ፍሰቱን ጠብቀው እንዲሄድ ሚታዊ ባህርያት ያሏቸውን ሁነቶች ስለመጠቀሙ እነዚህ ልቦለዶች ምስክሮች ናቸው፡፡የሚት ጠባያትን እና የሚት አላባውያንን ከልቦለዶቹ ታሪኮች ጋር ስምምነት እንዲኖራቸው አድርጎ ሀሳቡን ለማስኬጃነት የተገለገለባቸው ሲሆን ከዚሁ ጋር በማያያዝ ሚታዊ ተረኮችን ተጠይቃዊ በሆነ መንገድ በማምጣት ለታሪክ ማደራጃነት ተገልግሏል፡፡ ይህም ደራሲው ሚቶሎጂያዊ ጉዳዮችን ለታሪኩ ቀጣይነትም ሆነ ማበልጸጊያነት ስለመገልገሉ ማሳያ ነው፡፡

የሁነቶች ተለጣጣቂነትን በመፍጠርበሚል በቀረበው የትንታኔው ክፍል ደራሲው ሚታዊ ባህርይ ያላቸውን ሁነቶች ለአደረጃጀቱ ተጠቅሞባቸዋል፡፡ ታሪኮቹ እንደ ሰንሰለት እርስ በእርሳቸው እንዲተሳሰሩ፣ ጉዟቸው የሰመረ እንዲሆን እና በታሪኩ ውስጥ ለተነሱ ጥያቄዎች መልስ በማስገኘት ረገድ የጎላ አስተዋፅኦን አበርክተዋል፡፡ እንዲሁም በመጻህፍቱ የታሪክ ፍሰት ደራሲው የልቦለዶቹን ታሪኮች የሚያፋፉና የሚያዳብሩ መረማመጃ ድልድይ የሆኑ ሚታዊ ተረኮችን በታሪኮች መካከል በመፍጠር ከአንድ ድርጊት ወደ ሌላ ድርጊት የሚደረገው ሽግግር እንደው ዘው ተብሎ የማይገባበትና ከአንዱ ሁነት ወደ ሌላው ሁነት የሚደረገው ተስተላልፎ ተጠየቃዊ ቅደም ተከተል ያለውና ባለታሪኮቹ የተለያዩ ድርጊቶችን በመፈፀም ማንነታቸውን፤ የሚደርስባቸውን ክፉም ሆነ ደግ ነገር የሚያሳይ ነው፡፡ ለዚህም በማስረጃነት የሚቀርበው የሚት ተረክ በተጋድሎ የተሞላ እንደሆነ ሁሉ በሁለቱ ልቦለዶች ውስጥም ዋናው ገፀ ባህሪ በየታሪኩ ብዙ ውጣ ውረዶችን (ተጋድሎዎችን) እያደረገ

የተሰጠውን ትዕዛዝ እና አደራ ሲፈፅም ይታያል፡፡ በዚህም ደራሲው የስነፅሑፎቹን ትልም የገነባ ከመሆኑም ባሻገር ታሪኮቹን ልብ አንጠልጣይ በሆነ መንገድ ማቅረብ እንዲችል አግዞታል፡፡

እንዲሁም ወጣ ያሉ (ያልተለመዱ) ገፀ ባህርያትን በመጠቀም ታሪኩ የፍሰት አቅጣጫውን እየቀያየረ አንዱ ሌላውን እየጠራ አብሮ እንዲዘልቅ ማድረግ የቻለ ሲሆን ለዚህም በአብዛኛው የሰው ልጅ ዘንድ ተዘውትሮ የማይተገበረውን መናፍስትን የማናገር ጥበብ ዋናው ገፀባህሪ ከማናፍስት አለቃ ራሙኤል ጋር  በሚያደርጋቸው ምልልሶች ቀደም ብለው በቀረቡት ታሪኮች ለተነሱ መልስ ፈላጊ ሃሳቦች መልስ በማስገኘትና ድልድይ በመሆን የፊተኛው ከኋለኛው ታሪክ ጋር ትስስር እንዲፈጥር ማድረግ አስችሏል፡፡እንዲሁም በ ቤተክርስቲያኑ ደን (ሳይት 09) ውስጥ ሲከሰቱ የነበሩ ከሰው ልጆች ጥበብና አስተውሎትየረቀቁ ድርጊቶች ገፀባህሪውን የመደመም ስሜት ውስጥ ከተው የተለያዩ ጥያቄየዎችን ሲፈጥሩበት ይታያል ጥያቄዎቹ ባቀረቡት ጥሪ መሰረትም መልስ ሰጪ ታሪኮች ወደ ታሪኩ ዘልቀው በመግባት የልቦለዶቹ ይዘት ሰፊ እንዲሆን አድርገውታል፡፡በጥቅሉ በዝጎራም ሆነ በመርበብት የተነሱት ታሪኮች የሀይማኖትና ሳይንስ ዘመን አዛንቀው የያዙ፣ ባሕልና ስልጣኔን የሚያሚግቱና በእነዚህ ጥንዳዊ ተቃርኖዎች መካከል የምትውተረተረውን ህይዎት ልዩ ልዩ መልኮች በሚትና ልቦለድ ተደጋግፎ የሚፈነትዉ ናቸው፡፡

በልቦለዶቹ ታሪክውስጥ ከዋናው ታሪክ በተጨማሪ ብዙ ታሪካዊ፣ሳይንሳዊ እና ሀይማኖታዊ ንዑሳን ታሪኮች ዋናውን ታሪክ በሚያጎለብት መልኩገብተዋል፡፡ በተነሱት ታሪኮች ላይ ሚታዊባህርይያላቸው ሁነቶችተጨምረውና  ተደራጅተው ሲቀረቡም ይስተዋላል፡፡በዚህም በሚታወቁ ታሪካዊ ገጠመኞችና ሐይማኖታዊ ጉዳዮች ተንተርሶ ያልተዳሰሱ ሃሳቦችን አጉልቶ የሚያሳዩ አቀራረብ ያለቸው የአለማየሁ ስራዎችበውስጣቸው የተለያዩ ዘመናዊ አስተሳሰቦችንምይዘዋል፡፡ ደራሲው  ሀሳቦችን ለማዘመን  እንዲረዳው የስነ ምህዳር ሳይንስን ከሚታዊ ሁነቶች ጋር እያዋዛ  ታሪኩን ማቀናበር ችሏል፡፡በዚህም በስነ ፅሑፍ ስራዎቹ ውስጥ የሚመጡ ሚታዊም ሆኑ ታሪካዊ ጉዳዮች እውናዊ ትረካዎች እንዲመስሉ አድርጓል፡፡ በመሆኑም  በዚህ መልኩ በማደራጀትና በመተረክ  በተለየና በአዲስ እይታ ለአንባቢ መድረሱ ደራሲውን ሚቶ ከያኒ አድርጎታል፡፡

ጉዞ ትልም(ምንን እና ለምንን)በማሳየት በሚለው የትንታኔ ክፍል የሚት አላባውያንን መሰረት በማድረግ በተለዩት ሚታዊ ጉዳዮች ላይ በተደረገው የትንታኔ ክፍል ደራሲው በሚት ታሪክ ውስጥ ጎልተው የሚታዩትን የሚት አላባውያን በታሪኩ ውስጥ በመጠቀም በልቦለዱ ታሪክ ውስጥ ምን ለምን ለሚለው ጥያቄ ማለትም የገፀ ባህሪያቱን የአጠራር ሁኔታ፣ ከአንድ ቅፅር ወደ ሌላ ቅፅር የሚደረገው ሽግግርና የሽግግሩን ሂደት፣ የፍለጋውን የጉዞ ምክንያት እናውጤት የሚያሳዩ ሁነቶችን ወደ ታሪኩ በማስገባት ታሪኩን ተአማኒ ማድረግ ከመቻሉም ባለፈ ሀሳቦች ምክንያታዊ በሆነ መልኩ ትስስር ፈጥረው ታሪኮቹ ወደ ፊት እንዲቀጥሉ፣የታሪኮቹ ይዘት እንዲሁ ሳይሆን በሰበብ እንዲሰፋ  ማድረግ የቻለበት መሆኑን በማሳየትትንታኔ የተሰጠበት ክፍል ነው፡፡ በዚህም ደራሲው በስፋት በየምዕራፉ ለሚነሱ ጥያቄዎች ሚታዊ ባህርያት ባላቸው ሁነቶች አማካኝነት መልስ  እንዲያገኙ በማድረግ ተአማኒነትን መፍጠር ከመቻሉ በተጨማሪ ታሪክ እራሱ ታሪክን እንዲጠራ እና የልቦለዶቹ ታሪክ በተጠየቅ ወደፊት እንዲዘልቅ ማድረግ መቻሉ ታይቷ፡፡ እንዲሁም ሚታዊ ሁነቶችን በድንገት እንዲከሰቱ አድርጎ በልቦለዶቹ ታሪክ ውስጥ በማስገባት ረጅም ሂደትን ይጠይቁ የነበሩ ታሪኮች በተገቢው መልኩ አጥረው ሳይንዛዙና አሰልቺ ሳይሆኑ እንዲቀርቡ እና የታሪክ መቆራረጥ እንዳይኖር አድርጓል፡፡

አለማየሁ ዘመኑን የዋጁ ጭብጦችን በዘመናዊ የአማርኛ ረጅም ልቦለዶች ከሚያነሱ ስመ ጥር ጸሐፊዎች መሃል ሊመደብ የሚችል ይመስለኛል፡፡ ከ2007 ዓ.ም ጀምሮ በተከታታይ እያሳተመ ባወጣቸው ሦስት ስነ ጽሑፋዊ ስራዎቹውስጥ የሚገለገልባቸው የአፃፃፍ ብልሃቶች ዘመናዊነትእና የሚያነሳቸው ወጥነት ያላቸው ጭብጦጭከላይ ላነሳሁት ሃሳብ ተጠቃሽ ምክንያት ይመስለኛል፡፡ በተለይ በነዚህ ሁለት ልቦለዶች ውስጥ እንደሚታየው እያንዳንዱ ልቦለድ በራሱ የተሟላ ከመሆኑ ባሻገር በልቦለዶቹ ውስጥ ያሉ ታሪኮች በአንድ የሚገናኙበትን መዋቅራዊ ትስስር በመፍጠር ዘላቂነት ያለውና የሚያድግ ጭብጥን ሲፈጥር ይታያል፡፡ ይህም ተደራሲያን ለእያንዳንዱ ታሪክ እንግዳ እንዳይሆኑና በልቦለዶቹ ውስጥ ባሉ ታሪኮች መሀል ያለውን የጭብጥና መዋቅራዊ ትስስር እንዲፈልጉ የመመርመር ነፃነት የሚሰጥ ነው፡፡

ሐለቱ ልቦለዶች በተለያዩ ሚታዊና ስነፅሑፋዊ ትፅምርቶች የተበጁ በመሆናቸው በሚቶሎጂና ሥነ ጽሑፍ ምርምር ውስጥ እጅግ ገናን በሆነው የመባያ ጉዳይ ጽንሰ ሐሳብ ለመጠናት ምቹ ይመስሉኛል፡፡ ባጠቃላይ ከፍ ብዬ ለመግለፅ እንደሞከርኩትበስነፅሑፎቹ ታሪኮቹን የሚገናኙ መዋቅራዊ ትስስሮች መኖራቸው እና ዘላቂነት ያላቸውና የሚናበቡ ጭብጦች መታየታቸው መፃህፍቱን አንድ የሚያደርጋቸው አስተሳሳሪ ጉዳይ እንዳለ አመላካች ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ መነሻነት መፅሐፍቱ የሚጋሯቸው ጭብጦች እና ትፅምርታዊ ጉዳዮች ቢመረመሩ ከስነፅሑፋዊ ጠቀሜታቸው ባሻገር ስለ ማህበረሰቡ ብዙ የሚሉት ይኖራል የሚል እምነት አለኝ፡፡

## 5.2አስተያየት

በሥነጽሑፍእናበሚቶሎጂፅንሰሃሳብመካከልያለውግንኙነትየሰውንልጅእና የህይወቱን ትስስርመሰረትያደረገነው፡፡በሥነጽሑፍውስጥያለውንሚታዊሁነትመግለጥየሥነጽሑፍዋነኛጉዳ ይየሆነውንየሰውልጅ ህይወት መግለጥነው፡፡ የአማርኛሥነጽሑፍስለሰውልጅየሚያነሳቸውዝንቅሃሳቦችአሉት፡፡ ሆኖም እነዚህን ሃሳቦች በታለመው መሰረት ለተደራሹ(ለአንባቢው) ለማድረስ ደራሲው በመረጠው ዘዴ ታሪኩን ማስማማት የሚችል ሲሆን ዋናው ልብ ሊባል የሚገባው ጉዳይ ግን ታሪኩ የአንባቢውን ስሜት ነክቶ ቀልብን የመግዛት ሀይል ኖሮት ሳቢነቱ የጠነከረ ሆኖ የልቦለዱ ቁምነገሮች በአንድነት በጠበቀ ሁኔታ መቀናጀታቸው ላይ ነው፡፡ በተለያየ ዘዴ የተለያዩ ሁነቶችን በማቀናጀት ወደ አንድ አብይ ግብ ማምራት በተለያዩ የስነ ፅሑፍ ስራዎች ውስጥ የሚታይ ሀቅ መሆኑን የተለያዩ ጥናቶችንቅኝትበማድረግማየትይቻላል፡፡ በዋናነት ሚታዊ ባህርያት ያላቸው ሁነቶችና የልቦለድ ታሪክ እንዴት ባንድ ተሸርበው ተገኙ? (ሚታዊ ባህርያት ያላቸው ሁነቶች ለልቦለድ ታሪክ ማስኬጃነት ያላቸው አበርክቶምንድንነው?)የሚለውንበማጥናትግንይህጥናትየተለየነው፡፡ሆኖምጥናቱንከፅንሰሃሳቡም ሆነከሥነጽሑፉስፋትአንፃርካየነውውስንነው፡፡የተመረጡየአማርኛረጅምልቦለዶችላይበማተኮር ጥናቱሲካሄድ በቀጣይተመሳሳይጥናቶችንበሌሎችረጅምልቦለዶችላይበመስራት ሚቶሎጂና ስነጽሁፍያላቸውን ተዛምዶ በተለያየ መንገድመግለጥንታሳቢበማድረግነው፡፡

ቴዎድሮስ (2007) በብሌን መጽሔት ላይ "ሥነ ጽሑፍ እጅግ በፈጠነና በማያቋርጥ ለውጥ ውስጥ ያለ ኪን ነው፡፡ በዚህም ባህርይው በእጅጉ ተለጣጭ ከሆኑት የነገረ ሰብዕ ሐቲቶች

ጎራ ይሰለፉል፡፡ ሥነ ጽሑፍ ተለጣጭ ሐቲት ነው ስንል የሚቀርበው ጉዳይ፣ጉዳዩ የሚቀርብበት መንገድ፣ ሚናና ሙያው ከጊዜ ወደ ጊዜ ይቀያየራል፤እሱንም ተከትሎ ኪኑንም የምናነብበት፣ የምንመዝንበት መንገድ በአንድ አይረጋም፤ የምንመረምርበትም አናጻር በዓይነትም ይባል በመጠን ይለወጣል ማለታችን ነው፡፡" ሲሉ እንደገለጹትና በዚህ ጥናትም እንደታየው ልቦለድ የገሀዱ አለም ነጸብራቅ ነቱ እንዳለ ሆኖ በእውናዊው አለም ይከሰታሉ ብሎ ለመቀበል የሚከብዱ ነገር ግን ደሞ የሚከሰቱ ነገሮች መኖራቸውን በሚታዊ ሁነቶች እና በታሪካዊ ክስተቶች የጋራ ውህደት አማካኝነት መግለጥ እንደሚቻል መታየቱ በርግጥም ስነ ጽሑፍ እንደየዘመኑ ሊታይና ሊመረመር እንደሚችል ያሳያል፡፡

የአማርኛግጥሞች፣የአማርኛየተውኔትፅሁፎች እና አጭርልቦለዶችውስትሚታዊ ጉዳዮችንመመርመርለቀጣይጥናቶችየተመላከተስራነው፡፡

## ዋቢዎች


ለማ ንጋቱ፡፡(2002፣67-86):: የፎክሎር ኮርስ መግቢያ የማስተማሪያ መሳሪያ፡፡ጅማ ዩኒቨርሲቲ፡፡ያልታተመ፡፡

________(2008)፡፡ "ብቻ…ብቻ ምን ይሆናል…ል!"፤የ"ባህታዊ"ገፀ ባህርያት ስነ-ፅሑፋዊ ፋይዳፍከራ፣በፍቅር እስከመቃብርና በየቴዎድሮስ እንባ ረጅም ልቦለዶች፡፡የሀዲስ አለ ማየሁ የባህል ጥናት ተቋም አራተኛ ዓመታዊ አገር አቀፍ ዐውደ ጥናት መድበለ ጉባኤ፡፡ደብረማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ገፅ ፡፡

ስለሺ አስፋው ፡፡ (2009) ፡፡የእመን ረጅም ልቦለድ ፎክሎራዊ ፋይዳ ትንተና፡፡ጅማ ዩኒቨርሲቲ፡፡

ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህወዶ ቤተክርስቲያን፡፡(1993)፡፡መጽሐፈ ስንክሳር፡፡ አዲስ አበባ ትንሳኤ ማሳተሚያ ድርጅት፡፡

ባይለየኝ ጣሰው፡፡(1993፣29-45)፡፡ "ኦቴኖ ፡-የአኙዋ ባህላዊ ጀግና ፡፡ የኢትዮጲያ ቋንቋዎችና ሥነ ፅሑፍ መጽሄት ፡፡ቁጥር 10፣አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

ቴዎድሮስ ገብሬ፡፡ (2001) ፡፡ በይነ ዲስፕሊናዊ የስነፅሑፍ ንባብ፡፡አዲስ አበባ፡፡አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ፡፡

አፈወርቅ ገብረ ኢየሱስ፡፡(2000)፡፡ ጦቢያ፡፡ማተሚያ ቤት አልተገለጸም

ዘሪሁን አስፋው፡፡ (2007) ፡፡የስነ ጽሁፍ መሰረታውያን፡፡ አዲስ አበባ፡፡ ማህሌ ትአሳታሚ

ያለው እንዳወቅ፡፡(2009) ፡፡ የምርምር መሰረታዊ መርሆችና አተገባበር፡፡ አዲስ አበባ፡፡አልፋ አሳታሚዎች፡፡

ፈቃደ አዘዘ፡፡( 1991) ፡፡ የስነ ቃል መምሪያ ፡፡ አዲስ አበባ፡፡ አርቴስቲክ ፕሪንቲንግ ፕሬስ፡፡

Abraham, K. (1913). *Dreams and Myths: A Studying Race Psychology.* New York: The Journal of Nervous and Mental Disease Publishing Company.

Balaick,C.(2011).The concise oxford Dectionary of literary terms.2nd ed .New York.Oxford University press.

Baltes, B. and Staudinger, M. (2000). Wisdom: a Metaheuristic (Pragmatic) to Orchestrate Mind and Virtue toward Excellence. *The American psychological Association,* 55 (1) 122-136.

Bascom, W. (1965). The Forms of Folklore: Prose narratives. *The Journal of American Folklore,* 78 (307) 3-20.

Bell,M.(1997).Literatur.modern and Myth.Belief and Responsibility in the Twentieth century,New York.Cambridge University. press.

Brunvad, V. (1979).Reading American Folklore.

Campbell, J. 1994 (2004). The Hero with a thousand faces.3rded. New Jersey princetion University. press.

______________ (1949).*The Hero with a Thousand Faces.*New York: Pantheon Books.

Catherine, B. (1997). *Ritual: Perspectives and Dimensions.* New York: Published by Oxford University Press, Inc.

Danesi, M.(2004). Messages,signs,and meanings,3rd ed.Toronto ; Canadian scholars. press.

Davies, S.The Philosophy of Art.Mumbai; Blackwell Publishing Ltd, 2006.

Frazer, J. (1920). *The Golden Bough a Study in Magic and Religion.*3rd ed. London: Macmillan and co. limited

Huskinson, L.(Ed).Dreaaming the Myth Onwards. New York: Rutledge,2008.

James, W. (2007).*A Scientific definition of Religion.*Retrieved on March 10, 2015

Jung,L.The psychology of child Archetype>>.In sacred Narrative; Reading in the Theory of Myth.Dundes,Alan(ed) London University of Califomia press.

Kirk, G. (1973). *Myth: Its meaning and Functions in Ancient and Other Cultures.* Berkeley: University of California Press.

Lang, A. (1897). *Modern Mythology.*London: Long Mans Green and Co.

Larsen, S. (1990). The Mythic Imagination: Your Quest for Meaning Through Personal Mythology. New York: Bantam Books.

Leeming,David. (2002). Myth a Biography of Belief. New York,Oxford University Press

Levi-Strauss, C. (1963). *Structural Anthropology.*New York: Basic Books, Inc.

Lynch, A. (2004). *African Mythology A to Z.*New York.

Merkur, D. Psychoanalytic Approaches to Myth. New York: and London Rutledge,2005.

Mitchell, W.J.T. (1986). Iconology: Image, Text, Ideology. London; University of Chicago Press.

Norris, Nanette.(2010).Moderist Myth.Fergus; Dream Ridge publishing.press.

Pettazzoni, R. (1984). The Truth of Myth. In Alan Dundes (ed.), Sacred Narrative: Readings in the Theory of Myth (pp98-109). Berkeley: University of California Press.

Righter,W.(1972)."Myth and Interpretation",Inliterary History.Johns Hopkins University.press.

Rosenberg, H.The Anxious Object, Art Today and Its Audience.New York and Toronto; The New America library, 1969.

Sailors, L. (2007). *The Function of Mythology and Religion in Greek Society.* Unpublished Master‟s Thesis, East Tennessee State University.

Segal,Robert.A.(2004).Myth;Avery short Introduction. New York.Oxford University. press.

Spence, L. (1921). *An Introdution to Mythology.*New York: Moffat Yard and Company.

Thurschwell,P. and Sigmund F.London and NewYork:Routledge,2000

Tewodros,Gebre.(2010).”Myth and Sexuallity.A mythopetic Reading of letum Aynegalin”.Callalo.vol 33,no1 Johans Hopkins University. press.

Tylor.(1871). *Primitive Culture: Researches into the Development of Mythology, Philology, Religion, Art and Custom.*(Vol. II). London: Brad Bury Evans and Printers.

Vaughan, J. (1919). *Religion: A Comparative Study.* Appleton, Wisconsin.

Vico, G. (1948). *The New Science of Giambattista Vico.*(Bergin & Fisch Trans). New York: Cornell University Press. (Original Work Published in (1725).

Wellek, Rene and Austen, Warren.(1980). Theory of Literature.London; Pelican Books.

Wilson, W. (1979).Folklore and History. Facts Aimed to the Legends. Reading in Folklore.

# የኢንተርኔትምንጮች

Doyle and Flaten.(2004). *Mythology.*Retrieved on June 15, 2015, from http://www.pantheo. org/articles/m/mythology.html

Leonardo and Michael. (2003). *Myth and Knowing: An Introduction to World Mythology.*Retrieved on November 4, 2015, from www, Cuymaca. Edu/Kathryn .valdivia /mythology

Magoulick.*What is Myth?* Retrieved on December 13, 2015, from Hercules.gcsu.edu/ mmagouli/defmyth.htm.

Stenudd, Stefnn*The Logics of Myth - Basic Patterns of Creation Myths.* Retrieved on March 11, 2016, from *www.creation**myths**.org/**myth**logics-1.htm*

ጅማ ዩኒቨርሲቲ

የሶሻል ሳይንስና ሂውማኒቲስ ኮሌጅ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ- ጽሁፍ (አማርኛ) ትምህርት ክፍል

ድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

# ሚታዊ ሁነቶች ለታሪክ ማስኬጃነት ያላቸው አበርክቶ

# በዝጎራ መርበብት ልቦለዶች ማሳያነት

በ

ውብነሽ ወንድሙ

መስከረም 2012 ዓ.ም

ጅማ

# ሚታዊ ሁነቶች ለታሪክ ማስኬጃነት ያላቸው አበርክቶ

# በዝጎራና መርበብት ልቦለዶች ማሳያነት

ጅማ ዩኒቨርሲቲ

የሶሻል ሳይንስና ሂውማኒቲስ ኮሌጅ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ- ጽሁፍ (አማርኛ) ትምህርት ክፍል

ድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

በኢትዮጵያ ስነ-ጽሁፍና ፎክሎር ድህረ ምረቃ መረሀ ግብር ከፊሉን ማሟያ የቀረበ ጥናት

በ

ውብነሽ ወንድሙ

አማካሪ

ጌታቸው አንተነህ (PhD)

ሀብታሙ እንግዳው (MA)

መስከረም 2012 ዓ.ም

የሶሻል ሳይንስና ሂውማኒቲስ ኮሌጅ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ- ጽሁፍ (አማርኛ) ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

# ሚታዊ ሁነቶች ለታሪክ ማስኬጃነት ያላቸው አበርክቶ በዝጎራና መርበብት ልቦለዶች ማሳያነት

በ

ውብነሽ ወንድሙ

የፈተና ቦርድ አባላት

የአማካሪ ስም ፊርማ

______________________________ _______________

የፈታኝ ስም ፊርማ

______________________________ _____________

______________________________ ______________

# ምስጋና

በመጀመሪያ ስለ ሁሉም ነገር ቅዱስና ኃያል የሆነው አምላክ እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ፡፡ በማስከተል ከዚህ በታች የዘረዘርኳቸው ሰዎችና ተቋማት በተለያየ መንገድ ለዚህ ጥናት መሳካት የየራሳቸውን ድርሻ ያበረከቱ ናቸውና ምስጋና ይገባቸዋል፡፡ ለአማካሪዬ ዶ/ር ጌታቸው አንተነህ ከመጀመሪያው የትልመ ጥናት ንድፍ ጀምሮ ሲያደርጉልኝ ለነበረው ቅንነትና የተገባ አስተያየት መስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡ ሃሳቤን በማንኛውም ሰዓት በፍፁም ቅንነት እና ዕውቀት በመስማት ለማንበብ ፍፁም ፈታኝ የነበሩትን በተለያዩ ጊዜያት ያቀረብኳቸውን ንድፎች ያለመሰልቸት በማንበብ እና እርማት በመስጠት ከመስመር እንዳልወጣ በእጅጉ ላገዙኝ የእውቀት ብቻ ሳይሆን የህይወት  መምህሬ ለሆኑት ለዶ/ር ለማ ንጋቱ ልባዊ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡ እንዲሁም ፊር አልባ  የነበረውን የመጀመሪያ ንድፍ ፊር በማስያዝ ገንቢ አስተያየታቸውን ለሰጡኝ ረዳት አማካሪዬ ሀብታሙ እንግዳው ምስጋናዬ ላቅ ያለ ነው፡፡  እንዲሁም የትምህርት እድሉን ለሰጠኝ ለጅማ ዩኒቨርሲቲ ኮሚውኒቲ ትምህርት ቤት ከፍ ያለ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

ይህንን ጥናት በማካሄድበት ጊዜ ሁሉ ከጎኔ በመሆን ብዙ ውለታዎችን ለዋላችሁልኝ ቤተሰቦቼ ከፍ ያለ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡ ጓደኞቼም በዚህ ጥናት ላይ ድርሻ አላችሁና ምስጋናዬ ይድረሳችሁ፡፡

# አጠቃሎ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ *በዝጎራና መርበበብት* ልቦለዶች ሚታዊ ሁነቶች ለልቦለዶቹ ታሪክ ማስኬጃነት ያበረከቱትን  አስተዋጽኦ መተንተን ነው፡፡  የጥናቱ ዘዴ አይነታዊ ሲሆን የመተንተኛ ስልቱ ደግሞ ብዝሀ ግብር (multifunctionalism) ዘዴን መሰረት  ያደረገ ፍካሬ ነው፡፡ በመረጃ አሰባሰብ ሂደትም ለጥናት በተመረጡት የአማርኛ ረጅም ልቦለዶች(ዝጎራና መርበብት) መፃህፍት ውስጥ ሚታዊ ባህርያት ያሏቸውን ሁነቶች ከልቦለዶቹ ታሪክ ለይቶ በማውጣት ለትንተና በሚያመች መልኩ በመመደብ  ሚታዊ ባህሪ ያላቸው ሁነቶች ከልቦለዶቹ ታሪክ ጋር እንዴት ውህደት እንደ ፈጠሩና ሚታዊ ባህርያት ያሏቸው ሁነቶች በልቦለዶቹ ታሪኮች ቀጣይነት ላይ ስላበረከቱት አስተዋጽኦ ለመርመር የሞከረ ነው፡፡ ለዚህም የሚቶሎጂና ስነፅሁፍን ድንበር መሰረት ያደረጉ ንድፈሃሳቦችን ለጥናቱ በሚያመች መልኩ በማሰናዳት ለትንተናው ማስኬጃነት አውሏል፡፡ ልቦለዶቹ ውስጥ ያሉትን ሚታዊ ሁነቶች ከአላማው አንፃር ለመመርመር ያመቹ ዘንድ የሁነቶችን ተለጣጣቂነት በመፍጠተር እና ጉዞ ትልም (ምንን እና ለምንን) በማሳየት  በሚሉ ሁለት ክፍሎች ተከፍለዋል፡፡ በምርምሩ ለማረጋገጥ እንደተሞከረው በልቦለዶቹ ውስጥ ሚታዊ ባህሪያት ያሏቸው ሁነቶች በታሪኮቹ ውስጥ በመግባታቸው በልቦለዶቹ ታሪክ ውስጥ ያሉ ሁነቶች ጥምረት የሰመረ እንዲሆን፣ ትልማቸውን ለመገንባትና ጥብቅ እንዲሆን ለማድረግ፣ ታሪኮቹ ተአማኒነትን እንዲላበሱ፣  አግባባዊ በሆነ መንገድ ታሪኮቹ አቅጣጫቸውን እየቀየሩ የልቦለዱ ይዘት እንዲያሰፉና ታሪኩ ወደፊት እንዲቀጥል ጉልህ ሚና እንደተጫወቱ ታይቷል፡፡

# ማውጫ

ይዘት ገጽ

ምስጋና……………………………………………………………………………I
አጠቃሎ……………………………………………………………………………II
ማውጫ……………………………………………………………………………III
ምዕራፍ አንድ ........................................................................................ 10
መግቢያ ................................................................................................ 10
1.1 የጥናቱ ዳራ ........................................................................................ 10
1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ........................................................................ 14
1.3 የጥናቱ ዓላማ ..................................................................................... 14
1.4 የምርምር ጥያቄዎች ............................................................................... 15
1.4.1 ዓብይ የምርምር ጥያቄ ........................................................................ 15
1.4.2 ንዑሳን የምርምር ጥያቄዎች .................................................................. 15
1.5 የጥናቱ ጠቀሜታ .................................................................................. 15
1.6 የጥናቱ ወሰን ...................................................................................... 16
1.7 የምዕራፍ አደረጃጀት ............................................................................. 16
ምዕራፍ ሁለት ........................................................................................ 17
ክለሳ ድርሳናት ....................................................................................... 17
2.1 ንድፈ ሃሳባዊ ዳራ .................................................................................. 17
2.1.1 የሚት ምንነት ................................................................................... 17
2.1.2 የሚት አፈጣጠር ................................................................................ 22
2.1.3 ሚትን የድሮ ነገር ብቻ አድርጎ መደምደም የማይቻል ስለመሆኑ ............................ 23
2.1.4 የሚት ምደባ ...................................................................................... 24
2.1.5 የሚት አይነተኛ ጠባያት ...................................................................... 25
2.1.6 የሚት ተግባራት .................................................................................. 28
2.1.7 የሚት ተረክ አላባውያን ........................................................................ 29

2.1.8 ሚትና ስነ ፅሑፍ ........................................ 33
2.1.9 ሚቶ ኪን (mythopoesis) ........................................ 38
2.2 የተዛማጅ ጽሁፎች ቅኝት ........................................ 40
ምዕራፍ ሦስት ........................................ 47
የጥናቱ ሥነ-ዘዴና ዘዴዎች ........................................ 47
3.1. የጥናቱ ሥነ-ዘዴ ........................................ 47
3.2 የጥናቱ ዘዴ ........................................ 48
3.2.1 የመረጃ ምንጭ ........................................ 48
3.2.2 የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ........................................ 49
3.2.3 የናሙና አመራረጥ ........................................ 49
3.2.4 የመተንተኛ ስልት ........................................ 49
ምዕራፍ አራት ........................................ 52
የመረጃ ትንተና ........................................ 52
4.1 የልቦለዶቹ አፅመ-ታሪክ ........................................ 52
4.1.1 የዝጎራ ረጅም ልቦለድ ጭምቀ ታሪክ ........................................ 53
4.1.2 የመርበብት ረጅም ልቦለድ ጭምቀ ታሪክ ........................................ 56
4.2 ለልቦለዶቹ ታሪክ ማስኬጃነት የሚታዊ ሁነቶች ፋይዳ ትንተና ........................................ 62
4.2.1 የሁነቶችን ተለጣጣቂነት በመፍጠር ........................................ 63
4.2.2 ጉዞ ትልም (ምንን እና ለምንን) በማሳየት ........................................ 76
ምዕራፍ አምስት ........................................ 87
ማጠቃለያ እና አስተያየት ........................................ 87
5.1 ማጠቃለያ ........................................ 87
5. 2 አስተያየት ........................................ 90
ዋቢዎች ........................................ 92